# የኢትዮጵያ፡ ባህል፡ ጥናት ።

ከብላቴን፡ ጌታ፡ ማኅተመ፡ ሥላሴ፡ ወ፡ መ፡ ተዘጋጀ ፡

# ባለን፡ እንወቅበት ።

**(Apprenons à connaître ce que nous possedons)**

አዲስ፡ አበባ፡ ሺ፲፱፻፷፩ ዓ፡ ም፡

Niguss
Digital Library

## የኢትዮጵያ ፡ ባህል ፡ ጥናት።

# ባለን ፡ እንወቅበት።

(Apprenons à connaître ce que nous possedons)

ከብላቴን ፡ ጌታ ፡ ማኅተመ ፡ ሥላሴ ፡ ወልደ ፡ መስቀል ፡ ተዘጋጅቶ ፡
ለዓለም ፡ አቀፍ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ጥናት ፡ ጉባዔ ፡
በጥር ፡ ፳፯ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፵፰ ፡ ዓ ፡ ም ፡ የቀረበ።

አዲስ ፡ አበባ ፡ ሐምሌ ፡ ሺ፱፻፹፩ ዓ ፡ ም ፡
በአርቲስቲክ ፡ ማተሚያ ፡ ሊሚትድ ፡ ታተመ።

# ማውጫ

ማስገንዘቢያ ........................................................... 4

መግቢያ። ........................................................... 5

አንደኛ ፡ ክፍል። ........................................................... 7

የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ጠባይ ፡ ........................................ 7

ፈሪሃ ፡ እግዚአብሔር ፡ ........................................ 7

ትሕትና ፡ ........................................ 7

ርኅራሄ ፡ ........................................ 7

ታማኝነት ፡ ........................................ 8

ቃል ፡ ኪዳን ፡ መጠበቅ ፡ ........................................ 8

እንግዳ ፡ ተቀባይነት ፡ ........................................ 8

እውነተኛነትና ፡ ሐቀኝነት ፡ ........................................ 9

ሁለተኛ ፡ ክፍል። ........................................................... 11

የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ የተፈጥሮ: ችሎታ ........................................ 11

፩ ፡ ምሳሌ። ........................................ 11

፪ ፡ አማርኛ ፡ ቅኔ። ........................................ 18

፫. ተረት ........................................ 26

፬ ፡ ቧልት። ........................................ 31

፭ ፡ ዕንቆቅልሽ። ........................................ 33

ሦስተኛ ፡ ክፍል ........................................................... 41

የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ያገር ፡ ባህሎች። ........................................ 41

ሀ ፡ በአንደበት ፡ የሚገለጡ። ........................................ 41

ለ ፡ ኃይልንና ፡ ልምድን ፡ ማሰላሰልንና ፡ ቅልጥፍናን ፡ የተፈጥሮ ፡ ስጦታን ፡ ወይም ፡ ዝንባሌን ፡ የሚጠይቁ ፡ ባ ህ ሎ ች። ............. 70

# ማስገንዘቢያ

«ባለን ፡ እንወቅበት» ፡ የተባለውን ፡ መጽሐፍ ፡ ያዘጋጀሁት ፡ በ፲፱፻፲፫ ፡ ዓ.ም ፡ በአዲስ ፡ አበባ ፡ በተደረገው ፡ ዓለም ፡ አቀፍ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ጥናት ፡ ጉባዔ ፡ ላይ ፡ እንዲነበብ ፡ ነበር። ሀሳቡም ፡ በሀገራችን ፡ ጠቃሚ ፡ የሆኑ ፡ ከጥንት ፡ ሲያያዙ ፡ መጥተው ፡ ለኛ ፡ የደረሱ ፡ ብዙ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ባህሎችና ፡ ልምዶች ፡ ያሉን ፡ መሆናቸውን ፡ ለመግለጽ ፡ ነበር። ምክንያቱም ፡ ኢትዮጵያ ፡ ለምርምር ፡ የተመቸች ፡ ሀገር ፡ በመሆኗ ፡ ግራና ፡ ቀኝ ፡ ፊትና ፡ ኋላ ፡ ቢሄዱ ፡ የማያደናቅፉ ፡ ሰፋፊ ፡ የጥናት ፡ መስኮች ፡ አሏት ፡ ስል ፡ በዚሁ ፡ ዓመት ፡ ቀደም ፡ ብዬ ፡ በሽልማቱ ፡ ሥነ ሥርዓት ፡ ጊዜ ፡ ተናግሬ ፡ ነበርና ፡ ይህንኑ ፡ በተሰበሰቡት ፡ ሰዎች ፡ መኻከል ፡ ለማረጋገጥ ፡ ስል ፡ ነበር። ዳሩ ፡ ግን ፡ ላንዳንዱ ፡ ተናጋሪ ፡ ተመድቦ ፡ የነበረው ፡ ሰዓት ፡ ከ፳ ፡ ደቂቃዎች ፡ የማይበልጥ ፡ ሆነ። ስለዚህም ፡ የተዘጋጀውን ፡ ለማንበብ ፡ ባለመቻሉ በመጭመቅና ፡ በማሳጠር ፡ «የቀድሞው ፡ ዘመን ፡ ጨዋ ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ ጠባይና ፡ ባህል» ፡ የተባለችውን ፡ ጽሑፍ ፡ ማዘጋጀት ፡ ግድ ፡ ሆነብኝ። ሆኖም ፡ ይህ ፡ «ባለን ፡ እንወቅበት» ፡ የተባለውም ፡ መጽሐፍ ፡ በተጨማሪ ፡ መቅረቡና ፡ በጉባዔው ፡ ላይ ፡ ለተሰበሰቡት ፡ ተጋባዦች ፡ ሁሉ ፡ መታደሉ ፡ አልቀረም።

አሁን ፡ አንባቢዎቼን ፡ የምጠይቃቸው ፡ ወይም ፡ የምለምናቸው ፡ ጥናቱ ፡ የተሻለ ፡ መልክ ፡ እንዲይዝ ፡ ምንም ፡ የሁለቱም ፡ ዓላማ ፡ አንድ ፡ ቢሆን ፡ ሁሉንም ፡ እንዲመለከቷቸው ፡ ነው። ካሁን ፡ በፊት ፡ ሁለቱም ፡ መጽሐፎች ፡ ተዘጋጅተው ፡ የነበረው ፡ «በእስቴንሲል» ፡ ነበር ፡ ስለዚህም ፡ ቁጥሩ ፡ የተወሰነ ፡ ስለሆነ ፡ ባሁኑ ፡ ሰዓት ፡ ማግኘት ፡ አዳጋች ፡ ነው። በዚህ ፡ ላይ ፡ የፈላጊውና ፡ የጠያቂው ፡ ብዛት ፡ (ይልቁንም ፡ ከውጭ ፡ ሀገር) ፡ እየጨመረ ፡ ስለሄደ ፡ እነሆ ፡ በደንበኛው ፡ አሠራር ፡ በማተሚያ ፡ ቤት ፡ እንዲታተም ፡ ተደርጓል። ይህም ፡ ከተፈለገ ፡ ለማግኘት ፡ አዳጋች ፡ አይሆንም ፡ ማለት ፡ ነው።

ብላቴን ፡ ጌታ ፡ ማኅተመ ፡ ሥላሴ ፡ ወልደ ፡ መስቀል።
አዲስ ፡ አበባ ፡ ፲፱፻፹፩ ፡ ዓ ፡ ም።

# መግቢያ።

የቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴን ፡ የ፲፱፻፶፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡ የሥነ ፡ ጽሑፍ ፡ ሽልማት ፡ በተቀበልኩበት ፡ ዕለት ፡ ባደረግሁት ፡ ንግግር ፡ ላይ ሀገራችን ፡ ግራና ፡ ቀኝ ፡ ቢሄዱ ፡ የማያደናቅፍ ፡ ለጥናት ፡ የተመቸ ፡ ሰፊ ፡ መስክ ፡ ስለ ፡ አላት ፡ ወጣቶቻችን ፡ «ባለን እንወቅበት» ፡ የሚለውን ፡ ዓላማ ፡ በመከተል ፡ ተግተው ፡ መሥራትና ፡ ውጤቱን ፡ ለኛም ፡ ሆነ ፡ ለዓለም ፡ መግለጽ ይኖርባቸዋል ፡ ስል ፡ መናገሬን ፡ አስታውሳለሁ። ይህም ፡ ምን ፡ ማለት ፡ እንደሆነ ፡ በንግግር ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ የሚጨበጡ ፡ ማስረጃዎችን ፡ በመስጠት ፡ ጭምር ፡ ማስረዳት ፡ አስፈላጊ ፡ መስሎ ፡ ይታያል።

የሀገራችን ፡ ሕዝብ ፡ ጠባይ ፡ የተፈጥሮ ፡ ችሎታና ፡ ልምድ ፡ በዝዬ ፡ የተለያዩና ፡ የበዙም ፡ እንደመሆናቸው ፡ መጠን ፡ ጥልቅ ፡ የሆነ ፡ ምርመራ ፡ ቢደረግ ፡ አጥኚዎችን ፡ የሚያረኩ ፡ የባህል ፡ መረጃዎች ፡ እንደሚገኙ ፡ ጥርጥር ፡ የለውም ፡ ይህንኑም ፡ በመመልከት ፡ በዚህ ፡ ጽሑፍ ፡ ውስጥ ፡ ጠቅላላ ፡ የሆኑ ፡ መግለጫዎችን ፡ አቅርቤአለሁና ፡ አስተውለው ፡ እንዲመለከቷቸው ፡ አንባቢዎቼን ፡ አስቀድሜ ፡ እለምናቸዋለሁ።

ከሁሉ ፡ በፊት ፡ «ባለን ፡ እንወቅበት» ፡ ያልኩበት ፡ ምክንያት ፡ ምንም ፡ ታሪክ ፡ ቅርሳችን ፡ ሰፊና ፡ አጥጋቢ ፡ ቢሆን ፡ ከባህላችንም ፡ የሚበልጠው ፡ በዓሥርቱ ፡ ቃላተ ፡ ኦሪትና ፡ በስድስቱ ፡ ቃላተ ፡ ወንጌል ፡ ላይ ፡ የተመሠረተ ፡ በጎ ፡ ሥራን ፡ የተጎናጸፈ ፡ ሆኖ ፡ ቢገኝ ፡ ከዚህም ፡ በላይ ፡ ተወዳጅነት ፡ ያላቸው ፡ ጠባዮችና ፡ ልምዶችከሚያኮራ ፡ ግብረ ፡ ገብነት ፡ ጋራ ፡ ያልተለዩን ፡ ቢሆኑ ፡ እነዚህን ፡ በትክክል ፡ አላወቅ ናቸውምና ፡ እየተመራመርን ፡ እንድንረዳቸውና ፡ እንድንጠቀምባቸው ፡ ለማለት ፡ ነው።

ምንም ፡ እንኳ ፡ ዓለም ፡ «በቴክኖሎዝ» ፡ እና ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ጥበባት ፡ ረገድ ፡ በአለበት ፡ ሳይቆይ ፡ ከጊዜ ፡ ወደ ፡ ጊዜ ፡ በመራቀቅ ፡ በአሁኑ ፡ ሰዓት ፡ እስከ ፡ ዓለመ ፡ ጨረቃ ፡ የሚደርስበት ፡ ዕውቀት ፡ ለማግኘት ፡ የበቃ ፡ ቢሆንም ፡ በሰው ፡ ልጅ ፡ ዘንድ ፡ በሞራል ፡ በኩል ፡ መሻሻል ፡ የማያሻቸውና ፡ ባሉበት ፡ ሁናቴ ፡ ለዘለዓለም ፡ መጠበቅ ፡ የሚገባቸው ፡ ብዙ ፡ ጠቃሚ ፡ ጠባዮች ፡ አሉ። እንዳሉ ፡ ማቆየት ፡ ይጠቅማል ፡ የምለውም ፡ በደህና ፡ መጥፎን ፡ መለወጥ ፡ ጉዳታችን ፡ ስለሚሆን ፡ ነው።

እነዚህም ፡ በሀገራችን ፡ ይልቁንም ፡ በአንዳንድ ፡ የገጠር ፡ ነዋሪ ፡ ሕዝብ ፡ ዘንድ ፡ ተጠብቀው ፡ ሳይከለሱ ፡ ይገኛሉ።

አሁን ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ስለማይገኝ ፡ ንግግሬን ፡ በመግታትና ፡ በማሳጠር ፡ ስለኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ጠባይ ፡ ስለተፈጥሮው ፡ ስለችሎታው ፡ ስለባህሎቹና ፡ ስለጨዋታዎቹ ፡ ትንሽ ፡ መግለጫና ፡ ማሳሰቢያ ፡ ባጭሩም ፡ ቢሆን ፡ ለአንባቢዎቼ ፡ አቅርቤአለሁና ፡ መልካም ፡ ፈቃዳቸው ፡ ሆና ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ የተጻፈውን ፡ እንዲመለከቱልኝ ፡ በትህትና ፡ አሳስባለሁ።

ባላምባራስ ፡ ማኀተመ ፡ ሥላሴ ፡ ወልደ ፡ መስቀል።

ጥር ፡ ፳፯ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፺፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡

# አንደኛ ፡ ክፍል።

## የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ጠባይ ፡

### ፈሪሃ ፡ እግዚአብሔር ፡

የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ትንሣኤ ፡ ሙታንን ፡ ስለሚያምን ፡ ደግ ፡ በመሥራት ፡ ጽድቅ ፡ ክፉ ፡ በመሥራት ፡ ኲነኔ ፡ እንዳለ ፡ ያውቃል። ስለዚህም ፡ «የጥበብ ፡ መጀመሪያ ፡ እግዚአብሔርን ፡ መፍራት ፡ ነው» ፡ የሚለውን ፡ መሠረታዊ ፡ ሕግ ፡ ጠብቆ ፡ ሕሊናውን ፡ ንጹሕ ፡ አድርጎ ፡ ለመኖር ፡ ይጣጣራል ፡ የፈጣሪው ፡ ረድኤት ፡ እንዳይለየውም ፡ ጾምና ፡ ጸሎትን ፡ ማዘውተር ፡ ይወዳል። ይህንን ፡ በመፈጸም ፡ ክፉ ፡ ከማሰብና ፡ ከመሥራት ፡ ታጋሽነትን ፡ እንደሚአገኝ ፡ ያምናል።

### ትሕትና ፡

የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ በተፈጥሮው ፡ ትሑትና ፡ ሰው ፡ አክባሪ ፡ ነው። እንኳን ፡ የሚያውቀውን ፡ የማያውቀውንም ፡ ቢሆን ፡ በዕድሜ ፡ ከበለጠው ፡ እጅ ፡ በመንሳት ፡ ሰላምታ ፡ ሰጥቶ ፡ እርስዎ ፡ ብሎ ፡ ቦታ ፡ ይለቃል። ተቀምጦም ፡ እንደሆነ ፡ ተነስቶ ፡ ያነጋግራል ፡ በከብት ፡ ላይ ፡ እንደሆነ ፡ ይወርዳል። በማዕረጋቸውና ፡ በጨዋነታቸው ፡ ሊከበሩ ፡ የሚገባቸውን ፡ ሰዎች ፡ ጌታዬ ፡ እመቤቴ ፡ እንዲሁም ፡ በዕድሜ ፡ ታላቅ ፡ የሆኑትን ፡ አያ ፡ እንኮዬ ፡ እያለ ፡ ማነጋገር ፡ የተለመደ ፡ ተግባሩ ፡ ነው። ወጣቶች ፡ እንኳን ፡ እርስ ፡ በርሳቸው ፡ ሲከባበሩ ፡ ጋሼ ፡ አብዬ ፡ አበባዬ ፡ እትዬ ይባባላሉ።

### ርኅራኄ ፡

የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ርኅሩኅ ፡ ነው ፡ ወገኑ ፡ በተቸረ ፡ ጊዜ ፡ ያለውን ፡ ከፍሎ ፡ ይሰጣል ፡ ታስሮም ፡ እንደሆነ ፡ ዋስ ፡ ሆኖ ፡ ወይንም ፡ እንደ ፡ አቅሙ ፡ ዕዳውን ፡ በመክፈል ፡ ያስፈታል። የታመመን ፡

ይጠይቃል ፡ የታረዘን ፡ ያለብሳል ፡ የተራበን ፡ ያበላል ፡ የተጠማን ፡ ያጠጣል።

## ታማኝነት ፡

የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ በጣም ፡ ታማኝ ፡ ነው ፡ ጓደኛውን ፡ እንደ ፡ ወንድሙ ፡ ይወዳል ፡ የጌታውን ፡ ውለታ ፡ አይዘነጋም ፡ አሳዳሪው ፡ ቢደኸይ ፡ እንኳን ፡ በነበረው ፡ ጊዜ ፡ በልቼ ፡ ሲቸግረው ፡ አልለይም ፡ አልከዳም ፡ ብሎ ፡ ተጎድቶም ፡ ቢሆን ፡ አብሮት ፡ ይቀመጣል። አንዳንድ ፡ አሽከር ፡ ጌታው ፡ ሲሞት ፡ ውለታ ፡ ለመመለስ ፡ ብሎ ፡ ከልጅየው ፡ ጋር ፡ መኖርን ፡ ይቀጥላል ፡ ብዙ ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ሰዎች ፡ ከመጀመሪያ ፡ ሎሌዎቻቸው ፡ ጋር ፡ ረዥም ፡ ዘመን ፡ የሚኖሩ ፡ ይገኛሉ። አሽከሮቹም ፡ ጌታቸውን ፡ ዘመድ ፡ በሞተው ፡ ጊዜ ፡ የኀዘኑ ፡ ተካፋይ ፡ በመሆን ፡ ያጽናኑታል። ይህም ፡ የኢትዮጵያን ፡ ሰው ፡ ታማኝነት ፡ ከሚገልጹት ፡ ማስረጃዎች ፡ አንዱ ፡ ነው።

## ቃል ፡ ኪዳን ፡ መጠበቅ ፡

የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ቃሉን ፡ አክባሪ ፡ ነው ፡ በጽሕፈትም ፡ ባይሆን ፡ ያደረገውን ፡ ስምምነት ፡ ይጠብቃል። በጋብቻም ፡ ሆነ ፡ በንብረት ፡ ግዢና ፡ ሽያጭ ፡ ላይ ፡ የወረቀት ፡ ስምምነት ፡ ሳያስፈልገው ፡ በሰጠው ፡ ቃል ፡ ብቻ ፡ ይጸናል። በዱሮ ፡ ጊዜ ፡ ከአባቶቻችን ፡ እንደሰማነው ፡ ብዙ ፡ መኳንንትና ፡ ሀብታሞች ፡ ገንዘባቸውን ፡ ለነጋዴ ፡ እንዲሠራበት ፡ ሲሰጡ ፡ ያለጽሑፍና ፡ ያለምስክር ፡ ነበር ፡ ይባላል። አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ምንም ፡ እንካ ፡ ቃሉን ፡ የማያከብር ፡ ሰው ፡ ባይጠፋም ፡ በጠቅላላው ፡ በአንድ ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ ላይ ፡ የሚገኘው ፡ ታማኝነት ፡ መጠኑ ፡ በቀላሉ ፡ የሚገመት ፡ አይደለም።

## እንግዳ ፡ ተቀባይነት ፡

የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ እንግዳ ፡ በመቀበል ፡ የታወቀና ፡ ስመ ፡ ጥሩ ፡ ነው። ይልቁንም ፡ ለውጭ ፡ አገር ፡ ሰዎች ፡ ባይተዋር ፡ በመሆናቸው ፡ የተለየ ፡ ክብርና ፡ አስተያየት ፡ ይሰጣቸዋል ፡ ሰው ፡

ወደ ፡ ቤቱ ፡ በመጣ ፡ ጊዜም ፡ ሙብሉን ፡ መጠጡን ፡ ከብቱን ፡ ለእርድ ያቀርባል። የአንዳንድ ፡ ክፍለ ፡ ሀገር ፡ ሕዝብ ፡ ደግሞ ፡ እንግዳ ፡ ባየ ፡ ጊዜ ፡ ተሽቀዳድሞ ፡ ከቤቱ ፡ እንዲገባለት ፡ ይለምናል። ኃሣቡ ፡ ሳይፈጸምለት ፡ ቢቀር ፡ ግን ፡ ያዝናል ፡ ይቀየማል ፡ ይህም ፡ በእውነቱ ፡ እጅግ ፡ የሚያስደስትና ፡ የሚያኮራ ፡ ደግነትና ፡ ርኅሩኅነት ፡ የተመላበት ፡ የተቀደሰ ፡ ተግባር ፡ ስለሆነ ፡ ሊያስመሰግነው ፡ ይገባል። በኤኮኖሚም ፡ ረገድ ፡ ቢሆን ፡ እንኳን ፡ ዝናን ፡ አትርፎ ፡ ወዳጅ ፡ ስለሚገዛበት ፡ ያለ ፡ አግባብ ፡ ሃብት ፡ ባከነ ፡ የሚያሰኝ ፡ አይደለም።

## <u>እውነተኛነትና ፡ ሐቀኝነት ፡</u>

የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ በጣም ፡ ሐቀኛ ፡ ነው ፡ ሙት ፡ ካለ ፡ ቃሉን ፡ አያጥፍም ፡ በራሱ ፡ ይመሰክራል ፡ ቅጣት ፡ የሚያስከትልበትም ፡ ቢሆን ፡ ያደረገውን ፡ አይክድም ፡ በነፍስ ፡ ግዳይ ፡ የተያዘ ፡ ቢሆን ፡ እንኳ ፡ «ቢያናድደኝ ፡ ቢዝትብኝ ፡ ገደልኩት» ፡ ይላል ፡ እንጂ ፡ አልታየሁም ፡ በማለት ፡ የሚያከራክርና ፡ የሚያጓትት ፡ ነገር ፡ አያመጣም። ይህም ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ምን ፡ ያህል ፡ እውነተኛ ፡ መሆኑን ፡ ያስረዳል። ለምሳሌ ፡ ያህል ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ አንዳንዶቹን ፡ ብጠቅስም ፡ በሀገራችን ፡ የሚገኙት ፡ የሚያኮሩን ፡ ጠባዮችና ፡ ልምዶች ፡ አያሌ ፡ ናቸው ፡ እነዚህም ፡ ከማናቸውም ፡ የበለጡ ፡ የሰው ፡ ልክ ፡ መገመቻና ፡ መመዘኛ ፡ መሆናቸውን ፡ ማመን ፡ አለብን ፡ ስለዚህም ፡ አንድ ፡ በአንድ ፡ እየተከታተሉ ፡ የነበሩበትንና ፡ አሁንም ፡ ያሉበትን ፡ ሁናቴ ፡ ጠንቅቆ ፡ ማወቅ ፡ የአስተዋይ ፡ ተመራማሪዎች ፡ ፋንታ ፡ መሆን ፡ ይገባዋል። ሆኖም ፡ በአሁኑ ፡ ሰዓት ፡ አንዳንድ ፡ የከተማ ፡ ነዋሪዎች ፡ ያኮሩናል ፡ የምንላቸውን ፡ የተፈጥሮ ፡ ጠባዮች ፡ ውርደት ፡ እንደሚያስከትሉባቸውና ፡ የበታችነትም ፡ እንደሚያመጡባቸው ፡ ቆጥረው ፡ ማን ፡ ከማን ፡ ይበልጣል ፡ በሚል ፡ የተሳሳተ ፡ ኃሣብ ፡ እየተመሩ ፡ በመንቀፍና ፡ በመሠረዝ ፡ ላይ ፡ እንደሚገኙ ፡ ለመረዳት ፡ ተችሏል። ይህም ፡ በእውነቱ ፡ መላ ፡ ኢትዮጵያውያንን ፡ እንደሚያስቆጣና ፡ እንደሚያሳዝን ፡ ጥርጥር ፡ የለውም።

ከዚህ ፡ በላይ ፡ የገለጽኩት ፡ በጠባይና ፡ በባሕርይ ፡ በኩል ፡ ያለውን ፡ ስለሆነ ፡ አሁን ፡ ደግሞ ፡ የተፈጥሮ ፡ ችሎታውን ፡ ስለሚመለከቱት ፡ አንዳንድ ፡ መግለጫዎች ፡ አቀርባለሁ። የተፈጥሮ ፡ ችሎታውንም ፡ ስል ፡ የግብርናውን ፡ ወይም ፡ የተግባረ ፡ ዕዱን ፡ ሁናቴ ፡ ለመናገር ፡ አይደለም ፡ የተፈጥሮ ፡ ችሎታው ፡ የምለው ፡ ግን ፡ ምሳሌውን ፡ አማርኛ ፡ ቅኔውን ፡ ተረቱን ፡ ቧልቱን ፡ ዕንቆቅልሹን ፡ ሽለላውንና ፡ ፉከራውን ፡ ተጠየቅ ፡ ልጠየቅ ፡ የሚባለውን ፡ ጥያቄና ፡ መልሱን ፡ በላ ፡ ልበልህ ፡ የሚባለውን ፡ ውርዱን። ዘፈኑን ፡ ልቅሶውን ፡ ይህንና ፡ ይህንን ፡ የመሰለውን ፡ ሁሉ ፡ ነው።

ስለ ፡ እያንዳንዱም ፡ በዝርዝር ፡ ቢጠና ፡ የተስፋፋና ፡ የተሟላ ፡ መግለጫ ፡ ለመስጠት ፡ የሚያዳግት ፡ አይሆንም። እኔ ፡ ግን ፡ ልገልጸው ፡ የምፈልገው ፡ ስለዋና ፡ ዋናዎቹ ፡ ብቻ ፡ ያለኝን ፡ ጠቅላላ ፡ አስተያየት ፡ ነው። ጠልቆ ፡ መመራመር ፡ አርቆ ፡ መመልከት ፡ አስፋፍቶ ፡ መረዳት ፡ እና ፡ ተራቅቆ ፡ መድረስ ፡ የአጥኝዎችና ፡ የመምህራኑ ፡ ፋንታ ፡ ስለሆነ ፡ ትቼዋለሁ።

ወደፊት ፡ በምሰጠው ፡ መረጃ ፡ ላይ ፡ ጥልቅ ፡ ምሥጢር ፡ የያዙትን ፡ ግጥሞች እንዳይቃወሱ ፡ በማሰብ ፡ ያለ ፡ ትርጉም ፡ እንዳሉ ፡ ለማቅረብ ፡ ተገድጃለሁ። እነዚህንም ፡ በውጭ ፡ አገር ፡ ቋንቋ ፡ ለመፍታት ፡ ምን ፡ ያህል ፡ አስቸጋሪ ፡ እንደሆነ ፡ በሁሉም ፡ ዘንድ ፡ የታወቀ ፡ ነው። እያንዳንዱ ፡ ቃል ፡ የሚሰጠውን ፡ ስሜት ፡ ከነወዙና ፡ ከነለዛው ፡ ተርጉሞ ፡ ለማሰማት ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ችግር ፡ የሚያስከትል ፡ ነው። ከሞላ ፡ ጎደል ፡ በንግግር ፡ መግለጥ ፡ የሚቻል ፡ ቢሆን ፡ እንኳ ፡ ጣዕሙና ፡ ለዛው ፡ እንደሚቀነስ ፡ ጥርጥር ፡ የለውም። ስለዚህ ፡ አሁን ፡ ከዚህ ፡ የበለጠ ፡ ማስረዳት ፡ ስለማያሻኝ ፡ የተነሣሁበትን ፡ ዓላማዬን ፡ ተከትዬ ፡ አሳቤን ፡ እቀጥላለሁ።

# ሁለተኛ ፡ ክፍል።

## የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ የተፈጥሮ፡ ችሎታ

### ፩ ፡ ምሳሌ።

ምሳሌዎች ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜም ፡ ተረቶች ፡ የምንላቸው ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ሁናቴ ፡ የሀገራችንን ፡ ጠቅላላ ፡ መልክ ፡ የሚያሳዩ ፡ ናቸው ፡ እነዚህም ፡ በሕዝብ ፡ እጅ ፡ ገብተው ፡ በዘመን ፡ ብዛት ፡ መልካቸው ፡ ቢለወጥም ፡ ከተመራማሪዎች ፡ ከአርቆ ፡ ተመልካቾች ፡ ከአስተዋዮች ፡ በዕውቀት ፡ ከበሰሉ ፡ ሰዎች ፡ ማለት ፡ ከመምህራን ፡ ከአዋቆች ፡ የተገኙ ፡ መሆናቸው ፡ የማያጠራጥር ፡ ነው።

የአባቶች ፡ ቅርስ ፡ ተብሎ ፡ በተሰየመው ፡ መጽሐፍ ፡ ውስጥ ፡ ተሰብስበው ፡ የሚገኙት ፡ ተረቶች ፡ ወይም ፡ ምሳሌዎች ፡ የሚሰጡት ፡ ትምሕርት ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ግምት ፡ ያለው ፡ ነው። የሚበልጡትም ፡ በአሠርቱ ፡ ቃላተ ፡ ኦሪትና ፡ በስድስቱ ፡ ቃላተ ፡ ወንጌል ፡ የተደነገጉትን ፡ መለኮታዊ ፡ ትእዛዞችን ፡ ከመከተላቸው ፡ ሌላ ፡ ከኦሪትም ፡ ከሐዲስም ፡ የተውጣጡ ፡ አንዳንድ ፡ ሃሳቦችን ፡ የሚመለከቱ ፡ መስለው ፡ ይታያሉ።

በተለይም ፡ በሕሊና ፡ ርትዕን ፡ መሠረት ፡ በማድረግ ፡ የሚነገሩት ፡ ምሳሌዎች ፡ ምን ፡ ያህል ፡ የማስረዳት ፡ኃይለ ፡ ቃል ፡ እንዳላቸው ፡ መገንዘብ ፡ ኣስቸጋሪ ፡ አይደለም ፡ እነዚህም ፡ ከአባት ፡ ለልጅ ፡ እየተላለፉ ፡ ለእኛ ፡ የደረሱን ፡ ምሳሌዎች ፡ በአለፈው ፡ ጊዜ ፡ የሕግ ፡ አንቀጾች ፡ ሆነው ፡ በየአደባባዩ ፡ ሲሠራባቸው ፡ ቆይተዋል።

ስለዚህም ፡ በፍርድ ፡ ረገድ ፡ በቀድሞ ፡ ዘመን ፡ በነገሥታቱ ፡ ችሎታ ፡ ላይ ፡ ፍትሐ ፡ ነገሥት ፡ በአለው ፡ ኃይል ፡ መጠን ፡ በዳኞችም ፡ ሆነ ፡ በጠበቆች ፡ ዘንድ ፡ ታላቅ ፡ አገልግሎት ፡ አበርክቷል ፡ ለማለት ፡ እችላለሁ ፡ ከላይ ፡ የተነገረውን ፡ ለማስረዳት ፡ ለምሳሌ ፡ ያህል ፡ እነሆ ፡ በአጭሩ ፡ የሚቀጥለውን ፡ መግለጫ ፡ ለመስጠት ፡ እሞክራለሁ።

## (ሀ) ልዩ ፡ ልዩ ፡ ትምሕርት ፡ የሚሰጡ ፡ ምሳሌዎች።

### ፩ ፡ ሞኝ ፡ ወርውረው ፡ ቢስቱት ፡ ያልወጉት ፡ ይመስለዋል።

ማስተዋልና ፡ ማመዛዘን ፡ ያነሰው ፡ ሰው ፡ ባይመታም ፡ ባይረታም ፡ በአቅም ፡ ማነስ ፡ ወይም ፡ በልዩ ፡ ምክንያት ፡ ቢሳትም ፡ ድርጊቱን ፡ እንዳልተፈጸመበት ፡ ያህል ፡ ይቆጥረዋል ፡ እንደ ፡ እውነቱ ፡ «የወጋ ፡ ቢረሳ ፡ የተወጋ ፡ አይረሳ» ፡ የተባለውን ፡ ምሳሌ ፡ መዘንጋት ፡ ኣይገባም።

### ፪ ፡ ዋስ ፡ ካለው ፡ ዱቄትኽን ፡ ለነፋስ ፡ አበድረው።

ብድር ፡ ጠያቂው ፡ ያልታመነ ፡ ወይም ፡ ንብረቱ ፡ ዝቅተኛ ፡ ቢሆንም ፡ ዋሱ ፡ አጥጋቢ ፡ ከሆነ ፡ በርሱ ፡ አማካይነት ፡ ብድሩ ፡ ይሰጠው ፡ ማለት ፡ ነው።

### ፫ ፡ ከአፍ ፡ የወጣ ፡ ቃል ፡ ከእጅ ፡ የወደቀ ፡ እንቁላል።

ከእጅ ፡ የወደቀ ፡ እንቁላል ፡ መፍረጡ ፡ መፍረሱና ፡ መሰበሩ ፡ እንደማይጠረጠር ፡ ሁሉ ፡ ከአፍ ፡ የወጣውን ፡ ቃልም ፡ እሰውጆሮ ፡ ስለሚደርስ ፡ ማስቀረት ፡ አለመቻሉን ፡ ስለመግለጥ።

### ፬ ፡ ዓሣ ፡ ጐርጓሪ ፡ ዘንዶ ፡ ያወጣል ፡ የሰው ፡ ፈላጊ ፡ የራሱን ፡ ያጣል።

ዓሣ ፡ በመቃጥን ፡ እና ፡ በመረብ ፡ ሲያዝ ፡ አልጠግብ ፡ ባይ ፡ በእጅ ፡ ለመያዝ ፡ ዐለቱን ፡ በመፈንቀል ፡ ዘንዶ ፡ እንዲያወጣ ፡ ከአምላክ ፡ ያልታደሉትን ፡ የሰው ፡ ሃብት ፡ አንጋጦ ፡ ማየትም ፡ የራስን ፡ እስከማጣት ፡ ያደርሳል።

### ፭ ፡ ሳይበሉ ፡ ማግሳት ፡ ልክበር ፡ ብሎ ፡ መጓጓት።

ሳይበሉ ፡ ማግሳት ፡ እንደማይቻል ፡ ሳይሠሩ ፡ ለመክበር ፡ መመኘትም ፡ በሃሳብ ፡ ውቅያኖስ ፡ ተውጦ ፡ እንደመቅረት ፡ ያለ ፡ ነው።

### ፮ ፡ ሳይተርፋት ፡ አበደረች ፡ ሳትቀበል ፡ ሞተች።

ለብልጭልጭ ፡ እና ፡ ለከንቱ ፡ ነገር ፡ እንዲሁም ፡ ይወቁልኝ ፡ የሚሠራ ፡ ራሱን ፡ እንኳ ፡ እንደማይጠቅም ፡ ለውዳሴ ፡ ከንቱ ፡ ያበደረችም ፡

ሳትቀበለው ፡ ሞተች።

## ፺ ፡ የወጋ ፡ ቢረሣ ፡ የተወጋ ፡ አይረሳ።

ሞት ፡ ቢዘገይ ፡ እንደማይቀር ፡ ሁሉ ፡ በደል ፡ ቢቆይም ፡ አይረሳም ፡ በነገር ፡ የወጋው ፡ ቢዘነጋ ፡ እንኳ ፡ የተበደለው ፡ ሲቆረቁረው ፡ ይኖራል ፡ ቁስሉ ፡ ቢሽርም ፡ መዳው ፡ አይጠፋም።

## ፺፰ ፡ አመልና ፡ ቀንድ ፡ በስተኋላ ፡ ይበቅላል።

የእንሰሳት ፡ ቀንድ ፡ ቆይቶ ፡ እንደሚወጣ ሁሉ ፡ ሰውንም ፡ በጊዜ ፡ ብዛት ፡ የሚአስከትለው ፡ ነገር ፡ ስለማይታወቅ ፡ ፍጻሜውን ፡ ሳታይ ፡ በመጀመሪያ ፡ አትውደደው ፡ አታመስግነው።

## ፱ ፡ እወቁኝ ፡ ብሎ ፡ ደብቁኝ።

ወረተኛ ፡ ሰው ፡ በመጀመሪያ ፡ አለሁ ፡ አለሁ ፡ በማለት ፡ ባለሟል ፡ ወይም ፡ ዘመድ ፡ ይመስልና ፡ በኋላ ፡ የአገዳ ፡ መብራት ፡ ሲሆን ፡ ይታያል። እንዲሁም ፡ በሰላም ፡ ጊዜ ፡ ፎካሪና ፡ ባለጉራ ፡ ሆኖ ጦርነት ፡ ሲመጣ ለሚርበደበድና ፡ በነገር ፡ ሰው ፡ ሲያጠቃ ፡ ቆይቶ ፡ በተገለጠበት ፡ ጊዜ ፡ እንዳልሰማ ፡ ለመሆን ፡ ለሚጣጣር ፡ ወስላታ ፡ ሊጠቀስ ፡ ይችላል።

## ፲ ፡ ጥንቱን ፡ ባልዘፈንሽ ፡ ከዘፈንሽም ፡ ባላሳፈርሽ።

ቀድሞውኑ ፡ አለመጀመር ፡ አቅምን ፡ ማወቅ ፡ በጉዳዩ ፡ አለመግባት ፡ ደግ ፡ ነው ፡ ከጀመሩ ፡ ግን ፡ በነገሩ ፡ በሁኔታው ፡ መዝለቅ ፡ ይገባል።

## ፲፩ ፡ ወስፌ ፡ ሲለግም፡ ቅቤ ፡ አይወጋም።

ሰው ፡ ያለፈቃዱ ፡ ቢሠራ ፡ ፈር ፡ አያወጣም ፡ የሚያውቀውን ፡ እንኳን ፡ አላውቅም ፡ ሊል ፡ ይችላል ፡ ጉዳዩንም ፡ ከፍጻሜ ፡ አያደርስም።

## ፲፪ ፡ ዕንባ ፡ ሲሻኝ ፡ ጢስ ፡ ወጋኝ። (ላለቅስ ፡ ስፈልግ ፡ ጢስ ፡ ዓይኔን ፡ መታው)

ስፈልገው ፡ ተወሳልኝ ፡ ስመኘው ፡ ሳለ ፡ ሆነልኝ ፡ ወይም ፡ እንደፍላጎቴ ፡ ታዘዝሁ።

## (ለ) በፍርድ ፡ ላይ ፡ ይጠቀሱ ፡ የነበሩ ፡ ምሳሌዎች ፡ ከነማብራሪያቸው።

### ፩ ፡ ለዳኛ ፡ አመልከት ፡ እንዲሆን ፡ መሠረት።

ሕግ ፡ ለሰው ፡ ልጅ ፡ ኑሮ ፡ መሠረት ፡ ስለሆነና ፡ ዳኞችም ፡ የሕግ ፡ ባለአደራነት ፡ ስለተሰጣቸው ፡ በማናቸውም ፡ ረገድ ፡ ክርክርን ፡ የሚያስከትል ፡ ነገር ፡ ሲያጋጥም ፡ ወዲያውኑ ፡ ለዳኛ ፡ ማመልከት ፡ ጠቃሚነቱን ፡ ስለማስገንዘብ ፡ የተነገረ።

### ፪ ፡ ማን ፡ ይመስክር ፡ የነበር ፡ ማን ፡ ያርዳ ፡ የቀበር።

የአንድን ፡ ሰው ፡ ሞት ፡ የአሟሟቱን ፡ ታሪክ ፡ አጣርቶና ፡ አውቆ ፡ ነበርኩ ፡ ብሎ ፡ ማርዳት ፡ እንደሚገባ ፡ የምስክርነትም ፡ ቃል ፡ በቂ ፡ ሆኖ ፡ የሚገኘው ፡ ሲሸጥ ፡ ሲገዛ ፡ ወይም ፡ ሲመታ ፡ ሲገደል ፡ አይቻለሁ ፡ በማለት ፡ በተረጋገጠ ፡ ጊዜ ፡ መሆኑን ፡ ለማስገንዘብ ፡ ነው።

### ፫ ፡ ምስክር ፡ ለበለጠ ፡ ውድማ ፡ ለመለጠ።

ዓውድማውን ፡ በቀደምትነት ፡ ያዘጋጀ ፡ ገበሬ ፡ ባለመብት ፡ እንደመሆኑ ፡ መጠን ፡ በፍርድም ፡ ረገድ ፡ የበለጠ ፡ ምስክር ፡ የነገረለት ፡ የሚረታ ፡ መሆኑን ፡ ለማስረዳት።

### ፬ ፡ ምስክር ፡ ከተጠራ ፡ መሥዋዕት ፡ ከተሠራ።

ምሥዋዕት ፡ ከተዘጋጀ ፡ በኋላ ፡ ለቊርባን ፡ መቅረብ ፡ እንዳለበት ፡ ሁሉ ፡ ምስክርም ፡ አችሎት ፡ ከቀረበ ፡ በኋላ ፡ ቃሉን ፡ ሰጥቶ ፡ ይሄዳል ፡ እንጂ ፡ በአንድ ፡ መሰናክል ፡ ምክንያት ፡ መመለስ ፡ እንደማይገባው ፡ ለማስረዳት።

### ፭ ፡ ሰማንያ ፡ ለማገኛ ፡ ስለት ፡ ለማረጃ።

እንስሳት ፡ በስለት ፡ እንደሚታረዱ ፡ ሁሉ ፡ የማናቸውም ፡ ክርክር ፡ ነክ ፡ የሆነ ፡ ነገር ፡ ማቆሚያውና ፡ ማገኛው ፡ ባጭሩ ፡ መቆረጫው ፡ በ «ንጉሥ ፡ ይሙት» ፡ ሰማንያ ፡ ወይም ፡ መፈጠም ፡ መሆኑን ፡ ለማስገንዘብ።

### ፮ ፡ በሰማንያ ፡ ያለቀ ፡ በፀሐይ ፡ የደረቀ።

በፀሐይ ፡ የደረቀ ፡ ቅጠል ፡ ተመልሶ ፡ እንደማይለመልም ፡ ሁሉ ፡

በሰማንያ ፡ የተረታም ፡ እንደገና ፡ ወደ ፡ ክርክር ፡ ለመመለስ ፡ አለመቻሉን ፡ ለማስረዳት።

## ፯ ፡ በቆረጡት ፡ በትር ፡ ቢመቱ ፡ ባወጡት ፡ ዳኛ ፡ ቢረቱ ፡ የእግዜር ፡ ግቡ ፡ ከብቱ።

አንዱ ፡ ሌላውን ፡ አጠቃለሁ ፡ ብሎ ፡ በትር ፡ ይዞ ፡ ሔዶ ፡ ጠብ ፡ ካጫረ ፡ በኋላ ፡ በራሱ ፡ ዱላ ፡ ቢደበደብ ፡ እንደማይታዘንለት ፡ ሁሉ ፡ እንዲሁም ፡ በመረጠው ፡ ዳኛ ፡ ቢረታ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ሊያማርር ፡ እንደማይገባው ፡ ለማሳሰብ።

## ፰ ፡ በተለሙ ፡ ያርሷል ፡ በጀመሩ ፡ ይጨርሷል።

ገበሬ ፡ የመሬቱን ፡ አቀማመጥና ፡ የጎርፉን ፡ አወራረድ ፡ ተመልክቶ ፡ ምቹ ፡ በሆነው ፡ አቅጣጫ ፡ ተልሞ ፡ አዝመራውን ፡ ለመጨረስ ፡ እንደሚችል ፡ የክርክር ፡ ጭብጥንም ፡ ሆነ ፡ ድርሰትን ፡ ማንኛውንም ፡ ትችት ፡ መነሻውንና ፡ መድረሻውን ፡ አገናዝቦ ፡ መናገር ፡ ማዘጋጀት ፡ ማስፈለጉን ፡ ለማስረዳት።

## ፱ ፡ ባጉራ ፡ ጠናኝ ፡ የተረታ ፡ ማህል ፡ አገዳውን ፡ የተመታ።

ማህል ፡ አገዳውን ፡ ወይም ፡ ቅልጥሙን ፡ የተሰበረ ፡ መራመድ ፡ እንደማይችል ፡ ከዳኛ ፡ ቀርቦ ፡ ሲከራከር ፡ አጉራህ ፡ ጠናኝ ፡ ካለው ፡ ውርርዱን ፡ አንስቶ ፡ ክርክሩ ፡ መቆሙን ፡ ለማስረዳት።

## ፲ ፡ ባፈሳ ፡ ይታፈሳል ፡ በነጠር ፡ ይመለሳል።

በደል ፡ የሌለበት ፡ ሰው ፡ ገንዘብ ፡ ከበደለኞቹ ፡ ንብረት ፡ ጋራ ፡ ወይም ፡ ራሱ ፡ ባለቤቱ ፡ በወረራ ፡ ይያዝና ፡ ጥፋተኛ ፡ አለመሆኑ ፡ ከነጠረ ፡ በኋላ ፡ የተወሰደው ፡ ሀብት ፡ የሚመለስለት ፡ ወይም ፡ ራሱ ፡ የሚለቀቅ ፡ መሆኑን ፡ ለማስረዳት ፡ የተነገረ።

## ፲፩ ፡ በአፍ ፡ ይጠፉ ፡ በለፈለፉ።

በማያውቁት ፡ በማይገፉበት ፡ ጉዳይ ፡ ገብቶ ፡ መናገር ፡ ከትልቅ ፡ ውርደትና ፡ ቅሌት ፡ የሚያደርስ ፡ መሆኑን ፡ ለመግለጽ ፡ የሚጠቀስ።

## ፲፪ ፡ ንጉሥ ፡ የፈረደው ፡ ሠይፍ ፡ የቆረጠው።

በሠይፍ ፡ አንገቱን ፡ የተቆረጠ ፡ እንደማይድን ፡ ሁሉ ፡ በዙፋን ፡ ችሎት ፡ የተፈረደበትም ፡ ይግባኝ ፡ የሌለው ፡ መሆኑን ፡ ለማስረዳት ፡ የተነገረ።

## ፲፫ ፡ አንድ ፡ አይነድ ፡ አንድ ፡ አይፈርድ።

አንድ ፡ እንጨት ፡ ብቻውን ፡ እንደማይነድ ፡ አንድ ፡ ዳኛም ፡ ብቻውን ፡ አስችሎ ፡ መፍረድ ፡ እንደማይገባው ፡ ለማስረዳት ፡ የሚሰጥ ፡ ምሳሌ።

## ፲፬ ፡ ከራስ ፡ ወዲያ ፡ መስካሪ ፡ ከእግዜር ፡ ወዲያ ፡ ፈጣሪ።

ከእግዚአብሔር ፡ በላይ ፡ ፈጣሪ ፡ አለ ፡ ብሎ ፡ ማመን ፡ እንደማይቻል ፡ ሁሉ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ራሱ ፡ ገድያለሁ ፡ መትቻለሁ ፡ ሠርቄአለሁ ፡ በጠቅላላው ፡ አጥፍቻለሁ ፡ ካለ ፡ ሌላ ፡ ሳያስፈልግ ፡ ነገሩ ፡ ፍጻሜ ፡ ሊያገኝ ፡ መቻሉን ፡ ለመግለጥ ፡ ነው።

## ፲፭ ፡ ከአነጋገር ፡ ይፈረዳል ፡ ከአያያዝ ፡ ይቀደዳል።

ለምሳሌ ፡ ጨርቅ ፡ በሚገባ ፡ ከአልያዙት ፡ በትክክል ፡ እንደማይቀደድ ፡ ሁሉ ፡ እንዲሁም ፡ በክርክር ፡ ጊዜ ፡ ጉዳዩ ፡ በየመልኩ ፡ ተዘርዝሮ ፡ ለዳኛው ፡ ካልተነገረ ፡ ፍርዱ ፡ እንዳቀራረቡ ፡ የሚወሰን ፡ መሆኑን ፡ ለማስረዳት ፡ የሚነገር ፡ ጥቅስ።

## ፲፮ ፡ የሞተ ፡ አይከሰስ ፡ የፈሰሰ ፡ አይታፈስ።

የፈሰሰ ፡ ውሃ ፡ እንደማይታፈስ ፡ እንደዚሁም ፡ በሞተ ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ ክስ ፡ ሊቀርብ ፡ አለመቻሉን ፡ ለመግለጽ ፡ የሚጠቀስ።

## ፲፯ ፡ የሥራት ፡ መቋሚያው ፡ ፈጠም ፡ የሥጋ ፡ መቋሚያው ፡ ቅልጥም።

ጠቅላላውን ፡ አካል ፡ የሚሸከመው ፡ ቅልጥም ፡ እንደመሆኑ ፡ መጠን ፡ ፈጠምም ፡ የሥርዓት ፡ መጨረሻ ፡ የክርክር ፡ ማለቂያ ፡ መሆኑን ፡ የሚገልጽ።

## ፲፰ ፡ የተበደለ ፡ ከነጋሽ ፡ የተጠማ ፡ ከፈሳሽ።

የተጠማ ፡ ውሃን ፡ እንደሚሻ ፡ የተበደለ ፡ ሁሉ ፡ ጉዳቱን ፡ ለንጉሡ ፡ አሰምቶ ፡ የቀና ፡ ፍርድን ፡ ሊያገኝ ፡ ስለመቻሉ ፡ የሚነገር።

## ፲፱ ፡ የአባት ፡ ዕዳ ፡ ለልጅ ፡ የአፍንጫ ፡ እድፍ ፡ ለእጅ።

ከአፍንጫ ፡ የሚወጣ ፡ እድፍ ፡ ለእጅ ፡ እንደሚተርፈው ፡ ሁሉ ፡ አባትየው ፡ ተበድሮና ፡ ተለቅቶ ፡ በበላው ፡ ገንዘብ ፡ ልጁ ፡ በባለዕዳነት ፡ የሚጠየቅ ፡ መሆኑን ፡ ማስገንዘቢያ።

## ፳ ፡ ገድሎ ፡ ባለቃዬ ፡ ከሶ ፡ በጠበቃዬ።

ሰውን ፡ ገድሎ ፡ በአለቃዬ ፡ ማለት ፡ እንደማይቻል ፡ ሁሉ ፡ ከሳሽ ፡ ያስፈለገው ፡ እንደሆነም ፡ ጠበቃውን ፡ አስቀድሞ ፡ አዘጋጅቶ ፡ ከፍርድ ፡ አደባባይ ፡ መቅረብ ፡ እንጂ ፡ በከሰሰበት ፡ ነገር ፡ ከጠበቃዬ ፡ ብሎ ፡ ነገሩን ፡ እንዲያድር ፡ ማድረግ ፡ የማይገባ ፡ መሆኑን ፡ የሚያስገነዝብ።

## ፳፩ ፡ በልቶ ፡ መጠጥ ፡ ያጣ ፡ ተበድሎ ፡ ፍርድ ፡ ያጣ።

ምግብን ፡ ተመግቦ ፡ መጠጥ ፡ ያጣ ፡ ሰው ፡ የበላው ፡ እንደማይስማማው ፡ ሁሉ ፡ ተበድሎ ፡ ፍርድ ፡ ያጣም ፡ የተጎዳ ፡ መሆኑን ፡ ለመግለጽ ፡ የተነገረ።

## ፳፪ ፡ በርጥብ ፡ አያቃጥሉ ፡ በሰማኒያ ፡ አይቀጥሉ።

በእርጥብ ፡ ጭራሮ ፡ ወይም ፡ በእርጥብ ፡ ሣር ፡ እንጨት ፡ ሊቀጣጠል ፡ እንደማይችል ፡ የተፈረደበት ፡ ሰውም ፡ እከፍላለሁ ፡ እለቃለሁ ፡ ብሎ ፡ ከተፈጠመ ፡ በኋላ ፡ ለክርክሩ ፡ ምክንያት ፡ መፍጠር ፡ አለመቻሉን ፡ ለማስረዳት ፡ የተነገረ።

## ፳፫ ፡ በዋስ ፡ ያለ ፡ ከብት ፡ በጣት ፡ ያለ ፡ ቀለበት።

በጣት ፡ ያለ ፡ ቀለበት ፡ በእጅ ፡ የተጨበጠ ፡ ጥሪት ፡ እንደመሆኑ ፡ ንብረትና ፡ ሀብት ፡ በአለው ፡ ዋስ ፡ አማካይነት ፡ በብድር ፡ የተሰጠ ፡ ገንዘብ ፡ ተበዳሪው ፡ አልከፍልም ፡ ቢል ፡ እንኳን ፡ በዋሱ ፡ አማካይነት ፡ የሚገኝ ፡ መሆኑን ፡ ለማረጋገጥ ፡ የተሰጠ ፡ ምሳሌ።

## ፳፬ ፡ አለዳኛ ፡ ሙግት ፡ አለገመድ ፡ አክት።

እክት ፡ በገመድ ፡ ካልታበተ ፡ እንደሚበታተን ፡ ሁሉ ፡ ከሳሽና ፡ ተከሳሽ ፡ ዳኛ ፡ በሌለበት ፡ ሸንጎ ፡ ሲጨቃጨቁ ፡ ቢውሉ ፡ ለነገራቸው ፡ ውሳኔ ፡ የማይገኝለት ፡ ስለ ፡ መሆኑ ፡ የሚነገር ፡ ጥቅስ።

## ፪ ፡ አማርኛ ፡ ቅኔ።

ሕዝባችን ፡ ብልህ ፡ ነው ፡ ፈጥኖ ፡ የመረዳትና ፡ የማስረዳት ፡ ችሎታ ፡ አለው ፡ የነገርን ፡ አካሄድ ፡ ይመረምራል ፡ አስተዳደር ፡ ምክር ፡ ክርክር ፡ ዳኝነትና ፡ ፖለቲካ ፡ የተፈጥሮ ፡ ገንዘቡ ፡ ናቸው ፡ ስለዚህም ፡ ብዙ ፡ ሰው ፡ ያለ ፡ ትምህርት ፡ አእምሮው ፡ በስሎ ፡ ይታያል።

ከዚህም ፡ የተነሳ ፡ ነገር ፡ ሲያስረዳ ፡ ግጥም ፡ ሲገጥም ፡ ሙሾ: ሲያወርድ ፡ ሲመክር ፡ እና ፡ በንግግር ፡ ላይ ፡ ምሳሌ ፡ ሲሰጥ ፡ ለተመልካች ፡ ያስደንቃል። በግጥሞቹም ፡ ውስጥ ፡ ጣዕም ፡ ያላቸው ፡ ጥልቅ ፡ የሆኑ ፡ ስሜቶችንና ፡ ምሥጢሮችን ፡ የያዙ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ መንፈሳዊና ፡ ሥጋዊ ፡ ምክሮች ፡ ይገኛሉ

የባለ ፡ ቅኔዎቹ ፡ ስም ፡ በሙሉ ፡ ባይታወቅም ፡ ሲነገሩ ፡ የሚሰሙት ፡ ኅብረ ፡ ግጥሞች ፡ ከትንሽ ፡ እስከ ፡ ትልቅ ፡ ማለት ፡ ከተራ ፡ ሰው ፡ እስከ ፡ ንጉሥ ፡ ተካፋይ ፡ የሆኑባቸው ፡ ናቸው። እነዚህም ፡ እንደጊዜው ፡ ሁናቴ ፡ እና ፡ እንደስልቱ ፡ ዓይነት ፡ በበገና ፡ በመሰንቆና ፡ በክራር ፡ ድምፃውያን ፡ ተጫዋቾች ፡ ወይም ፡ ደራስያኑ ፡ ራሳቸው ፡ በአዜሟቸው ፡ ጊዜ ፡ የተለየ ፡ ስሜትና ፡ ጣዕም ፡ የሚሰጡ ፡ ናቸው። ስለዚህ ፡ ነው ፡ እኔ ፡ የሰበሰብኳቸውን ፡ ኅብር ፡ ግጥሞች ፡ የያዘውን ፡ መጽሐፍ ፡ «አማርኛ ፡ ቅኔ» ፡ ብዬ ፡ የሰየምኩት። ምክንያቱም ፡ እንደቅኔ ፡ ብዙ ፡ መንገዶችን ፡ የያዙ ፡ ባለኅብር ፡ ቃላት ፡ ወይም ፡ ሰምና ፡ ወርቅ ፡ በመሆናቸው ፡ ነው። «ሰም ፡ ብለን ፡ የምንገልጠው ፡ ደራሲው ፡ ሊናገረው ፡ የአሰበው ፡ ፍሬ ፡ ነገር ፡ የተሸፈነበትን ፡ የምሥጢሩን ፡ መጋረጃ ፡ ነው። «ወርቅ» ፡ የተባለው ፡ ደግሞ ፡ አንድን ፡ ቃል ፡ በማጥበቅ ፡ በማላላት ፡ ወይም ፡ አጠገቡ ፡ ካለው ፡ ከሌላው ፡ ጋር ፡ በማያያዝና ፡ በማናበብ ፡ በላንቃና ፡ በትናግ ፡ በድምፅና ፡ በንግግር ፡ የሚያጋጥመውን ፡ ስልት ፡ በመመርመር ፡ የሚገኘው ፡ ምሥጢር ፡ ወይም ፡ ፍሬ ፡ ነገር ፡ ነው።

ከእነዚህም ፡ አስደሳች ፡ ከሆኑ ፡ ኅብረ-ቃላት ፡ ውስጥ ፡ ከኃዘን ፡ የሚያጽናኑ ፡ ከብስጭት ፡ የሚመልሱ ፡ ትዕግሥትን ፡ የሚሰጡ ፡ የሰውን ፡ ግብዝነት ፡ የሚያስረዱና ፡ እነዚህን ፡ የመሳሰሉትን ፡ ሁሉ ፡ የሚገልጹ ፡ ሃሳቦች ፡ እናገኝባቸዋለን።

ከዚህም ፡ በቀር ፡ ማግኘት ፡ ማጣትን ፡ መከበር ፡ መዋረድን ፡ መሾም ፡ መሻርን ፡ መታመም ፡ መሞትን ፡ በጠቅላላው ፡ በዕድሜ ፡ ላይ ፡ እየተከታተሉ ፡ የሚደርሱትን ፡ ማናቸውንም ፡ ተለዋዋጭ ፡ የሆኑ ፡ ድርጊቶችን ፡ የያዙ ፡ መሆናቸውን ፡ መረዳት ፡ ይቻላል።

ምንም ፡ እንኳ ፡ የግጥሞቹ ፡ ስልትና ፡ ያነጋገሩ ፡ ሁናቴ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ መልክን ፡ የያዘ ፡ ቢሆንም ፡ ዋናው ፡ ዓላማ ፡ የሰውን ፡ ልቡና ፡ ከክፉ ፡ ኃሣብ ፡ ለመመለስና ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ መንገድ ፡ ለመምራት ፡ ስለሆነ ፡ በአማርኛ ፡ ቅኔ ፡ ውስጥ ፡ የሚገኙት ፡ ቃላት ፡ አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ ቅዱሳት ፡ መጻሕፍትን ፡ የተከተሉ ፡ ናቸው።

የምሥጢሩንም ፡ ርቀትና ፡ ጥልቀት ፡ ለመገንዘብ ፡ እንዲቻል ፡ ለምሳሌ ፡ ያህል ፡ ጥቂት ፡ ግጥሞችን ፡ እንጠቅሳለን።

## ከመዲና።

፩ ፡ ገድሎ ፡ ማዳኑን ፡ አየነው ፡
ለወልድ ፡ አብነት ፡ አለው። *ምሥጢረ ፡ ሥላሴ ፡*

**ሠ** ፡ ወልድ ፡ ከሞት ፡ አፋፍ ፡ የደረሰውን ፡ የሚያድን ፡ መድኃኒት ፡ አለው ፡

**ወ** ፡ እኔ ፡ በአብ ፡ አብም ፡ በኔ ፡ አለ ፡ ያለውን ፡ ያንድነት ፡ ቃል ፡ ያስረዳል።

፪ ፡ አረ ፡ እርዳኝ ፡ እባክህ ፡
አንተ ፡ ሰው ፡ በናትህ። *ምሥጢረ ፡ ሥጋዌ ፡*

**ሠ** ፡ በምትወዳት ፡ በምታፈቅራት ፡ እናትህ ፡ ብለህ ፡ እባክህ ፡ እርዳኝ ፡ አግዘኝ።

**ወ** ፡ እግዚአብሔር ፡ ወልድ ፡ ከእመቤታችን ፡ መወለዱንና ፡ ሰውም ፡ መሆኑን ፡ ለማስረዳት።

፫ ፡ የዛሬ ፡ ሳምንት ፡ ዓርብ ፡ ቀን ፡
ትልቅ ፡ ነጭ ፡ በግ ፡ አርደን ፡ *ምሥጢረ ፡ ቁርባን*
የታመሙ ፡ ሁሉ ፡ መላው ፡ ዳኑ ፡

በሥጋውና ፡ በደሙ።

***ሠ*** ፡ ነጭ ፡ በግ ፡ ለጭዳ ፡ አርደን ፡ ሥጋውን ፡ በልተው ፡ ደሙንም ፡ ጠጥተው ፡ የታመሙት ፡ ሁሉ ፡ ዳኑ።

***ወ*** ፡ ዓርብ ፡ ዕለት ፡ ተሰቅሎ ፡ ለሰው ፡ ዘር ፡ መድኃኒት ፡ የተሰጠውን ፡ ሥጋውንና ፡ ደሙን ፡ ተቀብለው ፡ ከነፍስ ፡ ሕመም ፡ ዳኑ።

፴ ፡ ዛሬ ፡ አላዝንብህም፡ ባታድለኝ ፡ ጠጅ ፡
ኋላ ፡ በትንሣኤ ፡ አትበድለኝ ፡ እንጅ። *ምሥጢረ ፡ ትንሣኤ ፡ ሙታን ፡*

***ሠ*** ፡ በፋሲካ ፡ እንዳትረሳኝ ፡ እንጂ ፡ ዛሬ ፡ በግብዣው ፡ ላይ ፡ መጠጥ ፡ ባትሰጠኝም ፡ አላዝንም ፡ አልቀየምም።

***ወ*** ፡ በትንሣኤ ፡ ሙታን ፡ ከወዳጆችህ ፡ ቆጥረህ ፡ ጽድቅን ፡ አድለኝ ፡ በግራ ፡ ኣታውለኝ።

፳ ፡ ትናንት ፡ ተኝተው ፡ ሌሊት ፡
አንቀዣበረኝ ፡ ያሉት ፡
ሀሰትም ፡ አይደል ፡ እውነት ፡
ይህ ፡ ሁሉ ፡ ያለሙት።

***ሠ*** ፡ ሕልምዎ ፡ እውነት ፡ ነው ፡ ቅዠት ፡
አይደለም ፡ ይደርሳል ፡ እርግጥ ፡ ይሆናል። *ስለሰው፡ ሟችነትና ፡ ከንቱነት ፡*

***ወ*** ፡ ይህ ፡ ሁሉ ፡ ቋሚ ፡ (ሕያው) ፡ ቀኑን ፡ የሚጠብቅ ፡ ሙት ፡ ነው ፡ የጊዜው ፡ ጊዜ ፡ ሁሉም ፡ ከሞት ፡ አይቀርም።

፺ ፡ የተቆጠረው፡ ምስክር ፡ ሰው ፡ በእግዚአብሔርና ፡ በእመቤታችን፡ስላለው፡ እምነት
ይንገር ፡ ካላችሁ ፡ ይንገር ፡
እኔ ፡ የማምናቸው ፡ ሁለቱን ፡
--እናትና ፡ ልጁን።

***ሠ*** ፡ እናትና ፡ ልጁን ፡ አምናቸዋለሁ ፡ ምስ
ክርነታቸውንም ፡ እቀበላለሁ።

***ወ*** ፡ ማርያምንና ፡ ጌታን ፡ አምናለሁ ፡ በሁለቱ ፡

ላይ ፡ ተስፋ ፡ አለኝ ፡ እነሱን ፡ ተማጥኛለሁ።

፺ ፡ የኔ ፡ ቤት ፡ እዚህ ፡ ሳለልሽ ፡ *በመቤታችን፡ ስለመማፀን*
ለምን ፡ ምድረ ፡ ግብፅ ፡ ወረድሽ ፡
ማልደሽ ፡ ይዘሽ ፡ ነይ ፡ ልጅሽን ፡
--ስሞት ፡ አደራሽን።

**ሠ** ፡ በኔ ፡ ሞት ፡ እንዳትቀሪብኝ፥ ልጅሽን ፡
ይዘሽ ፡ እንድትመጪ።

**ወ** ፡ በጊዜ ፡ ሞቴ ፡ እንዳትረሽኝ ፡ አደራሽን ፡
እንድታማልጅኝ።

፺፩ ፡ የጌታችንን ፡ ጠባይ ፡ *ቀን ፡ ሲጐድል ፡ ስለሚያስከትለው ፡ ችግር*
ያለእኔ ፡ የሚያውቀው ፡ አለ ፡ ወይ ፡
ማታ ፡ ለግብር ፡ መልካም ፡ ነው ፡
--ቀን ፡ ሲቀጣ ፡ ክፉ ፡ ነው።

**ሠ** ፡ ቀን ፡ ቀን ፡ ይቆጣል ፡ ሲመሽ ፡ ትዕግ
ሥተኛ ፡ ነው ፡ ማታ ፡ እንደ ፡ ቀን ፡
አያስፈራም።

**ወ** ፡ ዘመን ፡ ሲጣላ ፡ ጊዜ ፡ ሲጥል ፡ ክፉ ፡
ነው ፡ አያድርስ ፡ ነው።

፺፪ ፡ ይህ ፡ ሁሉ ፡ ድግስ ፡ ተደግሶ ፡
እንዳንሰደብ ፡ ዝግን ፡ አንሶ ፡ *ከሥጋ ፡ ይልቅ ፡ ለንፍስ ፡ ማሰብ ፡*
ነፍሴ ፡ ሥጋ ፡ አትሳሺ ፡ *የተገባ ፡ መሆኑን ስለማስገንዘብ ፡*
ገና ፡ ፍሪዳ ፡ አለልሺ።

**ሠ** ፡ ፍሪዳ ፡ ተዘጋጅቶልሻል ፡ ሥጋ ፡ አለልሽ ፡
ትበያለሽ ፡ ጮማ ፡ ትቆርጫለሽ።

**ወ** ፡ ሞት ፡ ኩነኔ ፡ አለብሽ ፡ ነፍሴ ፡ ፍሪ ፡
ለኋለኛው ፡ ዘመን ፡ አስቢ ፡ ዕለተ ፡
ሞትን ፡ ኣስታውሽ ፡ ዕዳ ፡ ኣለብሽ።

፲ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ልንገርህ ፡ *ሙገሳ ፡*
እንጀራ ፡ አባቴ ፡ ነህ ፡
ምን ፡ ጊዜም ፡ አትከፋ ፡
--አንተ ፡ ብልህ ፡ በይፋ።

**ሠ** ፡ በገሀድ ፡ አንተ ፡ ብዬ ፡ ብጠራህ ፡ ኣንቱ ፡
ሳልልህ ፡ ብቀር ፡ አትቆጣ ፡ አይከፋህ።

**ወ** ፡ ብልህ ፡ አስተዋይ ፡ ነህ ፡ አርቆ ፡ መመል
ከት ፡ ትችላለህ።

፲፩ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ በፈረስ ፡ *መልካም ፡ ምኞት ፡*
ብከተልህም ፡ አልደርስ ፡
አንተ ፡ ቁምልኝ ፡ እባክህ ፡
--በሞቴ ፡ ልቀደምህ።

**ሠ** ፡ እባክህ ፡ እፈት ፡ እፈትህ ፡ ቀድሜህ ፡
ልሂድ ፡ ወደኋላ ፡ አልቅር።

**ወ** ፡ በሞቴ ፡ ልቅደምህ ፡ ከአንተ ፡ በፊት ፡
እኔ ፡ ልሙት ፡ ሞትህን ፡ አያሳየኝ።

፲፪ ፡ ረኀዝም ፡ አይደል ፡ አጭር ፡ *ረኃብ ፡ ስለሚያመጣው ፡ ውርደት ፡*
ወፍራም ፡ አይደል ፡ ቀጭን ፡
ታግሎ ፡ የጣለኝ ፡ ከሰው ፡ ደጅ ፡
--እኔን ፡ ያህል ፡ ነው ፡ እንጅ።

**ሠ** ፡ ከእኔ ፡ የማይበልጥ ፡ የአካል ፡ ግዝፈት ፡
የሌለው ፡ አጭር ፡ ቀጭን ፡ ሲሆን ፡ ታግሎ ፡
ጣለኝ ፡ እኩያዬ ፡ የሆነ ፡ ሰው ፡ አሸነፈኝ።

**ወ** ፡ እኔን ፡ ያደከመኝና ፡ ያብረከረከኝ ፡ ረኃብ ፡
ነው ፡ የትም ፡ ወድቄ ፡ የቀረሁት ፡ ችጋር ፡ ጠን
ቶብኝ ፡ የምበላው ፡ እኽል ፡ አጥቼ ፡ ነው።

፲፫ ፡ የተመተረውን ፡ ለዝግን ፡ *የሥጋና ፡ የነፍስ ፡ ሥራ ፡ በአንድነት*

ማን ፡ አፈሰሰው ፡ ይሆን ፡ *ሊመራ ፡ ስለአለመቻሉ ፡*
አፍሰን ፡ በሰፌድ ፡ እፍ ፡ አንልም ፡
--ሥጋና ፡ ነፍስ ፡ አይሆንም።

**ሠ ፡** ሥጋን ፡ ማንፈስ ፡ ማበጠር ፡ ከአፈር ፡
መለየት ፡ አይቻልም ፡ ችግር ፡ ነው።

**ወ ፡** የሥጋና ፡ የነፍስ ፡ ሥራ ፡ ለየብቻው ፡
ነው ፡ ሁሉንም ፡ በየመልኩ ፡ መያዝ ፡ ያስፈልጋል።

## ከዘለሰኛ።

፲፬ ፡ መስፍን ፡ የመስፍን ፡ ልብስ ፡ መልበስ ፡ ሲገባው ፡ *ውለታን፡ ስለማስታወስ ፡*
--ትንሽ ፡ መጠቃቀም ፡ ነበረ ፡ ሥራው።

**ሠ ፡** ሥራው ፡ ጨርቃ ፡ ጨርቁን ፡ መስፋት ፡
መጠቃቀም ፡ ነበር።

**ወ ፡** ልዑል ፡ መኰንን ፡ የተቸገረ ፡ መርዳት ፡
የአዘነ ፡ ማረጋጋት ፡ የሚወድ ፡ ትልቅ ፡ ትንሹን ፡ ደጋፊ ፡ ነበር።

፲፭ ፡ ቆመህ ፡ ስትሟገት ፡ ዳኛው ፡ አያደላ ፡ *ጸጸትና ፡ ኃዘን*
—ባፋረዱህ ፡ እንጂ ፡ አትህ ፡ ምን ፡ ልበላ።

**ሠ ፡** ፍርድ ፡ በአዩልህ ፡ በመረመሩልህ ፡ ነበር ፡
እንጂ ፡ ፍርድ ፡ ከአዛቡብህ ፡ እኔ ፡ ምን ፡
ላድርግህ? ምን ፡ ልረዳህ ፡ እችላለሁ?
እግዚአብሔር ፡ ይየው ፡ እንጂ።

**ወ ፡** ፩ በአፉ ፡ አረዱህ ፡ ከለሉህ።
፪/ በአፍ ፡ አረዱህ ፡ ሸነገሉህ (ደለሉህ) አታለሉህ።

፲፮ ፡ ባልቆም ፡ ይሻለኛል ፡ ብሄድ ፡ ቶሎ ፡ ቶሎ ፡
-ያ ፡ የተማመንኩት ፡ ከጠፋብኝ ፡ በቅሎ። *መቆጨት፡መበሳጨት ፡ ማዘን ፣መተከዝ ፡*

**ሠ ፡** ልጭነው ፡ ያሰብሁት ፡ በቅሎ ፡
ከጠፋብኝ ፡ በጊዜ ፡ ላዝግም።

**ወ ፡** ይጦረኛል ፡ ይቀብረኛል ፡ ብዬ ፡ የተማመንኩ
ትና ፡ የተመካሁበት ፡ ልጄ ፡ እንዲህ ፡ ሆኖ ፡
ከተለየኝ ፡ ባልቆም ፡ ይሻለኛል።

<u>፲፯ ፡</u> ወገራ ፡ አሳላፊ ፡ ደንቢያ ፡ እንጀራ ፡ ጣይ ፡
–ተበላህ ፡ ጐንደሬ ፡ አትነሳም: ወይ። *ጦር ፡ ስለማስታወቅ ፡*

**ሠ** ፡ ምግብ ፡ ከተመገብህ ፡ በኋላ ፡ መነሳት ፡ አትችልምን? ።

**ወ ፡** የጎንደር ፡ ሕዝብ ፡ ጠላት ፡ ሊይዝህ ፡ ነው።
ተነስተህ ፡ እጅህን ፡ አውጣ ፡ አምረህ ፡ ሽሽ።

<u>፲፰ ፡</u> የራስ ፡ ዓሊማ ፡ ናት ፡ እጅግ ፡ ረዘመ ፡
– ላየውም ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ በጣም ፡ አስገረመ። *አግኝቶ ፡ በማጣት፡ መገረም*

**ሠ ፡** የራስ ፡ ዓሊ ፡ ጣት ፡ እጅግ ፡ ረዥም ፡ ነው ፡
አለንጋ ፡ ይመስላል።

**ወ ፡** እጅግ ፡ አድርገው ፡ አስደስተው ፡ የሚያበ
ሉት ፡ የሚያጠጡት ፡ ራስ ፡ ዓሊ ፡ እስከማ
ጣት ፡ መድረሳቸው ፡ በጣም ፡ አስገረመ።

<u>፲፱ ፡</u> ዘውዴ ፡ ለጐጃሞች ፡ ሲደግሥላቸው ፡
ከቤትም: አይደለ ፡ ከሜዳ ፡ ሰጣቸው። *የጀብዱ ፡ ሥራ ፡ ስለመግለጥ ፡*

**ሠ** ፡ ዘውዴ ፡ ለጎጃሞች ፡ ያዘጋጀውን ፡ ግብዣ ፡
ከሜዳ ፡ ላይ ፡ አበላቸው ፡ እዱር ፡ ጋበዛቸው።

**ወ ፡** ዘውዴ ፡ ጎጃሞችን ፡ ጨፈጭፋቸው ፡ ረብር
ቧቸው ፡ አመለጠ ፡ ገድሎ ፡ ከሜዳ ፡ ላይ ፡ አንጥፋቸው ፡ ሄደ።

<u>፳ ፡</u> የዱሮ ፡ መድሃኒት ፡ ኮሶ ፡ ምን ፡ አላችሁ ፡
ምንም ፡ አያስቀምጥ ፡ ይኸስ ፡ ቀጨሟችሁ። *አለማስተዋልንና ፡ ጨካኝነትን ፡ ስለመንቀፍ ፡*

***ሠ*** ፡ የቀጨሞ ፡ ፍሬ ፡ እንደኮሶ ፡ ሆድን ፡ አያጠራም ፡
ተቅማጥ ፡ የለውም ፡ ደስ ፡ አያሰኝም።

***ወ*** ፡ የቀጨሞ ፡ አርጩሜ ፡ ትዕግሥት ፡ ያስጨርሳል ፡
አያስቀምጥም ፡ በለበቅ ፡ የሚቆነድዱ ፡ ከልካዮች ፡
እያሉ ፡ ወደ ፡ ግብር ፡ መግባት ፡ አይቻልም።

፳፩ ፡ አፈር ፡ መልሱ ፡ እንጂ ፡ ድንጋይ ፡ ለምናችሁ ፡
-የቀለም ፡ ቀንድ ፡ ነው ፡ ትሰብሩታላችሁ።

*ብዙ ፡ በተማረና ፡ በዐዋቂ ፡ ሰው ፡ ምት ፡ ስለመጻጻት ፡*

***ሠ*** ፡ የቀለም ፡ መበጥበጫውን ፡ ቀንድ ፡ እን
ዳትሰብሩት ፡ ተጠንቀቁ።

***ወ*** ፡ ድንጋዩንና ፡ አፈሩን ፡ ዝግ ፡ ብላችሁ ፡
መልሱ ፡ የዕውቀት ፡ ምንጭ ፡ የነበረው ፡
የሊቁን ፡ አስከሬን ፡ ትጎዱታላችሁ።

፳፪ ፡ ቢነግሩሽ ፡ አትሰሚ ፡ ቢጠቅሱሽ ፡ አታዩ ፡
–ዝግ ፡ ብለሽ ፡ ሂጂ ፡ ብር ፡ ብር ፡ አትበዪ።

*ያለማስተዋልንና ፡ ገንዘብ ፡ ብቻ ፡ መውደድን ፡ ስለመንቀፍ ፡ ተግሣፅ ፡*

***ሠ*** ፡ ቢጠሩሽ ፡ ምልክት ፡ ቢያደርጉልሽ ፡
አታስተውይም ፡ እንደ ፡ ልጅ ፡ ትሮጫለሽ ፡ ትቸኩያለሽ።

***ወ*** ፡ በምታደርጊውና ፡ በምትሠሪው ፡ ሁሉ ፡ ማስተዋልን ፡
ጨምሪበት ፡ ለገንዘብ ፡ ብለሽ ፡ አትቅበዝበዢ ፡
ለብር ፡ ብለሽ ፡ ጤናሽን ፡ አታበላሺ።

፳፫ ፡ ያን ፡ የነገርኩሽን ፡ የተውሽው ፡ እንደሆን ፡
አንቺም ፡ ዘውድ ፡ አይደለሽ ፡ እኔም ፡ አክሊል ፡ አልሆን።

*ተነግሮ ፡ የነበረውን ፡ ትንቢት ፡* ስለማስታወስ ፡

***ሠ*** ፡ የተነጋገርነው ፡ ቃል ፡ ከተዘነጋ ፡ በእውነቱ ፡ ቁም ፡ ነገረኞች ፡
አንባልም ፡ የአቺም ፡ ዘውዲቱነት ፡ የእኔም ፡

አክሊሉነት ፡ ከንቱ ፡ ነው።

***ወ*** ፡ የለመንኩሽን ፡ ሹመት ፡ የማትፈጽሚልኝ ፡
ከሆንሽ ፡ ንግሥትነትሽ ፡ ለመቼ ፡ ነው።

፳፬ ፡ አስቲ ፡ ጠይቁልኝ ፡ ርቃ ፡ ሳትሄድ ፡
–እቴጌ ፡ ተዋበች ፡ ሚስት ፡ ናት ፡ ገረድ። *ውለታን፡ስለማስታወስ*

***ሠ*** ፡ ሚስት ወይስ ፡ ገረድ ፡ መሆኗን ፡ ርቃ ፡ ሳትሄድ ፡
አረጋግጣችሁ ፡ ጠይቁልኝ።

***ወ*** ፡ እትም ፡ እናትም ፡ ገረድም ፡ ነበረች ፡ በአዛኝነቷ ፡ እንደ ፡
እናት ፡ በአገልግሎቷ ፡ እንደ ፡ ገረድ ፡ ትጠብቀኝ ፡ ነበር።

## ፫. ተረት

ተረት ፡ እንደ ፡ ጉዳዩ ፡ ሁናቴ ፡ በሰውና ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ እንስሳት ፡ እየተመሰለ ፡ የሚነገር ፡ ልብ ፡ ወለድ ፡ ታሪክ ፡ ነው። ይህም ፡ እጅግ ፡ አድርጎ ፡ ደስ ፡ በማሰኘቱ ፡ በመኝታ ፡ ጊዜ ፡ ሕጻናትን ፡ እንቅልፍ ፡ ይከለክላቸዋል ፡ እኔም ፡ ይህንኑ ፡ በመመልከት ፡ ስለተረት ፡ የጻፍኩትን ፡ መጽሐፍ ፡ «እንቅልፍ ፡ ለምኔ» ፡ ብዬ ፡ ሰይሜዋለሁ።

ተረት ፡ አነጋገሩ ፡ እንደቧልት ፡ ዓይነት ፡ ሆኖ ፡ የሚያስቅ ፡ የሚያስለቅስ ፡ የሚያስገርምና ፡ የሚያስደንቅ ፡ ቢሆንም ፡ መነሻና ፡ መድረሻ ፡ ያለው ፡ ሙሉ ፡ ታሪክን ፡ የያዘ ፡ ነው። ከውስጡም ፡ ትምሕርት ፡ የሚሆን ፡ ጠቃሚ ፡ ተግሣጽና ፡ ምክር ፡ ይገኝበታል። የሀገራችን ፡ ሽማግሎችና ፡ ባልቴቶች ፡ ማታ ፡ ማታ ፡ ለሕፃናት ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ የሆኑ ፡ ተረቶችን ፡ ማሰማት ፡ ልማዳቸው ፡ ነው ፡ እንዲያውም ፡ ሕፃናትን ፡ ወደ ፡ ሽማግሎች ፡ ከሚያቀርቧቸው ፡ ከሚስቧቸው ፡ እንዲሁም ፡ ከሚያላምዷቸው ፡ ነገሮች ፡ ውስጥ ፡ ዋናዎቹ ፡ እነዚህ ፡ ናቸው ፡ ለማለት ፡ ይቻላል።

ተረቶች ፡ ሕፃናትን ፡ የማር ፡ የወተትና ፡ የስኳር ፡ ያህል ፡ ስለሚያረኳቸው ፡ በሚነገርበት ፡ ወቅት ፡ ከሥር ፡ ጀምረው ፡ በፈገግታና ፡ በደስታ ፡ ያዳምጧቸዋል።

ለልጆች ፡ ደግነትን ፡ ርኅሩኅነትንና ፡ ታዛዥነትን ፡ ለማስተማር ፡ ተግሣፅ

፡ ለማድረግና ፡ ጠቃሚ ፡ ምክሮችን ፡ ለመስጠት ፡ በአጭሩ ፡ ግብረ ፡ ገብነትን ፡ ለማስለመድ ፡ ተፈላጊነት ፡ ያላቸው ፡ ናቸው። እስካሁን ፡ ተረቶችን በቃል ፡ በመቀባበል ፡ እንጂ ፡ እምብዛም ፡ በመጽሐፍ ፡ መልክ ፡ ተዘጋጅተው ፡ አናገኛቸውም። ስለዚህ ፡ አነጋገሩ ፡ እንደየከፍለ ፡ ሀገሩ ፡ ሊለዋወጥ ፡ ይችላል ፡ ቢሆንም ፡ ፍሬ ፡ ነገሩ ፡ ምን ፡ እንደሆነ ፡ ከታወቀ ፡ በኋላ ፡ ሥዕሉን ፡ አስተካክሎ ፡ መሥራት ፡ የተመራማሪው ፡ ፋንታ ፡ መሆን ፡ አለበት ፡ በእኔ ፡ አስተያየት ፡ እነዚህን ፡ እያጠራቀሙ ፡ ለሕጻናት ፡ አእምሮ ፡ ማጎልመሻ ፡ እንዲሆኑ ፡ በትምሕርትገበታ ፡ ላይ ፡ ማቅረብ ፡ አስፈላጊ ፡ ነው። ለሞራል ፡ ወይም ፡ ለግብረ ፡ ገብነት ፡ ትምህርት ፡ ተቃራኒ ፡ የሚሆኑትን ፡ ግን ፡ እየመረመሩ ፡ ማስቀረት ፡ የጸሐፊው ፡ ድርሻ ፡ እንዲሆን ፡ ያሻል። ከተረቶች ፡ መካከል ፡ ለምሳሌ ፡ ያህል ፡ ሁለቱን ፡ ቀጥዬ ፡ ጽፌአለሁና ፡ የሚሰጡት ትምሕርት ፡ ምን ፡ እንደሆነ ፡ እንረዳው።

## ሀ ፡ ያውሬ ፡ ሁሉ ፡ ገበያ።

የምድር ፡ አውሬ ፡ ሁሉ ፡ መሰብሰቢያና ፡ መናገጃ ፡ አንድ ፡ ገበያ ፡ ነበር ፡ ይባላል። ከዕለታት ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ አውሬ ፡ ሁሉ ፡ እገበያ ፡ ሲውል ፡ አያ ፡ ኸርቦ ፡ ግን ፡ ሳይሄድ ፡ ቀረ። የማታ ፡ ማታ ፡ ገበያተኛ ፡ ሲመለስ ፡ ከጎሬው ፡ ወጣና ፡ ከመንገድ ፡ ዳር ፡ ተቀመጠ። ገበያ ፡ ምላሽ ፡ ሲሆን ፡ እንኮዬ ፡ ዝንጀሮ ፡ ኮተቷን ፡ በዠርባዋ ፡ አዝላ ፡ መጣች። አያ ፡ ኸርቦም ፡ እንኮዬ ፡ ዝንጀሮ ፡ እንደምን ፡ ዋልሽ ፡ ገበያውስ ፡ እንዴት ፡ ዋለ ፡ ምን ፡ ረከሷል ፡ ምንስ ፡ ተወዷል? ብሎ ፡ ጠየቃት። ወንድሜ ፡ እኔ ፡ መሽቶብኛል ፡ እቤት ገብቼ ፡ ገና ፡ ራቴን ፡ እጋግራለሁ ፡ እንኮዬ ፡ ጦጢት ፡ እኋላ ፡ አለችልህ ፡ እሷን ፡ ጠይቃት ፡ ብላው ፡ ሄደች።

እንኮዬ ፡ ጦጢትም ፡ ወዲያው ፡ ስለ ፡ መጣች ፡ ገበያው ፡ እንደምን ፡ ዋለ?' አላት። እባክህ ፡ አያ ፡ ኸርቦ ፡ እኔ ፡ መሽቶብኛል ፡ ገና ፡ እቤቴ ፡ ገብቼ ፡ ወደ ፡ ውሃ ፡ እወርዳለሁ ፡ እንኮዬ ፡ ሚዳቋ ፡ ከኋላ ፡ አለችልህ ፡ እሷን ፡ ጠይቃት ፡ ብላው ፡ አለፈች።

ሦስተኛ ፡ ሚዳቋ ፡ ቅራቅንቦዋን ፡ አዝላ ፡ በዚሁ ፡ ኣያ ፡ ኸርቦ ፡ በአለበት ፡ መንገድ ፡ መጣች ፡ አያ ፡ ኸርቦም ፡ ሚዳቋ ፡ እባክሽ ፡ ገበያው ፡ እንደምን ፡ ዋለ?'' አላት ፡ እንኮዬ ፡ አህዪት ፡ እኋላ ፡ አለችልህ ፡ እሷን 'ጠይቅ ፡ እኔ ፡

እነእንኮዬ ፡ ዝንጀሮ ፡ ስላመለጡኝ ፡ እቸኩላለሁ ፡ ብላው ፡ ሄደች።

ከዚህ በኋላ ፡ አህዪት ፡ ከኋላ ፡ ስትንቀረደድ ፡ መጣች። አህዪት ፡ ዛሬ ፡ ገበያ ፡ እንዴት ፡ ዋለ ፡ ምንስ ፡ ርካሽ ፡ ነው? ምንስ ፡ ውድ ፡ ሆነ? ፡ አላት። እባክህ ፡ አያ ፡ ዥቦ ፡ ደክሞኛል ፡ እስቲ ፡ አረፍ ፡ ብዬ ፡ ላውራልህ ፡ ይህ ፡ በዚህ ፡ ያኸል ፡ ይህ ፡ በዚህ ፡ ያኸል ፡ ሲገዛ ፡ ዋለ ፡ እያለች ፡ ስታወራለት ፡ አህዪት ፡ ኧረ ፡ ከሆነስ ፡ ሆነና ፡ እኔ ፡ የምዘለውን ፡ ለመዝለል ፡ ትችያለሽ? ፡ አላት ፡ ኧረ ፡ ንሺ ፡ እቴ ፡ አሳምሬ ፡ አለችው ፡ እሱም ፡ የሞት ፡ ሞቱን እንጣጥ ፡ ብሎ ፡ ተሻግሮ ፡ እሷን ፡ ደግሞ ፡ በዪ' እስቲ ፡ ዝለዪ ፡ አላት። እንጣጥ ፡ ስትል ፡ ወረደችና ፡ እፈፋ ፡ ውስጥ ፡ ውትፍ ፡ ብላ ፡ ቀረች። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ አያ ፡ ዥቦ ፡ ሆዬ ፡ ወርዶ ፡ ሆዷን ፡ ዘርግፎ ፡ ሲበላ ፡ እንኮዬ ፡ ውሽት ፡ እኋላ ፡ ነበረችና ፡ ደም ፡ ደም ፡ ሲሸታት ፡ ጊዜ ፡ አፋፍ ፡ ብቅ ፡ ብላ ፡ ብትመለከት ፡ አህዪትን ፡ ጥሎ ፡ ሲበላ ፡ አየችው። አበላሉም ፡ ስለ ፡ አስጎመዠት ፡ ለሐጪ ፡ ወርዶ ፡ ከራሱ ፡ ላይ ፡ ጠብ ፡ ኣለበት። ቀና ፡ ብሎ ፡ ቢያይ ፡ ውሽት ፡ ከበላዩ ፡ ቆማለች። በዪ ፡ እኮ ፡ ነይ ፡ ውረጂና ፡ እየመተርሽ ፡ አብሊኝ ፡ አላት ፡ እሷም ፡ እሺ ፡ ጌታዬ ፡ ብላ ፡ ወረደችና ፡ እየመተረች ፡ ስታበላው ፡ ቆይታ ፡ በመከካሉ ፡ ወደ ፡ ኋላው ፡ ዘወር ፡ ባለላት ፡ ሰዓት ፡ የአህዪትን ፡ ልብ ፡ ስልቅጥ ፡ አደረገችው ፡ መለስ ፡ አለና ፡ ቢያይ ፡ ልቧን ፡ አጣው ፡ ውሽት ፡ ልቧ ፡ ወዴት ፡ ሄደ? ብሎ ፡ ጠየቃት። ልብ ፡ ባይኖራት ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ልብማ ፡ ከአላት ፡ አንተ ፡ ዘንድ ፡ መጥታ ፡ መቼ ፡ ትቀመጥ ፡ ነበር ፡ ኣለችው። እሱም ፡ በፊት ፡ አይቶታልና ፡ ታመጪ ፡ እንደሆነ ፡ አምጭ ፡ አለዚያ ፡ አንቺንም ፡ እበላሻለሁ ፡ አላት። ምነው ፡ አያ ፡ ዥቦ ፡ እኔን ፡ በቅቤና ፡ በድልህ ፡ አጣፍጠህ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ እንደ ፡ አህዪት ፡ ደረቁን ፡ ትበላኛለህ? አለችው። ሆዳሜ ፡ እውነት ፡ መሰለውና ፡ ቅቤውና ፡ ድልሁ ፡ ከየት ፡ ይመጣል? አላት። ከመቤቴና ፡ ከጌታዬ ፡ ቤት ፡ እኔ ፡ ሄጄ ፡ አመጣዋለኋ ፡ ስትል ፡ መለሰችለት።

- ሄደሽ ፡ የጠፋሽ ፡ እንደሆነ ፡ ማ ፡ ብዬ ፡ እጠራሻለሁ?

- እንኮዬ ፡ ልብ ፡ አጥቼ ፡

በይ ፡ እንግዲያውስ ፡ ሄደሽ ፡ አምጭ ፡ አላትና ፡ እሺ ፡ ብላ ፡ ሜዳ ፡ ቅርት ፡ ብትል ነ«ኧረ ፡ እንኮዬ ፡ ልብ ፡ አጥቼ» ፡ እያለ ፡ ተጣራ። ከመቤቴና

፡ ከጌታዬ ፡ ቤት ፡ ለምን ፡ ወጣቹ ፡ በማለት ፡ የስድብ ፡ ጎርፍ ፡ ታወርድበት ፡ ጀመር። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ተናደደና ፡ አንቺም ፡ እጉድፍ ፡ እኔም ፡ እጉድፍ ፡ እንገናኝ ፡ የለምን ፡ ብሎ ፡ ዝቶ ፡ ተመለሰ።

ጥቂት ፡ ጊዜ ፡ ከአለፈ ፡ በኋላ ፡ የውሻ ፡ ነገር ፡ መለቃቀም ፡ ትወዳለችና ፡ ስትልከሰከስ ፡ ሳይገባ ፡ የቀረ ፡ ከብት ፡ ወይም ፡ ምናምን ፡ ነገር ፡ ቢያጋጥመኝ ፡ ብሎ ፡ ሲሄድ ፡ አያ ፡ ዥቦ ፡ እጉድፍ ፡ አገኛት። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ደነገጠችና ፡ ዐይኗ ፡ ፈጠጠ። እሱም ፡ ውሸት ፡ ኧረ ፡ ዐይንሽ ፡ በምን ፡ እንደዚህ ፡ አማረልሽ? አላት። ጌታዬ ፡ በዐሥር ፡ የኢጋም ፡ እሾክ ፡ ተነቅሼ ፡ ነዋ ፡ አለችው። እስቲ ፡ እባክሽን ፡ እንደዚህ ፡ ከአማረ ፡ እኔንም ፡ ንቀሽኝ ፡ ብሎ ፡ ጠየቃት። እሷም ፡ ከጌታዋ ፡ አጥር ፡ ላይ ፡ ዐሥሩን ፡ የኢጋም ፡ እሾኽ ፡ ሰብራ ፡ አንድ ፡ ላይ ፡ አሥራ ፡ አመጣችና ፡ ሁለቱንም ፡ ዐይኖቹን ፡ ትቸከችካቸው ፡ ጀመር። እንኮዬ ፡ ውሸት ፡ ኧረ ፡ እባክሽ ፡ አመመኝ ፡ አላት። ተው ፡ ዝምበል ፡ ሲያጌጡ ይመላለጡ ፡ ነው ፡ ማማር ፡ እንዲያው ፡ ይገኝ ፡ ይመስልሀል? ብላ ፡ ሁለቱንም ፡ ዓይኖቹን ፡ አጠፋቻቸው። በመጨረሻውም ፡ እንግዲህ ፡ ዝም ፡ ብለህ ፡ ከዚህ ፡ ቆየኝ ፡ አለችው ፡ እሱም ፡ እሺ ፡ ብሎ ፡ ከአሳየችው ፡ ቦታ ፡ ተቀምጦ ፡ ሳለ ፡ ጤፍ ፡ ወቂዎች ፡ ሆ ፡ ሆ ፡ ሲሉ ፡ ሰማ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ እንኮዬ ፡ ውሸትን ፡ ኧረ ፡ ይኸ ፡ የምሰማው ፡ ሆታ ፡ ምንድነው? እባክሽ ፡ አለና ፡ ጠየቃት ፡ ወንድሜ ፡ ዘመዶችህ ፡ ሡንጋ ፡ ጥለው ፡ በጎድን ፡ ከዳቢት ፡ ይማታሏ ፡ አለችው። እንግዲያው ፡ እባክሽ ፡ እኔንም ፡ አድርሺኝ ፡ አላትና ፡ እየመራች ፡ ወስዳ ፡ ከጤፍ ፡ ወቂዎች ፡ መካከል ፡ አገባችው ፡ ጤፍ ፡ ወቂዎቹም ፡ ይህ ፡ ዥብ ፡ ከወዴት ፡ መጣ ፡ እያሉ ፡ መውቂያ ፡ ሙጫቸውን ፡ እየመዘዙ ፡ ዥቡን ፡ ለመግደል ፡ ሲሯሯጡ ፡ እሷ ፡ የገበሬዎቹን ፡ ዳቦ ፡ ይዛ ፡ ወደ ፡ ቤቷ ፡ ተመለሰች ፡ ይባላል።

የታሪኩ ፡ ፍሬ ፡ ነገር ፡

- ያሰቡትንና ፡ ያቀዱትን ፡ ቸል ፡ ሳይሉና ፡ ሳይታለሉ ፡ ከፍጻሜ ፡ ማድረስ ፡ የአስተዋይ ፡ ተግባር ፡ ነው።
- እኩያ ፡ ያልሆነ ፡ ጓደኛ ፡ መያዝ ፡ ነገርን ፡ ሳያመዛዝኑና ፡ ሳያሰላስሉ ፡ ፈጥኖ ፡ ማመንና ፡ መቀበል ፡ የሚያስከትለውንም ፡ ኣለማሰብ ፡ ከየዋህነትና ፡ ከቂልነት ፡ አስቆጥሮ ፡ ከጥቃት ፡ ያደርሳል።

- አታላይ ፡ ለጊዜው ፡ በመብለጥለጥ ፡ ምኞቱን ፡ ቢያረካም ፡ የፈጸመው ፡ ደባ ፡ እንደሚደርስበት ፡ የዥቡን ፡ አወዳደቅ ፡ መመልከት ፡ ይበቃል ፡
- ከእንስሳትም ፡ ውስጥ ፡ በአስተዋይነታቸውና ፡ በብልህነታቸው ፡ የሚመሰገኑ ፡ ፍጥረታት ፡ ይገኛሉ ፡ እነሆ ፡ ውሻዪቱ ፡ በዘዴ ፡ ከአደጋ ፡ ከአመለጠች ፡ በኋላ ፡ ኃይለኛ ፡ የሆነ ፡ ጠላቷን ፡ አሞኝታ ፡ ከሞት ፡ አደጋ ፡ አድርሳዋለች።

ምክር ፡ ከአታላይ ፡ ወጥመድ ፡ ለመዳን ፡ መጠንቀቅ ፡ እንጂ ፡ እንደ ፡ ኣህያ ፡ ዝንጉና ፡ የዋህ ፡ መሆን ፡ ኣይገባም ፡ እንደ ፡ ውሻዪቱ ፡ በትዕግሥትና ፡ በዘዴ ፡ ከፈተና ፡ ለማምለጥ ፡ መጣጣር ፡ ተገቢ ፡ እርምጃ ፡ መሆኑንም ፡ መገንዘብ ፡ ያሻል።

## ለ ፡ ስለ ፡ አንዲት ፡ የቆቅ ፡ ልጅ ፡ በወጥመድ ፡ መያዝ።

አንዲት ፡ የቆቅ ፡ ልጅ ፡ የስንዴ ፡ እሸት ፡ ትርክክ ፡ ብሎ ፡ በስሎ ፡ በሚገኝበት ፡ እርሻ ፡ አጠገብ ፡ ወጥመድ ፡ ተጠምዶ ፡ አይታ ፡ እናቷን ፡ እናቴ ፡ ሆይ ፡ እሸት ፡ አምሮኝ ፡ ነበር ፡ ከዚህ ፡ ማሳ ፡ ገብቼ ፡ እንዳልበላ ፡ ወጥመድ ፡ እንዳይዘኝ ፡ ሰጋሁ ፡ ምን ፡ ይሻለኛል? አለቻት።

እናቷም ፡ ተዪ ፡ ልጄ ፡ ይቅርብሽ ፡ ትያዣለሽ ፡ አይሆንም ፡ ብላ ፡ መከረቻት። ልጅቷ ፡ ግን ፡ ግድየለሽም ፡ አይዘኝም ፡ ትንሽ ፡ ተከ ፡ ተከ ፡ አድርጌ ፡ ልውጣ ፡ አለችና ፡ ገብታ ፡ ስትበላ ፡ ያ ፡ ወጥመድ ፡ እናቷ ፡ እንደፈራችው ፡ እግሯን ፡ ጥርቅም ፡ አድርጎ ፡ ያዛት።

መቼም ፡ መከራ ፡ በመጣ ፡ ጊዜ ፡ በመጀመሪያ ፡ የሚታሰቡት ፡ ወላጆች ፡ ስለሆኑ ፡ ያች ፡ የናቷን ፡ ምክር ፡ አልሰማ ፡ ያለች ፡ ልጅ ፡ እናቴ ፡ ኧረ ፡ ተያዝኩልሽ ፡ አለቻት። እሷም ፡ ምነው ፡ ልጄ ፡ ኣስቀድሜ ፡ ነግሬሽ ፡ አልነበረምን ፡ አሁን ፡ ታዲያ ፡ ምን ፡ ላደርግልሽ ፡ እችላለሁ? ስትል ፡ መለሰችላት።

- እማምዬ ፡ እባክሽን ፡ ፍቺልኝ ፡
- በምን ፡ እጄ?
- ታዲያ ፡ እንዴት ፡ ልሁን ፡ ምን ፡ ይበጀኝ? የኔ ፡ እናት፡

በዚህ ፡ ጊዜ ፡ እናት ፡ ለልጅዋ ፡ ምን ፡ ጊዜም ፡ ምክር ፡ ዐዋቂ ፡ ናትና ፡ ዝም ፡ ብለሽ ፡ የሞትሽ ፡ መስለሽ ፡ ተኚ ፡ ባለወጥመዱ ፡ ሲመጣ ፡ ሞታለች ፡ ብሎ ፡ ፈትቶ ፡ ይለቅሻል ፡ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ ታመልጫለሽ ፡ አለቻት።

ያ ፡ ባለወጥመዱ ፡ ሰው ፡ ሰብሉን ፡ ኀብኝቶ ፡ መጣና ፡ ቢመለከት ፡ ዝልፍልፍ ፡ ብላ ፡ ተኝታ ፡ ዐይኗን ፡ አጨልማ ፡ አገኛት። እሱም ፡ የሞተች ፡ መሰለውና ፡ አዬ ፡ ጉድ ፡ ወጥመዴ ፡ ቆቅ ፡ ይዞልኝ ፡ ነበረ ፡ ነገር ፡ ግን ፡ በክታለች ፡ እያለ ፡ አዘነ።

ጓደኛው ፡ ከበላዩ ፡ ሰብል ፡ ይጠብቅ ፡ ነበርና ፡ ወንድም ፡ ብሎ ፡ ተጣርቶ ፡ ወጥመዴ ፡ ቆቅ ፡ ይዞልኝ ፡ ነበር ፡ ነገር ፡ ግን ፡ በክታ ፡ አገኘኋት ፡ አለና ፡ ነገረው። ባልንጀራውም ፡ እስቲ ፡ ወደ ፡ ላይ ፡ አጉናት ፡ አለው ፡ እሱም ፡ እያት ፡ አለና ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ ወርወር ፡ ቢያደርጋት ፡ ቱር ፡ ብላ ፡ ከጫካው ፡ ጥልቅ ፡ አለች ፡ ይባላል።

ምክር ፡ ያባቶችንና ፡ የእናቶችን ፡ እንዲሁም ፡ የሽማግሎችን ፡ ምክር ፡ መቀበልና ፡ ማክበር ፡ ይገባል። ከፈቃድ ፡ መውጣት ፡ ግን ፡ ከኣደጋ ፡ ላይ ፡ ስለሚጥል ፡ በምንሠራው ፡ ሁሉ ፡ ብርቱ ፡ ጥንቃቄ ፡ ማድረግ ፡ ጠቃሚያችን ፡ መሆኑን እንወቅ።

## ፬ ፡ ቧልት።

እንደ ፡ አሽሙር ፡ አግቦ ፡ ሽሙጥ ፡ ፌዝ ፡ ሾርኔ ፡ ተረብ ፡ ቀልድና ፡ ዋዛ ፡ የመሳሰሉት ፡ ሁሉ ፡ ቧልት ፡ ይባላሉ። እነዚህም ፡ በንግግር ፡ በሰላምታና ፡ በጨዋታ ፡ ሰዓት ፡ በአንድ ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ ሲሰነዘሩ ፡ እንደፍላጻ ፡ ልብን ፡ የሚወጉ ፡ ቃላት ፡ ናቸው። ነገር ፡ ግን ፡ ትርጉማቸው ፡ ለማንም ፡ ሰው ፡ በቀላሉ ፡ በቶሎ ፡ የሚገባ ፡ አይደለም ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ ሁለትና ፡ ሦስት ፡ ዓይነት ፡ ፍቺዎች ፡ ስለሚገኙባቸው ፡ ተራው ፡ ሕዝብ ፡ የሚረዳው ፡ መጋረጃ ፡ ሆኖ ፡ ጎልቶ ፡ የሚገኘውን ፡ ሰም ፡ የምንለውን ፡ የመጀመሪያውን ፡ ክፍል ፡ ብቻ ፡ ነው። ጨዋታው ፡ ወይም ፡ ውዝግቡ ፡ አቻ ፡ ለአቻ ፡ የሆነ ፡ እንደሆነ ፡ ከሁለቱም ፡ ዐዋቆች ፡ አንደበት ፡ የረቀቀ ፡ ምሥጢር ፡ የተዳፈነበት ፡ ንግግር ፡ ይሰማል።

እንደነአለቃ ፡ ገብረ ፡ ሐና ፡ አለቃ ፡ መልካሜ ፡ መምሕር ፡ ዕዝራ ፡

ዐራት ፡ ዓይና ፡ ጎሹ ፡ ነጋድራስ ፡ ተሰማ ፡ እሸቴ ፡ አቶ ፡ ማኅተመ ፡ ወርቅ ፡ እሸቴ ፡ ከአሉትና ፡ እነሱንም ፡ ከመሳሰሉት ፡ የአማርኛ ፡ ባለቤቶች ፡ ጋራ ፡ በነገር ፡ ለመቋቋም ፡ በጣም ፡ ከባድና ፡ ኣስቸጋሪ ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ ያውቋቸው ፡ የነበሩ ፡ ሰዎች ፡ ይናገራሉ። በአንዳንዶቹም ፡ የደረስንባቸው ፡ ስለሆነ ፡ የተባለውን ፡ ለመገንዘብ ፡ ችለናል። እነዚህም ፡ ተናጋሪው ፡ ምንም ፡ እንኳቀናውን ፡ መንገድ ፡ የተከተለ ፡ ቢሆን ፡ ከሚሰሙትም ፡ ሆነ ፡ ከአንደበታቸው ፡ ከሚፈልቀው ፡ ነገር ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ እጥፍና ፡ አሻሚ ፡ ሆነው ፡ ድርብ ፡ ትርጉም ፡ የሚሰጠው ፡ ቃላትን ፡ ለማግኘትና ፡ ለማሰማት ፡ የተለየ ፡ ስጦታ ፡ ነበራቸው።

ቋንቋችንም ፡ ለእነዚህ ፡ ሰዎች ፡ ደህና ፡ አድርጎ ፡ ስለሚታዘዝ ፡ በኣሉበት ፡ መንገድ ፡ ተመርቶ ከአለሙበት ፡ ይደርሳል። እንደዘበት ፡ ጣል ፡ አድርገው ፡ የሚያልፉት ፡ ቃል ፡ ልብ ፡ አድርጎ ፡ ለሚሰማውና ፡ ውስጡን ፡ ለሚመረምረው ፡ ሰው ፡ ውስጠ-ወይራ ፡ የሆነ ፡ ዘለፋ ፡ ወይም ፡ ምስጋና ፡ ይዞ ፡ ይገኛል።

ደረቅ ፡ ስድብ ፡ ነው ፡ ለማለት ፡ ግን ፡ አይቻልም ፡ በነገር ፡ የተጎነጠው ፡ ሰው ፡ የተዘለፈ ፡ ቢሆንም ፡ ቅሉ ፡ ለመከራከር ፡ ከአስቸጋሪ ፡ ሁናቴ ፡ ላይ ፡ ይወድቃል። አንደኛውን ፡ ትርጉም ፡ ይዞ ፡ እንዲህ ፡ ተባልኩ ፡ ቢል ፡ አይደለም ፡ እኔ ፡ እንዲህ ፡ ነው ፡ ያልሁት ፡ ብሎ ፡ በሁለተኛው ፡ ፍቺ ፡ ሊያሸንፈው ፡ ይችላል። ለምሳሌ ፡ ያህል ፡ ከቧልቶቹ ፡ ጥቂቶችን ፡ ከዚህ ፡ ቀጥዬ ፡ ጽፌአለሁ።

**(ሀ)** አለቃ ፡ ገብረ ፡ ሐና ፡ በተሾሙበት ፡ ደብር ፡ የሚያገለግል ፡ አንድ ፡ መልከ ፡ ጥፉ ፡ ፉንጋ ፡ ደብተራ ፡ ይኖር ፡ ኖሮ ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ይህ ፡ ሰው ፡ አለቃን 'ያለ ፡ ጫማ ፡ ሲሄዱ ፡ አያቸውና ፡ መምሕር ፡ ምነው ፡ በባዶ ፡ እግርዎ ፡ ጫማ ፡ አይገዙም? ቢላቸው ፡ እስቲ ፡ አንተ ፡ ፊት ፡ ግዛ ፡ እኛ ፡ ደግሞ ፡ ኋላ ፡ እንገዛለን ፡ አሉት ፡ ይባላል።

**(ለ)** አንድ ፡ ታላቅ ፡ መስፍን ፡ እንደጥንቱ ፡ ልማድና ፡ ወግ ፡ ለመኳንንቱና ፡ ለሊቃውንቱ ፡ ግብር ፡ አግብተው ፡ ሲበላ ፡ ሲጠጣ ፡ ከአለቃ ፡ መልካሜ ፡ አጠገብ ፡ የተቀመጡ ፡ አንድ ፡ ባይተዋር ፡ ካህን ፡ በሳንሳ ፡ ከቀረበው ፡ ሥጋ ፡ እየቆረጡ በመብላት ፡ ፋንታ ፡ ወደ ፡ አኩፋዳቸው ፡ ይከቱ

፡ ኖሯል። በዚህ ፡ ነገር ፡ ሊቁ ፡ ተገርመው ፡ ምን ፡ ያለ ፡ ይሉኝታ ፡ ቢስ ፡ ሰው ፡ ነው ፡ እያሉ ፡ ሲያጉተመትሙ ፡ መስፍኑ ፡ አለቃ ፡ እንግዳውን ፡ ይጋብዙ ፡ እንጂ ፡ አሉ። ጌታዬ ፡ ሰውየው ፡ ሆዱን ፡ አሞታል ፡ አሉ ፡ እንዴት ፡ እያደረገ? ፡ ቢሏቸው። ኧረ ፡ እየቆረጠ ፡ ያስቀምጠዋል ፡ ሲሉ ፡ መለሱላቸው ፡ ይባላል።

**(ሐ)** አንድ ፡ የእጅ ፡ ዐመል ፡ ያለበት ፡ የቆሎ ፡ ተማሪ ፡ የመምሕሩን ፡ ዳዊት ፡ ሠረቀና ፡ ጠፍቶ ፡ ሲኖር ፡ ከብዙ ፡ ጊዜ ፡ በኋላ ፡ እግር ፡ ጥሎት ፡ ከሠረቀበት ፡ ገዳም ፡ ተመልሶ ፡ አስተማሪውም ፡ ድንገት ፡ ስለአገኙት ፡ ልጄ ፡ እንደምን ፡ አለህ ፡ ዛሬ ፡ ከየት ፡ ተገኘህ ፡ ዳዊት ፡ ለመድገም ፡ ከገዳማችን ፡ መጣህ ፡ ወይ? አሉት ፡ ይባላል።

**(መ)** አንድ ፡ ችግረኛ ፡ ሰው ፡ አቅሙ ፡ በሚፈቅድለት ፡ መጠን ፡ ድግስ ፡ ደግሶ ፡ ዘመድ ፡ ወዳጁን ፡ ሲጠራ ፡ ጎረቤቱ ፡ የሆኑትንም ፡ አንድ ፡ መምሕር ፡ አብሮ ፡ ጋበዛቸው።

እኚህ ፡ ሰው ፡ ደህና ፡ ምግብና ፡ ጠጅ ፡ የለመዱ ፡ ስለሆነ ፡ የቀረበላቸው ፡ ጠላውም ፡ ሆነ ፡ ወጡ ፡ እንደነገሩ ፡ ስለ ፡ ነበር ፡ አልበላልህ ፡ አልጠጣልህ ፡ አላቸው። ለይምሰል ፡ ብቻ ፡ እንጀራውን ፡ እየቆረሱ ፡ ጣል ፡ ሽክናቸውን ፡ ተከንፈራቸው ፡ እያደረሱ ፡ መልሰው ፡ ቁጭ ፡ ያደርጉት ፡ ጀመር።

ሰውየውም ፡ ሁኔታቸውን ፡ ተመልክቶ ፡ ነገሩ ፡ ስለገረመው። ቀረብ ፡ አለና ፡ መምሕር ፡ ይጋበዙ ፡ እንጂ? ምነው ፡ ቢላቸው ፡ አለቃ ፡ አንገታቸውን ፡ ገደድ ፡ ፊታቸውን ፡ ፈገግ ፡ አደረጉና ፡ በገዛ ፡ ቤታችን ፡ መች ፡ ጋባዥ ፡ ያስፈልገናል ፡ ቢሻን ፡ (በጋልኛ ፡ ውሃ) ፡ እንጠጣለን ፡ ቢሻን ፡ እንበላለን ፡ አሉት ፡ ይባላል።

## <u>፳ ፡ ዕንቆቅልሽ።</u>

ዕንቆቅልህ ፡ በግዕዝ ፡ «ዐንቆቅሆ» ፡ ማለት ፡ ነው። ወደ ፡ አማርኛ ፡ ሲተረጎም ፡ ዐንቆቅሆ ፡ ዕንቁላል ፡ ማለት ፡ ይሆናል ፡ ስለዚህ ፡ ዕንቆቅልህ ፡ ማለት ፡ በስረ ፡ መሠረቱ ፡ እንደ ፡ ዕንቁላል ፡ ድፍን ፡ የሆነ ፡ ፍቺው ፡ ያልታወቀ ፡ መመርመርን ፡ የሚጠይቅ ፡ ፈተና ፡ ማለት ፡ ነው።

ዕንቆቅልህ ፡ የአእምሮ ፡ ንቃትን ፡ ይጠይቃል ፡ ተጠያቂው ፡ ወይም ፡ ተፈታኙ ፡ ሰው ፡ በተወሰነ ፡ ሰዓት ፡ የምሳሌውን ፡ ፍቺ ፡ ማግኘት ፡ አለበት ፡ አለዚያ ፡ አገር ፡ መስጠትና ፡ መሰደብ ፡ ይኖርበታል። ነገር ፡ ግን ፡ በተወሰነ ፡ ደቂቃ ፡ ውስጥ ፡ ትክክለኛ ፡ የሆነውን ፡ ፍቺ ፡ ያገኘ ፡ እንደሆነ ፡ አገር ፡ ከመስጠትና ፡ ከመሰደብ ፡ ይድናል ፡ የአእምሮ ፡ ዝቅተኛነትም ፡ አይሰማውም።

ዕንቆቅልሽ ፡ ሥዕላዊ ፡ ምርመራን ፡ ይፈልጋል ፡ ጠያቂው ፡ የረቀቀና ፡ የበሰለ ፡ ምሥጢር ፡ ያዘለ ፡ ምሳሌን ፡ ሲያቀርብ ፡ ተጠያቂው ፡ ከምሳሌው ፡ ጋራ ፡ የሚነጻጸሩትን ፡ ነገሮች ፡ ሁሉ ፡ እያሰበ ፡ ትክክለኛ ፡ ከሆነ ፡ መልስ ፡ እስኪደርስ ፡ ማውጣት ፡ ማውረድና ፡ መመርመር ፡ የሚያሻው ፡ ነው።

ትርጉም ፡ የሚሆኑትን ፡ ነገሮች ፡ ሁሉ ፡ በዓይነ ፡ አእምሮ ፡ እየተመለከተ ፡ ከምሳሌው ፡ ጎን ፡ ለጎን ፡ እየኮለኮለ ፡ ማስተያየትና ፡ ማነጻጸር ፡ ይኖርበታል ፡ ተፈታኙ ፡ እንደዒላማ ፡ አነጣጥሮ ፡ ከእውነተኛው ፡ ትርጉም ፡ ሲደርስ ፡ የዕንቆቅልሹ ፡ ትርጉም ፡ ይህ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ይመልሳል።

በትግል ፡ አቅምን ፡ በመገመት ፡ ጉልበትን ፡ መፈተን ፡ እንደሚቻል ፡ ሁሉ ፡ በዕንቆቅልሽም ፡ የአእምሮን ፡ ንቃትና ፡ የአሳብን ፡ ኃይል ፡ ማወቅ ፡ ይቻላል ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ አንድ ፡ ዓይነት ፡ አስተያየት ፡ የለውም ፡ አንዱ ፡ ከሌላው ፡ በችሎታ ፡ ይበልጣል ፡ አንዱ ፡ ደግሞ ፡ የተለየ ፡ ስጦታ ፡ ኖሮት ፡ በአንደኛው ፡ ነገር ፡ ንቁ ፡ ሲሆን ፡ በሌላው ፡ ይደክማል ፡ ስለዚህ ፡ አንዳንድ ፡ ልጆች ፡ ብቻ ፡ ዕንቆቅልሽን ፡ ቶሎ ፡ ለማግኘትና ፡ ትክክለኛም ፡ ፍች ፡ ለመስጠት ፡ ይችላሉ።

እንቆቅልሽ ፡ ጊዜን ፡ የሚጠይቅ ፡ የምርመራ ፡ ፈተና ፡ ነው። ይሁን ፡ እንጂ ፡ ጥያቄው ፡ በተወሰነ ፡ ደቂቃ ፡ ውስጥ ፡ መመለስ ፡ አለበት ፡ የዕንቆቅልሹ ፡ አቅራቢ ፡ «መሽብህ ፡ ዕንቆቅልሼ ፡ ጠነዛብህ ፡ ዋለብህ ፡ አደረብህ ፡ አገር ፡ ስጠኝ» ፡ እያለ ፡ ተጠያቂውን ፡ ይወተውተዋል ፡ ያዋክበዋል።

ተጠያቂው ፡ ዕንቆቅልሹን ፡ መፍታትና ፡ ከትርጉሙ ፡ መድረስ ፡ ያቃተው ፡ እንደሆነ ፡ አገር ፡ ይሰጠዋል ፡ በዚህም ፡ ድል ፡ መሆኑንና ፡ መሸነፉን ፡ ስለሚገልጥ ፡ የአእምሮ ፡ ዝቅተኛነት ፡ ይሰማዋል ፡ የዕንቆቅልሹ ፡

ባለቤት ፡ በበኩሉ ፡ ይደሰታል። የአገሩን ፡ ስም ፡ እየጠየቀ ነ አነሰኝ ፡ ጨምርልኝ ፡ እያለ ፡ ያስገድደዋል ፡ የሚመኘውንና ፡ የሚፈልገውን ፡ ከአገኘ ፡ በኋላ ፡ እዚህ ፡ ተቀምጨ ፡ ምን ፡ አጥቼ ፡ ሁሉ ፡ በእጁ ፡ ሁሉ ፡ በደጁ ፡ እንዳልሰድብህ ፡ ወንድሜ ፡ እንዳልተውህ ፡ ጠላቴ ፡ እያለ ፡ ይወቅሰዋል።

በዚህ ፡ ጊዜ ፡ በጠያቂውና ፡ በተጠያቂው ፡ ፊት ፡ ላይ ፡ የበላይነትና ፡ የበታችነትን ፡ ስሜት ፡ ማንበብ ፡ አዳጋች ፡ አይሆንም። የዕንቆቅልሹ ፡ ባለቤት ፡ በጌታ ፡ ሁናቴ ፡ በሡንጋ ፡ በቅሎ ፡ ሆኜ ፡ አንተን ፡ አሽከሬን ፡ በገጣባ ፡ አህያ ፡ አስቀምጨ ፡ እያለ ፡ የተሸናፊውን ፡ ዝቅተኛነት ፡ ያስረዳዋል።

ከዚህም ፡ አነጋገር ፡ ታላቅ ፡ ምሥጢር ፡ እናገኛለን ፡ ይኸውም ፡ በአእምሮ ፡ ያልጎለመሰ ፡ የማሰብ ኃይሉ ፡ ከተፈጥሮ ፡ ኋደኛው ፡ ያነሰ ፡ ሁሉ ፡ ለወንድሙ ፡ አሽከር ፡ ሆኖ ፡ መኖሩን ፡ የሚያስገነዝብ ፡ ነው።

ምንም ፡ እንኳ ፡ በቀድሞ ፡ ጊዜ ፡ ለጉልበት ፡ ሥራ ፡ ብቻ ፡ ከፍተኛ ፡ ግምት ፡ ቢሰጠው ፡ አባቶቻችን ፡ የማስተዋል ፡ ንቃት ፡ የመንፈስ ፡ ብርታትና ፡ የናላ ፡ ኃይል ፡ አስፈላጊ ፡ መሆኑን ፡ አልዘነጉትም።

በዕንቆቅልሽ ፡ የሚገኘውንም ፡ ጥቅም ፡ ለመረዳት ፡ ከአሁን ፡ በፊት ፡ ብላታ ፡ ወልደ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ወልደ ፡ ዮሐንስ ፡ አንዲት ፡ መጽሐፍ ፡ ስላዘጋጁ ፡ እሷኑ ፡ መመልከት ፡ ይጠቅማል።

ይህን ፡ አጭር ፡ መግቢያ ፡ ከሰጠን ፡ በኋላ ፡ ለምሳሌ ፡ ያህል ፡ ከዕንቆቅልሾቹ ፡ መካከል ፡ አንዳንዶቹን ፡ ከዚህ ፡ አስከትዬ ፡ ጽፌአለሁ።

### <u>1. **ጥ**) ዕንቆቅልህ? ምን ፡ አውቅልህ?</u>

ላዩ ፡ ሰርዶ ፡ ውስጡ ፡ ብርንዶ ፡

**መ)** ቀይ ፡ ሽንኩርት ፡ ነው ፡

በልጣጭ ፡ የተሸፈነ ፡ ሽንኩርት ፡ ሲገልጡት ፡ እንደሚያስደስት ፡ በአቋሙ ፡ ወይም ፡ በአለባበሱ ፡ አልባሌ ፡ የሆነ ፡ ሰውም ፡ በቅርብ ፡ ሲታይ ፡ እና ፡ ሲመረመር ፡ የቁም ፡ ነገር ፡ ጎተራ ፡ ሊሆን ፡ ይችላል ፡

### <u>2. ጥ) ዕንቆቅልህ? ምን ፡ አውቅልህ?</u>

ሲወለድ ፡ ይጠቁር ፡ ሲያረጅ ፡ ይቀላ።

**መ)** በርበሬ።

በርበሬ ፡ አበባውን ፡ ጥሎ ፡ እምቡጥ ፡ በያዘ ፡ ጊዜ ፡ ዛላው ፡ ጥቁር ፡ ነው። በኋላ ፡ ሲበስል ፡ ግን ፡ ወደ ፡ ቀይነት ፡ ይለወጥና ፡ አገልግሎቱን ፡ ያበረክታል። ሰውም ፡ ገና ፡ ሲወለድ ፡ በዕውቀት ፡ ያልጎለመሰ ፡ ስለሆነ ፡ ክፉውንና ፡ በጎውን ፡ ለይቶ ፡ ለማወቅ ፡ አይችልም ፡ በዕድሜና ፡ በትምህርት ፡ ከአደገ ፡ በኋላ ፡ ግን ፡ በሕሊናው ፡ የዕውቀት ፡ ብርሃን ፡ ስለሚሳልበት ፡ የሥራ ፡ ፍሬውን ፡ ለሀገሩና ፡ ለወገኑ ፡ ያበረክታል።

## 3. ጥ) እንቆቅልህ? ምን ፡ አውቅልህ?

በትልቅ ፡ ምጣድ ፡ ትንሽ ፡ ዕንጐቻ:

**መ)** ጨረቃ ፡ ናት።

ጨረቃ ፡ ሙሉ ፡ በሆነች ፡ ጊዜ ፡ ሌሊት ፡ በጠራ ፡ ሰማይ ፡ ላይ ፡ ሲመለከቷት ፡ በሠፊ ፡ ምጣድ ፡ የተጋገረ ፡ ዕንጎቻን ፡ ስለምትመስል ፡ ሰማዩ ፡ በምጣድ ፡ ጨረቃዋ ፡ በእንጎቻ ፡ ተመስለዋል።

## 4. ጥ) ዕንቆቅልህ? ምን ፡ አውቅልህ?

ወተቱ ፡ ጥቁር ፡ ማለቢያው ፡ ነጭ።

**መ)** ቡና ፡ ነው።

ቡና ፡ በጀበና ፡ ወይንም ፡ በኩስኩስት ፡ ከፈላ ፡ በኋላ ፡ በስኒ ፡ እየተከፋፈለ ፡ ለሰዎች ፡ ይታደላል ፡ ስለዚህ ፡ ቡናው ፡ በወተት ፡ ስኒው ፡ ደግሞ ፡ በማለቢያ ፡ ተመሰሉ።

## 5. ጥ) ዕንቆቅልህ? ምን ፡ አውቅልህ?

የክፉ ፡ ላም ፡ ማሠሪያዋ ፡ እሳት።

**መ)** ንብ ፡ ናት።

ንብ ፡ በተፈጥሮዋ ፡ ብልህ ፡ እንደሆነች ፡ ይነገርላታል ፡ በብዙ ፡ ድካም ፡ ያጠራቀመችው ፡ ማር ፡ ሲወሰድባትም ፡ በሽንኮሯ ፡ ትናደፋለች። ስለዚህ ፡ ማሩ ፡ በሚቈረጥበት ፡ ጊዜ ፡ በኩበት ፡ ጢስ ፡ ስለምትታፈን ፡ የክፉ ፡ ላም ፡ ማሠሪያዋ ፡ እሳት ፡ ተባለ።

## 6. ጥ) ዕንቆቅልህ? ምን ፡ አውቅልህ?

እልም ፡ ካለ ፡ ዱር ፡ ገብቼ ፡ የምቆርጠው ፡ አጥቼ።

**መ)** ጉም ፡ ነው።

ጉም ፡ በክረምት ፡ ወራት ፡ ጥቅጥቅ ፡ አድርጎ ፡ ሲይዝ ፡ ዛፍና ፡ ዛፉ ፡ በሐረግ ፡ የተጠላለፈ ፡ ጫካን ፡ ይመስላል ፡ ከውስጡ ፡ ሲገቡ ፡ ግን ፡ አንድም ፡ ሚጨበጥ ፡ ነገር ፡ የለም ፡ ሰውም ፡ ሊያገኘው ፡ በማይችለው ፡ የምኞት ፡ ጫካ ፡ ውስጥ ፡ ገብቶ ፡ ሲባዝን ፡ ይኖርና ፡ አንዱን ፡ ሳይዘው ፡ እንዲው ፡ በከንቱ ፡ ባክኖ ፡ ይቀራል።

## 7. ጥ) ዕንቆቅልህ? ምን ፡ አውቅልህ?

ልብስም ፡ ጉርስም ፡ ትሆን።

**መ)** በግ ፡ ናት።

በግ ፡ በሕይወቷ እስካለች ፡ ጊዜ ፡ ድረስ ፡ ጠጉሯ ፡ እየተሸለተ ፡ ልብስ ፡ ስለሚሆን ለሰው ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ጥቅም ፡ ትሰጣለች ፡ ከታረደችም ፡ በኋላ ፡ ሥጋዋ ፡ በምግብነት ፡ በብዙ ፡ መንገድ ፡ ያገለግላል። አንዳንድ ፡ ደጋግ ፡ ሰዎችም ፡ በሕይወተ-ሥጋ ፡ ሳሉ ፡ ከወገኖቻቸው ፡ ጋራ ፡ ሲበሉና ፡ ሲጠጡ ፡ ለደኃም ፡ ሲመጸውቱ ፡ ኖረው ፡ ከሞቱ ፡ በኋላ ፡ ቀሪው ፡ ንብረታቸውን ፡ ለነዳያንና ፡ ለወገኖቻቸው ፡ ይናዘዛሉ።

## 8. ጥ) ዕንቆቅልህ? ምን ፡ አውቅልህ?

እናቲቱ ፡ ወደ ፡ ዱር ፡ ልጅቱ ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን።

**መ)** ሠጎን ፡ (ዕንቁላልዋ) ፡ ነው።

ሠጎን ፡ በበረሐ ፡ የምትኖር ፡ በራሪ ፡ ናት ፡ ይሁን ፡ እንጂ ፡ ዕንቁላልዋ ፡ እየተፈለገ ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ጉልላት ፡ ይውላል ፡ እናቲቱ ፡ ወደ ፡ ዱር ፡ ልጂቱ ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ተብሎ ፡ የሚነገረውም ፡ ስለዚህ ፡ ነው። እንደዚህም ፡ ከዳር ፡ አገርም ፡ ሆነ ፡ ከአልባሌ ፡ ቤተሰብ ፡ የመጣ ፡ ሰው ፡ በቤተ ፡ መንግሥት ፡ ሆኖ ፡ ክብር ፡ ባለው ፡ ቦታ ፡ ቁም ፡ ነገር ፡ ያለው ፡ ሥራ ፡ ለመሥራት ፡ መቻሉን ፡ ያስገነዝበናል።

## 9. ጥ) ዕንቆቅልህ? ምን ፡ አውቅልህ?

የድንጋይ ፡ ንጉሥ ፡ የቅጠል ፡ ትኩስ።

**መ)** የድንጋይ ፡ ንጉሥ ፡ የተባለው ፡ ጨው ፡ ነው።

የቅጠል ፡ ትኩስ ፡ የተባለው ፡ በርበሬ ፡ ነው። ጨው ፡ በተፈጥሮው ፡ ድንጋይን ፡ ይመስላል ፡ ነገር ፡ ግን ፡ የልዩ ፡ ልዩ ፡ ምግቦች ፡ ማጣፈጫ ፡ ስለሆነ ፡ በሚያው ፡ የድንጋይ ፡ ንጉሥ ፡ ተባለ። እንዲሁም ፡ በርበሬ ፡ በግብሩ ፡ የቅጠል ፡ ትኩስ ፡ ተሰኘ። አሳቻ ፡ የሆነ ፡ ሰውም ፡ ታላቅ ፡ ሚያ ፡ ሲሠራ ፡ ከመጠኑ ፡ ስሙና ፡ ደረጃው ፡ በልጦ ፡ ይታያል። ይህም ፡ በመልካቸውና ፡ በቁመናቸውከሚያምሩ ፡ ሰዎች ፡ ይልቅ ፡ ከአልባሌዎቹ ፡ ዘንድ ፡ ታላቅ ፡ ቁም ፡ ነገር ፡ መገኘቱንም ፡ ያስረዳል።

## 10.ጥ) ዕን ህ? ምን ፡ አውቅልህ?

ሐምሳ ፡ ጨፋሪ ፡ አንድ ፡ በርባሪ።

**መ)** የወጥ ፡ እንጨት ፡ ነው። (ማማሰያ)።

ወጥ ፡ በእሳት ፡ ኃይል ፡ ይሰክርና ፡ እንደተከደነ ፡ ሲፈላ ፡ ጥሬና ፡ ብስል ፡ እንዳይሆን ፡ በማማሰያው ፡ ሲበረበር ፡ ድምጹ ፡ ይቀነሳል ፡ እንዲሁም ፡ ፎካሪዎችን ፡ በመካከላቸው ፡ አንድ ፡ ቆራጥ ፡ ጀግና ፡ በድንገት ፡ በደረሰ ፡ ጊዜ ፡ ጭጭ ፡ ያደርጋቸዋል። ምሳሌ ፡ ተልባ ፡ ቢንጫጫ ፡ በአንድ ፡ ሙቀጫ።

## 11. ጥ) ዕንቆቅልህ? ምን ፡ አውቅልህ?

ምን ፡ ቢወደ ፡ ት ፡ ወንዝ ፡ አያሻግሯት።

**መ)** ቦታ ፡ ናት።

በዚች ፡ በአለንባት ፡ ዓለም ፡ ላይ ፡ እንደቦታ ፡ ያለ ፡ ተወዳጅ ፡ ነገር ፡ የለም ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ምንም ፡ ቢወደ ፡ ት ፡ ለማነቃነቅና ፡ ከወንዝ ፡ ማዶ ፡ ለማሸጋገር ፡ አይቻልም። በዚህ ፡ ዓይነት ፡ ማናቸውም ፡ ለዓይን ፡ የሚያስደስቱ ፡ ከመሬት ፡ ጋራ ፡ የተያያዙ ፡ ነገሮች ፡ ሁሉ ፡ ምንም ፡ ቢወደዱ ፡ ሊንቀሳቀሱ ፡ አለመቻላቸውን ፡ ያሳስበናል።

12. **ጥ**) ዕንቆቅልህ? ምን ፡ አውቅልህ?

እቴ ፡ ጥና ፡ ጥና ፡ ታጥቃ ፡ በዘጠና ፡ እሷም ፡ አብዳ ፡ ሰው ፡ ታሳብድ።
**መ**) ከበሮ ፡ ናት።

በሸንሸን ፡ ቀሚስ ፡ ዓይነት ፡ ማህል ፡ ወገቧ ፡ በጠፍር ፡ የተለበጠውና ፡ አፍ ፡ በቆዳ ፡ የተለጐመው ፡ ከበሮ ፡ በስልት ፡ ሲመቷት ፡ የምታሰማው ፡ ድምፅ ፡ ተወዳጅነት ፡ ስለ ፡ አለው ፡ እርሷ ፡ አብዳ ፡ አብዳ ፡ ሰውንም ፡ ታሳብዳለች ፡ ተብሎ ፡ ይነገራል። እንዲሁም ፡ ተናግሮ ፡ የሚያናግር ፡ ክፉ ፡ ሥርቶ ፡ የሚያሠራ ፡ አብዶ ፡ የሚያሳብድ ፡ ስላለ ፡ መጠንቀቅ ፡ እንደሚገባ ፡ ያስገነዝበናል።

13. **ጥ**) ዕንቆቅልህ? ምን ፡ አውቅልህ?

እንደ ፡ እንጀራ ፡ ንብርብር ፡ እንደነብር ፡ ዝንጉርጉር።
**መ**) ዳዊት።

ዳዊት ፡ ዘሩ ፡ የተጻፈበት ፡ ብራና ፡ ወይንም ፡ ወረቀት ፡ አቀማመጡ ፡ የተደራረበ ፡ በመሆኑ ፡ እንደ ፡ እንጀራ ፡ ንብርብር ፡ ተባለ ፡ በነጩ። ብራና ፡ ወይንም ፡ ወረቀት ፡ ላይ ፡ የተጻፈው ፡ ቀለም ፡ ደግሞ ፡ ጥቁርና ፡ ቀይ ፡ በመሆኑ ፡ እንደነብር ፡ ዝንጉርጉር ፡ ተሰኘ።

14. **ጥ**) ዕንቆቅልህ? ምን ፡ አውቅልህ?

እናቷን ፡ አትመስል ፡ አባቷን ፡ አትመስል፣አለች ፡ እንዲት ፡ ብስል።
**መ**) በቅሎ።

መቸም ፡ ልጅ ፡ ተወልዶ ፡ እናቱን ፡ ወይም ፡ አባቱን ፡ መምሰል ፡ አለበት። በቅሎ ፡ ግን ፡ ከፈረስና ፡ ከአእያ ፡ ተወልዳ ፡ ከሁለቱም ፡ የተለየች ፡ በመሆኗ ፡ የተነገረ ፡ ነው።

15. **ጥ**) ዕንቆቅልህ? ምን ፡ አውቅልህ?

ጉድ ፡ መጣ ፡ ጉዳጉድ ፡ መጣ ፡ ገንፎ ፡ ከዛፍ ፡ ላይ ፡ ወጣ።
**መ**) ሙዝ።

ሙዝ ፡ ከዛፍ ፡ ተክል ፡ የሚገኝ ፡ የፍሬ ፡ ምግብ ፡ ቢሆንም ፡ አላላሙ ፡ የእህል ፡ ቅቤን ፡ ስለሚመስል ፡ በገንፎ ፡ ተመስሏል።

## 16. ጥ) ዕንቆቅልህ? ምን ፡ አውቅልህ?

ትንሽ ፡ ምላጭ ፡ ሀገር ፡ ትላጭ።

**መ**) እሳት።

በትንሽ ፡ ምላጭ ፡ ረዥም ፡ ጉተና ፡ እንዲላጭ ፡ ሁሉ ፡ እሳትም ፡ በትንሹ ፡ ተያይዞ ፡ ብዙ ፡ ሀገር ፡ ለማቃጠል ፡ ይችላል።ይህም ፡ ምሳሌ ፡ አላኳሽ ፡ ያመጣው ፡ ትንሹ ፡ ጸብ ፡ ተስፋፍቶ ፡ ለሀገርም ፡ ሆነ ፡ ለዓለም ፡ የሚተርፍ ፡ መሆኑን ፡ ሊያስገነዝበን ፡ ይችላል።

## 17. ጥ) ዕንቆቅልህ? ምን ፡ አውቅልህ?

ሲሄድ ፡ እንደሬሳ ፡ ሲጮህ ፡ እንደ ፡ አንበሳ።

**መ**) ጠብ ፡ መንጃ ፡ ነው።

ጠብ ፡ መንጃ ፡ በሰው ፡ ትከሻ ፡ በመዋሉ ፡ በሬሳ ፡ ተመሰለ ፡ ግን ፡ ቃታው ፡ ሲሳብ ፡ የሚሰጠው ፡ ድምፅ ፡ አስፈሪነት ፡ ስለአለው ፡ እንደ ፡ አንበሳ ፡ ጩኸት ፡ ተሠይሟል።

# ሦስተኛ ፡ ክፍል

## የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ያገር ፡ ባህሎች።

### ሀ ፡ በአንደበት ፡ የሚገለጡ።

#### ፩ ፡ ቀረርቶ ፡ ወይም ፡ ሽለላ።

ኢትዮጵያ ፡ በፈጣሪዋ ፡ ተመክታ ፡ በክንዷ ፡ ተፈርታ ፡ የምትኖር ፡ የጐበዞች ፡ ሀገር ፡ የጀግኖች ፡ አምባ ፡ ናት።

ኢትዮጵያዊ ፡ ግፍንና ፡ ጥቃትን ፡ አይወድም ፡ ከዚህም ፡ የተነሣ ፡ ስንኳን ፡ እሱ ፡ ራሱ ፡ ወገኑ ፡ ሲበደል ፡ ባየ ፡ ጊዜ ፡ ትዕግሥቱ ፡ ያልቅና ፡ ጠላትን ፡ ለመቀበል ፡ እጁ ፡ ፈጥናል። ጀግንነት ፡ ሲወርድ ፡ ሲዋረድ ፡ ተያይዞ ፡ ከአባት ፡ ለልጅ ፡ የተላለፈ ፡ ቅርሱ ፡ ነው ፡ ወላጆችም ፡ ልጆቻቸው ፡ ፈለጋቸውን ፡ ተከትለው ፡ ጐበዝ ፡ ሆነው ፡ እንዲያድጉላቸው ፡ በብርቱ ፡ ይጥራሉ ፡ የቤተሰባቸውም ፡ ዝና ፡ ተጠብቆ ፡ እንዲኖር ፡ ሲታገሉ ፡ ማየት ፡ አዲስ ፡ ነገር ፡ አይሆንም።

ስለዚህ ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ አባቶች ፡ የጀብዱ ፡ ሥራ ፡ በናላቸው ፡ እንዲቀረጽ ፡ ልጆቻቸውን ፡ ቀረርቱ ፡ እያሰሙ ፡ ያሳድጓቸዋል ፡ ቀረርቱ ፡ ወይም ፡ ሽለላ ፡ ማለት ፡ የጦርነት ፡ ዘፈን ፡ ነው ፡ ወይም ፡ ወታደር ፡ በጌታው ፡ ፊት ፡ በሰልፍ ፡ መካከልና ፡ በጨዋታ ፡ ላይ ፡ የወንዶችን ፡ ወኔ ፡ ለማነቃቃት ፡ በዜማ ፡ የሚያሰማው ፡ ቃል ፡ ነው።

አቅራሪዎች ፡ በሰልፍ ፡ ውስጥ ፡ ወይም ፡ በግብር ፡ ላይ ፡ የጀግኖችን ፡ ልቡና ፡ በሽለላ ፡ እንደበገና ፡ አውታር ፡ እየቃኙ ፡ በየጦሩ ፡ ሜዳ ፡ የወደቁትን ፡ ለሀገራቸው ፡ ታላላቅ ፡ ጀብዱዎች ፡ ሠርተው ፡ የሞቱትን ፡ የጦር ፡ ስልት ፡ በሆነ ፡ ዜማ ፡ በአማረ ፡ ድምፅ ፡ ምሥጢር ፡ ያላቸውን ፡ ግጥሞች ፡ በአሰሙ ፡ ጊዜ ፡ ባለሱሪዎቹን ፡ በልጓም ፡ እንደተያዙ ፡ ፈረሶች ፡ ያቅበጠብጧቸዋል ፡ ደማቸው ፡ እንዲፈላ ፡ አድርገው ፡ መቀመጥ ፡ እስኪሳናቸው ፡ ቦታ ፡ እስኪጠባቸው ፡ ያሟሙቋቸዋል።

በዚህ ፡ ጊዜ ፡ አላስችል ፡ ይላቸውና ፡ ባለወኔዎቹ ፡ ብድግ ፡ ብለው ፡ መፎከር ፡ ልማዳቸው ፡ ነው ፡ ቀረርቱና ፡ ፉከራ ፡ አይለያይም ፡ ቀረርቱ ፡ ይቀድማል ፡ ፉከራ ፡ ወይም ፡ ድንፋታ ፡ ይከተላል። ይህንንም ፡ አተኩረን ፡ የተመለከትን ፡ እንደሆነ ሽለላ ፡ ጠብ ፡ ማጫሪያ ፡ የነገር ፡ ማንሻ ፡ እንቁርቁሮሽን ፡ ይመስላል። ሽላዮች ፡ ጀግኖችን ፡ በማመስገን ፡ በመንቀፍና ፡ በመገሥጽ ፡ ወጣቶችን ፡ አነቃቅተው ፡ ለመንፈስ ፡ ብርታትን ፡ ከአስገኙም ፡ በኋላ ፡ እንኳን ፡ የወንዶችን ፡ የሴቶችንም ፡ ቢሆን ፡ የቆራጥነት ፡ ወኔአቸውን ፡ ይቀሰቅሱታል። ከቀረርቶዎቹ ፡ ውስጥ ፡ አንዳንዶቹን ፡ የሚሰጡትን ፡ ስሜት ፡ ለማወቅ ፡ ይቻል ፡ ዘንድ ፡ ከዚህ ፡ አስከትዬ ፡ ጽፌአቸዋለሁ።

ንዳው ፡ ላሙን ፡ ንዳው ፡ ላሙን ፡ አቧራው ፡ ይነሳ ፡
ይመጣ ፡ የለም ፡ ወይ ፡ ኮርማው ፡ እያገሳ። *ወኔ፡ስለመቀስቀስ (አጫሪ) ፡*

ካባቴ ፡ ባድማ ፡ ፍግ ፡ አታፍሱበት ፡ »
ነዷዱ ፡ ቢጠፋ ፡ የመጡ ፡ አለበት።

እነዚያ ፡ ወረዱ ፡ እንውረድባቸው ፡ »
አንበሳም ፡ ኣይደሉ ፡ እንደኛው ፡ ሰው ፡ ናቸው ፡ »

በዛ ፡ ምጡ ፡ በዛ ፡ ምጡ ፡ ወይ ፡ እኛ ፡ አልወረድን ፡
ወይ ፡ እነሱ ፡ ኣልመጡ።

ጦር ፡ አይመጣም ፡ ሲሉት ፡ ይመጣል ፡ ድንገት ፡ *ተዘጋጅቶ ፡*
ደህና ፡ ደህና ፡ ጐበዝ ፡ መርጠው ፡ ካልቆዩት። *መጠባበቅ ፡ ኣስፈላጊ ስለመሆኑ ፡*

በለው ፡ በለው ፡ ሲል ፡ ነው ፡ የጋሜ ፡ ኩራቱ ፡
ሴትም ፡ ትዋጋለች ፡ ከረጋ ፡ መሬቱ። *በጦር፡ጊዜ፡ ስለማደፋፈር*

ሂድ ፡ ሲሉት ፡ ካልሄደ ፡ ና ፡ ሲሉት ፡ ካልመጣ ፡ »
ስደደው ፡ ጐበዙን ፡ እጁን ፡ ይዞት ፡ ይምጣ።

ሱሪህን ፡ ከፍ ፡ አድርግ ፡ ጐራዴህን ፡ ቀና ፡ »
ከዚያም ፡ ቤት ፡ ከዚህም ፡ ባለደም ፡ ነህና።

እባክሽ ፡ እናቴ ፡ ውለጅልኝ ፡ መንታ ፡
ቀኝ ፡ እጄን ፡ ስመክት ፡ ግራ ፡ እጄ ፡ ተመታ። *ጥቃትን ፡ ስለመጥላት፡*

አጭር ፡ ነው ፡ ቀጭን ፡ ነው ፡ ዋጋም ፡ አያወጣ ፡
የጠመዱት ፡ እንደሁ ፡ ከፈርም ፡ አይወጣ ፡ *አልባሌ ፡ መስሎ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ዋጋ ፡ ያለው ፡ መሆኑን ፡ ስለመግለጥ ፡*

ተው ፡ በለው ፡ ተው ፡ በለው ፡ ይሞታል ፡ »
ሎጋው ፡ ሲወረወር ፡ አገዳ ፡ መስሎታል።

እንደዕውር ፡ መጋዣ ፡ ወዴት ፡ ጐድን ፡ ጐድን ፡
ሙት፡ ያለው፡ ሰው፡ ሊሞት፡ ዳን ፡ ያለው፡ ሰው፡ ሊድን። *ጓደኛውን ፡ ስለማነቃቃትና ፡ ስለመምከር ፡*

ፈረሱንም ፡ ጋልበው ፡ ላቡ ፡ እስኪንቆረቆር ፡
ነፍጡንም ፡ ተኩሰው ፡ ቃታው ፡ እስኪሰበር ፡
ጦሩንም ፡ ወርውረው ፡ ሶማያው ፡ ይሠንጠር ፡
አዳራሽ ፡ ሲገቡ ፡ አንገት ፡ ከማቀርቀር። »

ሞኙ ፡ ሎሌ ፡ ጅሉ ፡ ሎሌ ፡ ደጅ ፡ አጣኑኝ ፡ ይላል ፡
ጋሻው ፡ ከበረታ ፡ ጌታው ፡ መች ፡ ዝም ፡ ይላል። »

አባት ፡ ጀግና ፡ ሆኖ ፡ ልጅ ፡ የፈራ ፡ እንደሆን ፡
እናቱን ፡ ጠይቁ ፡ ዘር ፡ ለውጣ ፡ እንደሆን። »

ቢገዝፍ ፡ ቢደነድን ፡ ቢቆለል ፡ እንደ ፡ ጭድ ፡
ደንዳናውን ፡ አንድዶ ፡ ይቆርጠዋል ፡ ማጭድ። »

የለመደው ፡ መሸሽ ፡ የለመደው ፡
በመጫኛም ፡ ቢያስሩት ፡ ሄደ ፡ እየጐመደው። *ፈሪን ፡ ስለመገሠፅ ፡*

ቱሪ ፡ ናፉ ፡ ቱሪ ፡ ናፉ ፡
በጦር ፡ ሜዳ ፡ አትገኝ ፡ ከቀለቡ ፡ አትጠፉ ፡ »

አባዛኸኝ ፡ ተወኝ ፡ አባዛኸኝ ፡
አንተም ፡ ኣልተጠቀምክ ፡ እኔንም ፡ ጐዳኸኝ »

አየኸው ፡ ወይ ፡ ጫሜወ ፡ ሲቃጠል ፡
አየኸው ፡ ወይ ፡ ላንቃው ፡ ሲቃጠል ፡ *ደህና ፡ ኣለቃን ፡ ስለማመስገን ፡*

አባ ፡ ሻውል ፡ ደምስ ፡ (ራስ ፡ ደምሰው ፡ ነሲቡ)
ለነገም ፡ አይል።

ጮማውን ፡ በካራ ፡ ኣንተው ፡ ብቻ ፡ በልተህ ፡
ጠጁን ፡ በብርሌ ፡ ብቻህን ፡ ጠጥተህ ፡
የት ፡ ትገባ ፡ ይሆን ፡ ሆድኸን ፡ አንዘርጠህ። *መጥፎ ፡ አለቃን ፡ ስለ ፡መውቀስና ፡ ስለመዝለፍ ፡*

እነአገልግል ፡ ፍቱ ፡ እነሸማ ፡ ጋርዱ ፡ እነአሽከር ፡ ወጊዱ ፡
ጦርነት ፡ ሲመጣ ፡ ከመርፌ ፡ ቀዳዳ ፡ ይጠባል ፡ መንገዱ። »

ጭቅቅት ፡ ነው ፡ ቀሚስ ፡ አለቤቱ ፡
አሽከሮቹ ፡ ቆመው ፡ ሸሽ ፡ ባለቤቱ። »

## ፪ ፡ ፉከራ ፡ ወይም ፡ ድንፋታ።

ጀግኖች ፡ ለገዢዎቻቸው ፡ ወይም ፡ ለአለቆቻቸው ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ድምጽ ፡ በማሰማት ፡ ወኔአቸውን ፡ የሚገልጹበት ፡ የጦር ፡ ግጥም ፡ ነው።

ሽላዮች ፡ በጦር ፡ ሜዳ ፡ ላይ ፡ የተደረገውን ፡ ታላቅ ፡ ጀብዱ ፡ በማውሳት ፡ በአማረ ፡ ድምጽ ፡ በአቅራሩ ፡ ጊዜ ፡ ጀግኖቹ ፡ ደማቸው ፡ ይፈላና ፡ በፈጣን ፡ ንባብ ፡ ግጥም ፡ እየደረደሩ ፡ ጋሻቸውን ፡ አንግበው ፡ ጐራዴያቸውን ፡ ጨረቃ ፡ አስመስለው ፡ በሚታዘዙበት ፡ ቦታ ፡ ሁሉ ፡ ደማቸውን ፡ ለማፍሰስ ፡ ዝግጁ ፡ መሆናቸውን ፡ በሲቃና ፡ በወኔ ፡ በአንድ ፡ እግራቸው ፡ ተንበርክከው ፡ ወይም ፡ በተቅበጠበጡ ፡ ፈረሶች ፡ ሆነው ፡ እያስጨፈሩ ፡ ጦር ፡ እየሰበቁ ፡ ቃታ ፡ እየፈለቀቁ ፡ ወዲያና ፡ ወዲህ ፡

እየተንጐራደዱ ፡ የገደሉበትንና ፡ ጀብዱ ፡ የሠሩበትን ፡ ቦታ ፡ ወንዙንና ፡ መልካውን ፡ ለይተው ፡ በምስክር ፡ እያረጋገጡ ፡ ይፎክራሉ። የግጥሙ ፡ ስልት ፡ ከሽለላ ፡ ያጥራል። በውስጡም ፡ ደጊመ ፡ ቃል ፡ ይገኝበታል ፡ ለምሳሌ ፡ ዘራፍ ፡ ዘራፍ ፡ የጠቅል ፡ አሽከር ፡ የጠቅል ፡ ሎሌ ፡ ማለት ፡ የተለመደ ፡ ነው። ጀግና ፡ የሆነ ፡ ሰው ፡ ሲፎክር ፡ ጀግነንቱን ፡ የሚያውቁለት ፡ ኖር ፡ ብለው ፡ ይነሱለታል ፡ እሱም ፡ በእግዚአብሔር ፡ ተቀመጡ ፡ ይልና ፡ ፉከራውን ፡ ይቀጥላል። በመካከሉም ፡ ሙያውን ፡ የሚያውቁለትን ፡ እህ ፡ አገሴ ፡ እህ ፡ አገሴ ፡ ብሎ ፡ ሲጠይቃቸው ፡ ለካ ፡ ለካ ፡ አይተናል ፡ ሠርቷል ፡ እያሉ ፡ ያረጋግጡለታል። እሱም ፡ ደስ ፡ ብሎት ፡ ከዓይናችሁ ፡ ያውጣኝ ፡ ጌቶቼ ፡ ወንድሞቼ ፡ ተቀመጡ ፡ ይላል ፡ ሽለላው ፡ ሲቀጥል ፡ ደግሞ ፡ ሌላው ፡ ጀግና ፡ ይተካል። አንዱ ፡ ሲፎክር ፡ ሌላው ፡ ተደርቦ ፡ የደነፋ ፡ እንደሆነ ፡ ምነው ፡ በላዬ ፡ በምን ፡ በልጠሽኝ ፡ ነው? ተባብለው ፡ ሚያቸውን ፡ ይቋጠራሉ ፡ ለበለጠው ፡ ቅድሚያ ፡ ይሰጠዋል። ስለዚህም ፡ በሚያ ፡ ለመብለጥ ፡ በኣደባባይ ፡ ለመከበር ፡ ሹመት ፡ ሽልማት ፡ ለማግኘት ፡ ሀገርንና ፡ መንግሥትን ፡ ለማስከበር ፡ ሲሉ ፡ ወታደሮች ፡ በጦር ፡ ሜዳ ፡ ላይ ፡ ያለፍርሐትና ፡ ሥጋት ፡ ቀርበው ፡ ጠላታቸውን ፡ በጐራዴ ፡ ያጠቁ ፡ እንደነበረ ፡ ይነገራል።

ከዚህም ፡ የተነሣ ፡ ቀረርቱ ፡ ወይም ፡ ሽለላ ፉከራ ፡ ወይም ፡ ድንፋታ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ኅብረሰብ ፡ ውስጥ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ቦታ ፡ ይዘው ፡ ይገኛሉ። እነዚህም ፡ ግጥሞች ፡ ደፋርነትን ፡ ቆራጥነትን ፡ ልበ ፡ ሙሉነትንና ፡ ጀግንነትን ፡ በኢትዮጵያውያን ፡ ልብ ፡ ውስጥ ፡ የሚቀርጹ ፡ ናቸው። ቀረርቱ ፡ የሚሰማ ፡ ድንፋታ ፡ የሚያይ ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ ሁሉ ፡ ልበ ፡ ሙሉ ፡ ይሆናል ፡ ባላጋራውንም ፡ ከፊቱ ፡ ያየ ፡ ይመስል ፡ ጠጉሩ ፡ ይቆማል ፡ ደሙ ፡ ይፈላል። በተለይ ፡ የሚፎክረው ፡ ሰው ፡ ሲቅበጠበጥ ፡ ቁጭ ፡ ብድግ ፡ ሲል ፡ ለተመልካች ፡ የራበው ፡ አንበሳን ፡ ይመስላል። እልሁ ፡ ያነቀው ፡ ጀግና ፡ ጠላቱን ፡ ያገኘ ፡ ያህል ፡ ዓይኑን ፡ አፍጥጦ ፡ ወዲያና ፡ ወዲህ ፡ ሲንጐራደድ ፡ ከአራስ ፡ ነብር ፡ የበለጠ ፡ ያስፈራል። ፉከራ ፡ ለጀግኖች ፡ ኃይልን ፡ ይሰጣል ፡ ለፈሪዎች ፡ ሐሊናን ፡ እንዲገዙ ፡ ያደርጋል። በተለይም ፡ በገለሌ ፡ ውስጥ ፡ የሚገኙት ፡ ቃላት ፡ በጣም ፡ ወኔ ፡ የሚቀሰቅሱ ፡ በመሆናቸው ፡ ለፈሪው ፡ እንኳን ፡ ድፍረትን ፡ ይሰጣሉ ፡ ወጣቶችም ፡ ፡ ይህንን ፡ በአዩና ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፡ አባቶቻቸውን ፡ ለማኸል ፡ እንዲያውም ፡ ለመብለጥ ፡ ይጥራሉ ፡

ለማለት ፡ ያስደፍራል። አሁን ፡ ከፉከራዎቹ ፡ ውስጥ ፡ ጥቂቶቹን ለማስተዋወቅ ፡ ያህል ፡ ቀጥዬ ፡ አቅርቤአለሁ።

## ፉከራ።

አካኪ ፡ ዘራፍ አካኪ ፡ ዘራፍ ፡

ጭው ፡ ሲል ፡ ገዳይ ፡ ደጀን ፡ ሲላላ ፡
የጠቅል ፡ አሽከር ፡ የጠቅል ፡ ባላ።

ጐራዴ ፡ መዞ ፡ ሲሄድ ፡ ከቤቱ ፡
ወየው ፡ ሰው ፡ ፈጀ ፡ ኣለች ፡ እናቱ።

እንኳን ፡ እናቱ ፡ የወለደችው ፡
ኮራች ፡ ኣማቱ ፡ የተጋባችው።
በሰፊ ፡ አውድማ ፡ የተበጠረው ፡
ገለባው ፡ ሄዶ ፡ ምርቱ ፡ የቀረው።
ዘራፍ ፡ ሰው ፡ በሰው ፡
በደረሰበት ፡ ባፎቁ ፡ እሚያርሰው።

ሰንደቅ ፡ ዓላማው ፡ ኮከብ ፡ ሲመስል ፡
ነጋሪት ፡ አብጅር ፡ አብጅር ፡ ሲል ፡

መትረየስ ፡ ሲጮኽ ፡ መድፉ ፡ ሲያጓራ ፡
ደጀን ፡ ሲበተን ፡ ርሳስ ፡ ሲዘራ ፡
አጣድፎ ፡ ገዳይ ፡ በያዘው ፡ ጣምራ ፡
ባባቱ ፡ ወጥቷል ፡ ልጁም ፡ አይፈራ ፡
አንድ ፡ ለናቱ ፡ የሜዳ ፡ ጐራ።

ገዳይ ፡ ንጉሥ ፡ ሲቆጣ ፡
አይዞህ ፡ ባይ ፡ ቱኒ ፡ አፉ ፡ ሲነጣ ፡
ባለህ ፡ እርጋ ፡ ባይ ፡ ቡክን ፡ መድረሻ ፡ ሲያጣ።

ዘራፍ ፡ የተፈራ ፡ ጦር ፡ አጋጣሚ ፡
አፋ ፡ ቸምቻሚ ፡ ባለጅ ፡ አድካሚ ፡

አጪጪሂ ፡ በየጐራ ፡
ገትሮ ፡ ቋሚ ፡ እንደ ፡ ወጋግራ ፡
አባሮ ፡ ገዳይ ፡ ጋራ ፡ ለጋራ ፡
ሳያንቆበርር ፡ ሳያንጠራራ ፡
ከያዘም ፡ አይለቅ ፡ እንደ ፡ ዳሞትራ።

ሽምልምል ፡ ያለ ፡ እንደ ፡ ቀጭን ፡ ልብስ ፡
ባንድ ፡ ጊዜ ፡ ሲቃ ፡ አንጀት ፡ የሚያርስ።

ይምጡ ፡ ባይ ፡ ይሰብሰቡ ፡ ባይ ፡
እኒያ ፡ ሲመጡ ፡ አይበቁንም ፡ ባይ።

ዘራፍ ፡ ዘራፍ ፡ አካኪ ፡ ዘራፍ ፡

ንጉሡ ፡ ጠቅል ፡ አሸከሩ ፡ አንበሳ ፡
ብቅ ፡ አለ ፡ መጣ ፡ ያው ፡ እያገሳ።

ዝሆን ፡ ገዳይ ፡ ለጉትቻ ፡
አውራሪሥ ፡ ገዳይ ፡ ለመምቻ ፡
ጐሽ ፡ ገዳይ ፡ ለመመከቻ ፡
ጐፈር ፡ ገዳይ ፡ ለደጌቻ ፡
ጐበዝ ፡ ገዳይ ፡ ለቁትቻ።

## ፫ ፡ የጠበቆች ፡ ውርድ።

(ተጠየቅ ፡ ልጠይቅህ ፡ ተዘከረኝ ፡ ዳኛ ፡ ማርያም ፡ በላ ፡ ልበልህ ፡ ተጠየቅ ፡ ልጠይቅህ ፡ በላ ፡ ልበልሃ) የሚባሉትን ፡ ከመግለጻችን ፡ በፊት ፡ ስለጥንቱ ፡ የክስ ፡ አቀራረብና ፡ የዳኝነት ፡ አፈጻጸም ፡ ከሙሉ ፡ በከፊሉ ፡ ለማስረጃ ፡ ያህል ፡ የሚከተለውን ፡ ማብራሪያ ፡ እናቀርባለን።

አንድ ፡ ሰው ፡ ሌላውን ፡ ገንዘብ ፡ አለብህ ፡ ወይም ፡ መሬቴን ፡

ይዘህብኛል ፡ በማለትና ፡ በሌላም ፡ ይኸንን ፡ በመሳሰለ ፡ ክስ ፡ ለማቅረብ ፡ በአሰበ ፡ ጊዜ ፡ ለዳኛ ፡ ያመለክትና ፡ ተከሳሹ ፡ በቀላጤ ፡ እንዲጠራ ፡ ወይም ፡ በንጉሡ ፡ ስም ፡ ተፈጥሞ ፡ በዚህ ፡ ቀን ፡ እንድትቀርብ ፡ ተብለሃል ፡ ብሎ ፡ የዳኛውን ፡ ቃል ፡ ይነግረዋል። እንደዚሁም ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ባለዕዳውን ፡ በድንገት ፡ ያገኘው ፡ እንደሆነ ፡ ማንኛውንም ፡ መንገደኛ ፡ ከዳኛ ፡ አድርሰኝ ፡ ብሎ ፡ በንጉሡ ፡ ስም ፡ ያማጥነዋል ፡ መንገደኛውም ፡ ቁም ፡ ወዴት ፡ ትሄዳለህ ፡ በንጉሥ ፡ ሲሉት ፡ እንኳን ፡ ሰው ፡ ውሃ ፡ ይቆማል ፡ ይልና ፡ በቀጥታ ፡ ወደቀበሌው ፡ ዳኛ ፡ እንዲሔዱ ፡ ያፈጠጥማቸዋል ፡ ወይም ፡ ራሱ ፡ ያደርሳቸዋል ፡ ይህም ፡ ሰው ፡ የውሃ ፡ ወራጅ ፡ ዳኛ ፡ ይባላል ፡ ዳኛውም ፡ ዋስና ፡ እማኝ ፡ ይዘው ፡ እንዲቀርቡ ፡ ይቀጥራቸዋል።

ከላይ ፡ በተገለጸው ፡ ጥሪ ፡ መሠረት ፡ ከዳኛ ፡ ሲቀርቡ ፡ ከሳሽና ፡ ተከሳሽ ፡ የሥርዓት ፡ ዋስ ፡ ይጠራሉ ፡ ክርክሩ ፡ ሊሰማ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓቱ ፡ የተሟላ ፡ ሆኖ ፡ ሲገኝ ፡ ከሳሽ ፡ እግዚአብሔር ፡ ያሳይዎ ፡ በማለት ፡ ለቀረበበት ፡ ክስ ፡ መልስ ፡ ይሰጣል ፡ ባልተስማሙ ፡ ጊዜ ፡ ከሳሽ ፡ እንዳለብህ ፡ እንደሰጠሁህ ፡ ወይም ፡ እንደወሰድክብኝ ፡ በቅሎ ፡ እሰጥ ፡ ሲለው ፡ ሌላውየለብኝም ፡ አልሰጠኸኝም ፡ ለበቅሎህ ፡ አገባ ፡ ይለዋል ፡ ተከሳሽ ፡ ከዶ ፡ ከሳሽ ፡ በቅሎ ፡ እሰጥ ፡ በማለት ፡ ውርርድ ፡ ከተከለ ፡ በኋላ ፡ እረታለሁ ፡ የማለት ፡ ጥርጣሬ ፡ ያለው ፡ እንደሆነ ፡ ውርርድህን ፡ ዝቅ ፡ አድርግልኝ ፡ ሲለው ፡ ፈረስ ፡ እሰጥ ፡ በማለት ፡ ይለውጣል። አሁንም ፡ ዝቅ ፡ አድርግ ፡ ሲለው ፡ ውርርዱን ፡ በማር ፡ ይለውጥለትና ፡ አገባ ፡ ብሎ ፡ ሲመሰከርበት ፡ ይረታል ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ተከሳሹ ፡ አጉራህ ፡ ጠናኝ ፡ በማለት ፡ ክሱን ፡ ከአመነ ፡ «በአጉራህ ፡ ጠናኝ ፡ የተረታ ፡ ማህል ፡ አገዳውን ፡ የተመታ» ፡ እንደሚባለው ፡ ሁሉ ፡ የመጨረሻ ፡ እርት ፡ ይሆናል።

በዘመኑ ፡ በአጉራህ ፡ ጠናኝ ፡ የተፈጸመ ፡ ክርክር ፡ ዛሬ ፡ በሽምግልና ፡ ዳኝነት ፡ እንዳለቀ ፡ ስምምነት ፡ ይግባኝ ፡ የሌለው ፡ ነገር ፡ መደምደሚያ ፡ ነበር ፡ ለተካደው ፡ ክርክር ፡ በቅሎ ፡ ወይም ፡ ማር ፡ እሰጥ ፡ አገባ ፡ ተባብለው ፡ ከሦስት ፡ ያላነሱ ፡ ምስክሮች ፡ ይቆጠሩና ፡ ወዲያው ፡ ቃላቸውን ፡ እንዲሰጡ ፡ ይደረጋል። እቦታው ፡ ላይ ፡ ከሌሉ ፡ ግን ፡ የዳኛው ፡ መልእክተኛ ፡ ወይም ፡ ተከራካሪዎቹ ፡ የመረጡት ፡ ሰው ፡ ጭብጡን ፡ ተቀብሎ ፡ ምስክሮቹ ፡ ወዳሉበት ፡ ሔዶ ፡ ሁለቱም ፡ ወገኖች ፡ ባሉበት ፡ ያመሳክራል ፡

በዚህም ፡ ጊዜ ፡ በሁለቱ ፡ ተከራካሪዎች ፡ የተመረጡ ፡ ዐራት ፡ እማኞች ፡ መኖር ፡ አለባቸው ፡ መልእክተኛው ፡ ትእዛዙን ፡ ከፈጸመ ፡ በኋላ ፡ የምስክሮቹን ፡ ድምጽ ፡ በቃሉ ፡ ይዞ ፡ እያንዳንዳቸው ፡ የተናገሩትን ፡ በየስማቸው ፡ ዘርዝሮ ፡ ለዳኛው ፡ ያስረዳል። ምስክሮቹ ፡ ከተናገሩት ፡ ቃል ፡ ውስጥ ፡ ያስቀረ ፡ ወይም ፡ የጨመረ ፡ እንደሆነ ፡ ቅር ፡ የተሰኘው ፡ ወገን ፡ ተዘከረኝ ፡ ዳኛ ፡ ማርያም ፡ እግዚአብሔር ፡ መዘከሪያ ፡ ልቦና ፡ መተላለፊያ ፡ ጐዳና ፡ ይስጥህ: አቶ ፡ ፡ እንደዚህ ፡ ብሎ ፡ የመሰከረ ፡ መሆኑን ፡ አስታውስ ፡ ይለዋል ፡ የተዘነጋው ፡ ነገር ፡ ቢኖር ፡ ያቃናል ፡ በቃሉ ፡ የጸና ፡ እንደሆነ ፡ ግን ፡ ተቃዋሚው ፡ የምስክሮቹን ፡ ቃል ፡ በማጣረሱ ፡ ሰድቤዋለሁና ፡ ምስክሩን ፡ የሰሙት ፡ እማኞች ፡ ይንቀሱልኝ ፡ ይላል ፡ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ እማኞቹ ፡ እንዴት ፡ እንደተመሰከረ ፡ ይጠየቃሉ ፡ እርሱ ፡ እዳለው ፡ ነው ፡ ብለው ፡ የመሰከሩ ፡ እንደሆነ ፡ ነቃፊው ፡ ኣመሳካሪውን ፡ ዳኛ ፡ ይክሳል ፡ አጓድሎ ፡ የተገኘ ፡ እንደሆነ ፡ ግን ፡ የምስክሮቹ ፡ ድምጽ ፡ እማኞቹ ፡ እንደተናገሩት ፡ ሆኖ ፡ ይጸናል ፡ ዳኛውም ፡ ይወቀሳል። ተከራካሪዎቹ ፡ የምስክሮቹን ፡ ቃል ፡ ለኔ ፡ ነገሩ ፡ ለኔ ፡ ነገሩ ፡ በማለት ፡ የተሻሙ ፡ እንደሆነ ፡ ለማን ፡ እንደመሰከሩ ፡ በእማኞች ፡ ይታደላል ፡ እማኞቹ ፡ የምስክሮቹ ፡ ድምጽ ፡ ለተከሳሹ ፡ ነው ፡ ብለው ፡ ቢአድሉም ፡ ዳኛው ፡ የምስክሮቹ ፡ ድምጽ ፡ ለካሳሽ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ለተከሳሽ ፡ አይደለም ፡ ካለ ፡ በእሱው ፡ ይጸናል ፡ በፍርድም ፡ ጊዜ ፡ እማኞቹም ፡ ሆነ ፡ ዳኛው ፡ የሚያደርጉት ፡ ቃለ ፡ መሐላ ፣

ይፍረድብኝ ፡ ይፈረድብኝ ፡
ባደላም ፡ ያድላብኝ ፡
በጌታዬ ፡ ጠላት ፡ ሠይፍ ፡ ሞት ፡ ይፈረድበት ፡
የራቀውን ፡ በመድፍ ፡ የቀረበውን ፡ በሰይፍ ፡
አርዶ ፡ ፈርዶ ፡ ይጣለው ፡ በሚል ፡ አነጋገር ፡ ነው።

በቀድሞው ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ክርክር ፡ ጊዜ ፡ እንደዛሬ ፡ ተከሳሹ ፡ በመከላከያ ፡ ምስክር ፡ የሚጠቀም ፡ አልነበረም ፡ ተከሳሽ ፡ ክስ ፡ ለቀረበበት ፡ ነገር ፡ ማስረዳት ፡ የሚገባኝ ፡ እኔ ፡ ነኝ ፡ እንጂ ፡ ከሳሽ ፡ አይደለም ፡ ብሎ ፡ በይገባል ፡ ይከራከራል ፡ ይህንንም ፡ የመሰለ ፡ ክርክር ፡ ሲቀጥል ፡ ተከራካሪው ፡ ራሱ ፡ ወይም ፡ ጠበቃው ፡ መጠየቅ ፡ እንዲፈቀድለት ፡

ያመለክታል ፡ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ አንዱ ፡ ወገን ፡ ጥያቄ ፡ ካመጣህ ፡ በጠበቃዬ ፡ ይላል ፡ በጥይቅ ፡ ጊዜ ፡ አንዱ ፡ ወገን ፡ ጠበቃ ፡ ባይኖረውም ፡ ጠበቃዬን ፡ ይዤ ፡ ወይም ፡ ጨምሬ ፡ ለማለት ፡ ሙብት ፡ ስላለው ፡ ለስምንት ፡ ቀን ፡ ይቀጠራል ፡ በተወሰነው ፡ ቀን ፡ ክርክሩ ፡ በጥያቄና ፡ መልስ ፡ እንዲቀጥል ፡ ከሳሽ ፡ ተጠየቅ ፡ ይልና ፡ አንድ ፡ ስጠይቅህ ፡ አንድ ፡ ሁለት ፡ ስሰጥህ ፡ ሁለት ፡ መልስልኝ ፡ ከዚህ ፡ እንዳትዛነፍ ፡ ማር ፡ ያግድህ ፡ ይለዋል ፡ ባላጋራውም ፡ በመጠንቀቅ ፡ ለጥያቄው ፡ ብቻ ፡ መልስ ፡ ይሰጣል ፡ ተረፍረፍ ፡ አድርጐ ፡ የመለሰ ፡ እንደሆን ፡ አጣርሷል ፡ ለማሩ ፡ ዋስ ፡ ይባል ፡ ይለዋል ፡ ማጣረሱንም ፡ ቢያምን ፡ የማር ፡ ዳኝነቱን ፡ ይከፍላል ፡ ከተወሰነው ፡ ጥያቄ ፡ አልወጣሁም ፡ ቢል ፡ እማኞች ፡ አጣርሷል ፡ አላጣረሰም ፡ ብለው ፡ ይመሰክራሉ ፡ ከሳሽ ፡ ጥያቄውን ፡ ሲጨርስ ፡ ተከሳሹ ፡ ደግሞ ፡ የተራውን ፡ ጥያቄ ፡ ይቀጥላል።

በቀድሞ ፡ ዘመን ፡ በነበረው ፡ የዳኝነት ፡ አመራር ፡ ዛሬ ፡ በምስክር ፡ ጥያቄ ፡ ላይ ፡ ጥቅምና ፡ ጉዳት ፡ እንዳለ ፡ ሁሉ ፡ በተጠየቅም ፡ ለክሩክር ፡ መፍቻ ፡ የሚሆን ፡ መረጃ ፡ ይገኝለት ፡ ነበር ፡ እንዲያውም ፡ አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ በተጠየቅ ፡ ብቻ ፡ የመጨረሻ ፡ ውሳኔ ፡ የሚያሰጥ ፡ እምነት ፡ ይገኝበት ፡ ነበር።

መጠየቁ ፡ ካለቀ ፡ በኋላ ፡ ሁለቱም ፡ የይገባል ፡ ውድር ፡ ያደርጋሉ ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜም ፡ አንደኛው ፡ ወገን ፡ የኔ ፡ ቀዘቀዘኝ ፡ ያንተ ፡ ሞቀኝ ፡ ለማርህ ፡ አገባ ፡ ብሎ ፡ በአንደኛው ፡ ውርርድ ፡ አቅጣጫ ፡ ብቻ ፡ ክርክሩ ፡ ይቀጥላል ፡ ሁለቱም ፡ በይገባል ፡ የተወዳደሩ ፡ እንደሆነ ፡ ከሳሽ ፡ ዳኛውን ፡ በማሞገስ ፡ የባላጋራውን ፡ ነውሩን ፡ በዘሩ ፡ ጭምር ፡ ያለበትን ፡ በመዘርዘር ፡ በሾርኔ ፡ እየሰደበ ፡ የተቀማጬን ፡ ሃሳብ ፡ ወደርሱ ፡ ለመሳብ ፡ ነገሩን ፡ በሚመስል ፡ ሁናቴ ፡ እያብራራ ፡ በግጥም ፡ እያደረገ ፡ ምሳሌ ፡ እየሰጠ ፡ ውርድ ፡ ይነዛል ፡ ወይም ፡ የማስረጃ ፡ ቃሉን ፡ ይሰጣል። መልስ ፡ ሰጭውም ፡ በተራው ፡ በዚህ ፡ ዓይነት ፡ መንገድ ፡ ለተከራካሪው ፡ ተገቢውን ፡ ይመልስለታል።

የውርድ ፡ አነዛዙም ፡ እንደሚከተለው ፡ ነው።
በላ ፡ ልበልሃ ፡ የአጤ ፡ ሥርዓቱን ፡ የአብርሃም ፡ ራቱን ፡ የሙሠ
ረቱን ፡ ኣልናገርም ፡ ሐሰቱን ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ እውነት ፡ እውነቱን ፡

ከ ....................ወዲያ ፡ ዳኛ ፡
ከ ....................ወዲያ ፡ ዘንገኛ ፡
አይፈጠርም ፡ ዳግመኛ።

....................የፈረደው ፡
የአዳል ፡ ዱቢት ፡ ያረደው ፡
የፈረደው ፡ አይገለበጥ ፡
ያረደው ፡ አይንፈራገጥ።
እሰጥ ፡ ብዬ ፡ ማር ፡ ጥዬ ፡
ከእግር ፡ ዘንጥዬ ፡
ባለማ ፡ ፍረዱኝ ባጠፋ ፡ ስደዱኝ ፡ ሲል ፡ ይሚገታል ፡
አፈ ፡ ማሩ ፡ ነገረ ፡ ደማሙ።
አንደኛው ፡ ወገን ፡ ደግሞ ፡ በዚሁ ፡ ዓይነት ፡ በላ ፡ ልበልህ ፡ በማ
ለት ፡ ይቀጥልና ፡

ጠራን ፡ ለጌኛ ፡ሙግትን ፡ ላፍለኛ ፡
አንተ ፡ በቅቶሃል ፡ ልቀቅ ፡ ለኛ ፡ ይለዋል።

ውርድ ፡ መንዛት ፡ ማለትም ፡ በጥያቄው ፡ ጊዜ ያስተማመነውንና ፡ ከቃሉ ያገኘውን ፡ መልስ ፡ ለክርክሩ ፡ እንዲደግፈው ፡ የሚያብራራበትና ፡ የራሱን ፡ ቀጥተኛነትና ፡ እውነተኛነት ፡ የሚገልጥበት ፡ ነው። ይህም ፡ ዛሬ ፡ ለውሳኔ ፡ በደረሰ ፡ ነገር ፡ ላይ ፡ የፍርድ ፡ ማብራሪያ ፡ እንደሚሰጠው ፡ ያለ ፡ ዓይነት ፡ ነው።

## ፬ ፡ የደስታና ፡ የሐዘን ፡ ግጥም።

ከሕዝባችን ፡ መካከል ፡ አብዛኛው ፡ የሙዚቃን ፡ ስሜትና ፡ ጣዕም ፡ ለይቶ ፡ ያወቀ ፡ ነው ፡ ግጥም ፡ ወይም ፡ ዘፈን ፡ ብለን ፡ የምንጠራው ፡ ምርጥ ፡ የሆኑ ፡ ቃላትን ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ስልት ፡ በማዜም ፡ የደስታችንም ፡ ሆነ ፡ የሐዘናችንን ፡ ስሜት ፡ የምንገልጥበትን ፡ ሁናቴ ፡ ነው። ግጥም ፡ በጠቅላላ ፡ አነጋገር ፡ መንፈስን ፡ ቀስቅሶና ፡ አነቃቅቶ ፡ ስሜትን ፡ የሚያዳብር ፡ ኃይለ ፡ ቃል ፡ ነው። ስለዚህም ፡ የሀገራችን ፡ ሰው ፡ ዘፈንን ፡ በባህሉ ፡ ውስጥ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ቦታ ፡ አስይዞታል ፡ የሚበልጠውን ፡ ጊዜ ፡ ጀግንነቱን ፡ በቀረርቱና ፡ በድንፋታ ፡ ደስታውን ፡ በዘፈን ፡ ሐዘኑን ፡ በሙሾ ፡ ይገልጣል። ከዚህም

፡ በተቀር ፡ ገበሬዎች ፡ በማኅበር ፡ በሚሠሩበት ፡ ጊዜ ፡ ድካማቸውን ፡ በግጥም ፡ ያቃልላሉ ፡ እረኞች ፡ ከብቶቻቸውን ፡ በሚጠብቁበት ፡ ወቅት ፡ ብቸኝነት ፡ እንዳይሰማቸውና ፡ ቀኑ ፡ እንዳይረዝምባቸው ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ግጥሞችን ፡ ያሰማሉ ፡ ምዕመናን ፡ በግጥም ፡ ለአምላክ ፡ ምሥጋና ፡ ያቀርባሉ ፡ ደሆች ፡ በዜማ ፡ ይለምናሉ ፡ የዘፈን ፡ ዓይነቶች ፡ ከላይ ፡ እንደገለጽኩት ፡ ብዙ ፡ ቢሆንም ፡ ለምሳሌ ፡ ያህል ፡ ከያንዳንዱ ፡ ከፍል ፡ ምርጥ ፡ ምርጥ ፡ የሆኑትን ፡ በየአርዕስቱ ፡ እየለየሁ ፡ ቀጥዬ ፡ ጽፌአቸዋለሁ።

## ፬-ሀ የሠርግ ፡ ዘፈን።

የሠርግ ፡ ዘፈን ፡ በየጠቅላይ ፡ ግዛቱና ፡ በየአውራጃው ፡ ይለያያል ፡ ቢሆንም ፡ ሙሽሮችን ፡ የሚያሞግስ ፡ ደስታቸውንም ፡ የሚገልጽ ፡ የትዳርን ፡ ከባድነትና ፡ የኑሮን ፡ አስቸጋሪነት ፡ ከአለው ፡ ኃላፊነት ፡ ጋር ፡ የሚያስገነዝብ ፡ ሆኖ ፡ ይገኛል።

ግጥሙ ፡ የሠርጉን ፡ ትርዕይት ፡ በቅደም ፡ ተከተል ፡ ይዘረዝራል ፡ የሙሽራውንና ፡ የሙሽራዩቱን ፡ ውበት ፡ ያሞግሳል ፡ አልፎ ፡ አልፎ ፡ ሚዜዎቹን ፡ ይወቅሳል ፡ ሚስቲቱ ፡ ባሏን ፡ ሳታስቀይም ፡ አክብራ ፡ እንድትይዝ ፡ እንዲሁም ፡ ባልዮው ለሚስቱ ፡ የሚያስፈልጋትን ፡ ሁሉ ፡ እንዲያደርግ ፡ በምሥጢር-ለበስ ፡ ግጥም ፡ ይመክራል። አንዳንድ ፡ ጊዜም ፡ የሙሽሮቹን ፡ ዘርና ፡ ወገን ፡ ሀብትና ፡ ባልትና ፡ ያወሳል ፡ ለማስረጃም ፡ ያህል ፡ ከዚህ ፡ በታች ፡ ያለውን ፡ እንመልከት።

| የዘፈኑ ፡ አውራጅ ፡ | የዘፈኑ ፡ ተቀባዮች ፡ | የተነገረበት፡ ዓላማ፡ |
|---|---|---|
| አጀባዬ ፡ | እኸ | ወደ ፡ ሙሽራይቱ ፡ |
| ኣጀባዬ ፡ | በተቀባዮቹ የሚደጋገም ፡ ቃል፡ | ቤት ፡ ሲያመራ ፡ |

ኣጀባ ፡ ነው ፡ ፈረሱ ፡
ወዴት ፡ ነው ፡ እሱ።

ኣጀባዬ ፡
አጀባዬ ፡

አጀባ ፡ ነው ፡ ጭብጨባ ፡
በየት ፡ ሊገባ።

አጀባዬ።
አጀባዬ ፡

አጀባ ፡ ነው ፡ ግርግርታ ፡
ግባ ፡ አታመንታ።

ጡረው ፡ ጡረው ፡ አማላጅህን ፡
ጡረው ፡ ጡረው ፡ አማላጅህን ፡
ጡረው ፡ አማላጅህን።

ሙሽራው ፡ ወደቤት ፡ ሲገባ ፡

አንተ ፡ አገኘህ ፡ አገኘህ ፡ ድል ፡
የጨዋ ፡ ልጅ ፡ የድልድል ፡
አንተ ፡ አገኘህ ፡ ድል።

ወሰው ፡ ወሰው ፡ ወሰው ፡ ጋብቻ ፡
ወሰው ፡ ጋብቻ ፡
ይበቃሐል ፡ የናቷ ፡ ብቻ።

እምም ፡ አለች ፡ ምድር ፡
እምም ፡ አለች ፡ ምድር ፡
አቶ ፡ ፡ ልጁን ፡ ሲድር።

ሙሽራው ፡ ገብቶ ፡ ከሽማግሌዎቹ ፡
ፊት ፡ በቆመ ፡ ጊዜ ፡

ሽቦዬ ፡ ሎጋው ፡ ሽቦዬ ፡
ሽቦ ፡ አመጣው ፡ ስቦ ፡

ሀይ ፡ ሀይ ፡ ሎጋው ፡ ሽቦዬ ፡

ሙሽራዪቱን ፡ ተረከቦ
፡ ሲወጣ ፡

አድባር ፡ ትቀበልሺ ፡
ሌላ ፡ ምን ፡ እንበልሺ።

አድባር ፡ ትቀበልሽ ፡

የሙሽራዬቱ ፡ ቤተ ፡ ሰቦች ፡
ሲሸኙ ፡

ሸኘቼ ፡ መጣሁ ፡ ሸኘቼ ፡
ትንሽቱን ፡ መልሼ ፡

ሸኘቼ ፡ መጣሁ ፡ ሸኘቼ ፡

ትልቂቱን : ሸኘቼ።

ወንድምዬ :
ወንድም : አበባ :
ይዘህ : በጊዜ : ግባ።

እሺ
በሙሉ : በመመለስ

ሙሽራው : ወደ : ቤቱ :
አካባቢ : ሲደርስ : የሱ :
ቤተሰቦች : የሚሉት :

ወንድምዬ :
ወንድም : ደስ : ደስ :
ይዘህ : በቶሎ : ድረስ።

እሺ
በሙሉ : በመመለስ :

ዘራፍ : አባቷ : ጨዋ : ሸንገሎ : አስታራቂ :
እናቷ ባልቴት : እንዝርት : አራቂ :
ወንድሟ : ጨዋ : በሩን : አጥባቂ :
እሷ : ጨዋ : ልጅ : ሕጓን : ጠባቂ።

የምሥራች : ባዮቹ :
ለዕድ መኞቹ : የሚገልጹት :

ጫጉላሽ : አብቧል : ዛሬ :
ጫጉላሽ : አብቧል : ዛሬ :
እድልሽ : ዛሬ : ነው : ዛሬ :
አዱኛሽ : ዛሬ : ነው : ዛሬ :
እቴ : ሸንኮሬ : ጫጉላሽ : አብቧል : ዛሬ።

እሽሽ : እቴ : ሸንኮሬ :

ብር : አምባር : ሰበረልዎ :
ብር : አምባር : ሰበረልዎ :
ብር : አምባር : ስብርብር :
ብር : አምባር : ስብርብር :

እሺ : እሺ : ወንዱ : ልጅዎ :
እሺ : እሺ :

ሚዜዎቹ : ወደ : ሙሽራው :
እናት : በቀረቡ : ጊዜ :

እሽሽ : ጥንት : የነበረ :
ኬላው : ተሰበረ።

## ፬-ለ የየዓውደ : ዓመቱ : ዘፈን።

የኢትዮጵያ : ሕዝብ : ለዕንቁጣጣሽ : ለመስቀል : ለገና : እና : ለፋሲካ : በየአደባባዩና : በየመስኩ : ለበዓላቱ : ነክ : የሆኑትን : ዘፈኖች : በማዜም

፡ ደስታውን ፡ ይገልጻል። የግጥሞቹም ፡ ምሥጢር ፡ ጊዜውን ፡ የሚከተል ፡ ነው ፡ ለምሳሌ ፡ መስከረም ፡ ለምለም ፡ የሚታይበትና ፡ ምድር ፡ በአበባ ፡ የምትሸፈንበት ፡ ወቅት ፡ በመሆኑ ፡ ለዕንቁጣጣሽ ፡ የሚደረገው ፡ ዘፈን ፡ ልምላሜን ፡ በሚያደንቁ ፡ ቃላት ፡ የተመሠረተ ፡ ነው። ዓውደ ፡ ዓመቶች ፡ በሀገራችን ፡ በታላቅ ፡ ክብር ፡ ይከበራሉ ፡ በእነዚህም ፡ ቀናት ፡ ሴቶችና ፡ ወንዶች ፡ የጸዳ ፡ የክት ፡ ልብሶቻቸውን ፡ ለብሰው ፡ በየአደባባዩ ፡ ሲጫወቱ ፡ ማየት ፡ እጅግ ፡ ያስደስታል። ሽማግሎችና ፡ ባልቴቶች ፡ ሕፃናትም ፡ ጭምር ፡ በዓውደ ፡ ዓመት ፡ ከቤት ፡ አይውሉም ፡ ምክንያቱም ፡ ከሰው ፡ የሚገናኙበትና ፡ የሚጫወቱት ፡ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ስለሆነ ፡ ነው። ሕዝቡ ፡ ድግስ ፡ እየደገሰ ፡ የሚገባበዝበትም ፡ እንደዚህ ፡ ያሉትን ፡ በዓላት ፡ ምክንያት ፡ እያደረገ ፡ ነው። ከላይ ፡ በአጭሩ ፡ ለገለጽነው ፡ ግጥሞቹ ፡ ራሳቸው ፡ አስረጅዎች ፡ ስለሆኑ ፡ ከዚህ ፡ በታች ፡ የጊዜውን ፡ ቅደም ፡ ተከተል ፡ በመጠበቅ ፡ የተጻፉትን ፡ መመልከት ፡ ይጠቅማል።

## ፩ የዕንቁጣጣሽ ፡ ዘፈን ፡ (የሴቶች)።

አበባዩ ፡ ሆይ ፡ ለምለም ፡ (ለምለም ፡ የሚለው ፡ ቃል ፡ በተቀባዮቹ ፡ ይደጋገማል) ።
ባልንጀሮቹ ፡ ቁሙ ፡ በተራ ፡
እንጨት ፡ ሰብሬ ፡ ቤት ፡ እስትሠራ ፡

እንኳን ፡ ቤትና ፡ የለኝም ፡ አጥር ፡
ከደጅ ፡ አድራለሁ ፡ ኮከብ ፡ ስቆጥር ፡

ኮከብ ፡ ቆጥሬ ፡ ስገባ ፡ ቤቴ ፡
ንፍሮ ፡ ቀቅዬ ፡ ብላ ፡ ብለው ፡
ጉልቻ ፡ አንስቶ ፡ ጐኔን ፡ አለው ፡

ከጐኔም ፡ ጐኔን ፡ ኩላሊቴን
እናቴን ፡ ጥሯት ፡ መድኃኒቴን ፡
እሷን ፡ ብታጡ ፡ መቀነቷን።

ከብረው ፡ ይቆዩኝ ፡ ከብረው ፡ (ሁሉም) ፡
ለዓመት ፡ ወንድ ፡ ልጅ ፡ ወልደው ፡
በመጋረጃ ፡ ውለው ፡
ሐምሳ ፡ ጥገቶች ፡ አስረው ፡
ከብረው ፡ ይቆዩኝ ፡ ከብረው።

## ሆያ ፡ ሆዬ ፡ (የቡሄ ፡ ዕለት የሚዘፈን) ።

ሆያ ፡ ሆዬ ፡ ናና ፡ በሥፌው ፡ ጐዳና ፡ (በተቀባዮቹ፡የሚደጋገም ቃል)
ድንጋይ ፡ ተቀብሮ ፡ አይበሰብስም ፡
አንዴ ፡ መጥተናል ፡ አንመለስም።

የኔማ ፡ እመቤት ፡ የፈተለችው:
የሸረሪት ፡ ድር ፡ አስመሰለችው ፡
ሸማኔ ፡ ጠፍቶ ፡ ማርያም ፡ ሠራችው ፡

ለዚያች ፡ ለማርያም ፡ እዘኑላት ፡
ዓመት ፡ ከመንፈቅ ፡ አለቀላት።

አሆ ፡ አሆዬ ፡ አሆ ፡ ኣሆዬ ፡

ያ ፡ የማን ፡ ነው ፡ ጋሻ ፡ ከመከታው ፡ ላይ ፡
የዚያ ፡ የየኔታ ፡ የጣምራው ፡ ነቃይ።

ያ ፡ የማን ፡ ነው ፡ እንዝርት ፡ በአገልግሉ ፡ ላይ ፡
የዚያች ፡ እመቤቴ ፡ የቀጭን ፡ ፈታይ።

ሆያ ሆዬ ፡ ጉዴ ብሯን ፡ ብሯን ፡ ይላል ፡ ሆዴ ፡
የኔ ፡ ጌታ ፡ ተው ፡ ስጠኝና ፡ ልሂድልህ ፡
እንደ ፡ አሮጌ ፡ ኾብ ፡ አልጩህብህ።

## ፪/ የመስቀል ፡ ዘፈን።

በቀደም ፡ መጥተን ፡ የለም ፡ አሉን ፡

ዛሬም ፡ መጥተናል ፡ ሆድ ፡ ሳይብሰን ፡

አሸከሩ ፡ መጣ ፡ የለም ፡ ሊለን ፡
ቸሩ ፡ ፈጣሪ ፡ አራራልን።

ወይ ፡ የኔ ፡ ጌታ ፡ ለጋ ፡ ጠንበለል ፡
ዝናሙ ፡ መጣ ፡ ወዴት ፡ ልጠለል ፡

ወይ ፡ የኔ ፡ ጌታ ፡ ወርካ ፡ ነው ፡ ወርካ ፡
ቢጠለሉበት ፡ የማያስነካ።

ከዳሳ ፡ ወዲያ ፡ ከመገዘዝ ፡
አንተን ፡ የሚያህል ፡ የለም ፡ ጐበዝ ፡

መጥቼ ፡ ነበር ፡ ዝና ፡ ሰምቼ ፡
የሰው ፡ በላይነህ ፡ ሲሉ ፡ ሰምቼ ፡

ብትሰጠኝ ፡ ስጠኝ ፡ ባትሰጠኝ ፡ እንዳሻህ ፡
ከጐረቤትህ ፡ ካነሰ ፡ ጋሻህ።

የኔማ ፡ ጌታ ፡ የሰጠኝ ፡ ሙክት ፡
በለጭማ ፡ ነው ፡ ባለምልክት ፡
መስከረም ፡ ጠባ ፡ እሱን ፡ ሳነክት።

(ከስጦታ ፡ በኋላ) ፡
ክበር ፡ በስንዴ ፡ ዝና ፡ ወዳዴ ፡
ክበር ፡ በጤፍ ፡ ምቀኛህ ፡ ይርገፍ።

## ፬-ሐ የማኅበራዊ ፡ ሥራ ፡ የደቦ ፡ ዘፈን።

የሀገራችን ፡ ሰው ፡ ብዙውን ፡ ጊዜ ፡ ሥራን ፡ በኅብረት ፡ መሥራት ፡ ይወዳል ፡ ይኸውም ፡ ደቦ ፡ ወይም ፡ ጅጊ ፡ እየተባለ ፡ ይጠራል። አንድ ፡ ሰው ፡ አንድ ፡ ሥራ ፡ ለመሥራት ፡ ብዙ ፡ ጉልበትና ፡ ጊዜ ፡ ስለሚጠይቀው ፡ ከሌሎቹ ፡ ሰዎች ፡ ጋር ፡ በመተባበር ፡ ለመሥራት ፡ ይፈልጋል ፡ ስለዚህም

፡ በአካባቢው ፡ ከሚገኙት ፡ ሰዎች ፡ ጋር ፡ ወንፈል ፡ በመግባት ፡ የግብርና ፡ ሥራውን ፡ ያከናውናል ፡ በቤትም ፡ ውስጥ ፡ ሴቶች ፡ ለጥጥ ፡ ሥራ ፡ ጅጌ ፡ ያደርጋሉ። በዚህ ፡ ጊዜም ፡ ለሠራተኞቹ ፡ ማስተናገጃ ፡ ድግስ ፡ ይሰናዳል። ሆኖም ፡ ከሀገሩ ፡ ዕድር ፡ ወይም ፡ ደንብ ፡ የወጣ ፡ መስተንግዶ ፡ አይዘጋጅም ፡ ምክንያቱም ፡ «ወይኖ ፡ አረሰው ፡ ወይኖ ፡ ጐረሰው» ፡ እንደሚባለው ፡ እንዳይሆን ፡ ነው።

በኅብረት ፡ እርሻውን ፡ አርሰው ፡ ዘሩን ፡ ሲዘሩ ፡ በመከር ፡ ወቅት ፡ ሰብሉን ፡ ሲሰበስቡና ፡ ሲወቁ ፡ ለማበረታታት ፡ ሲባል ፡ ከመሐከላቸው ፡ አንደኛው ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ግጥም ፡ ስልት ፡ ባለው ፡ ዜማ ፡ እያወረደ ፡ ሥራውን ፡ ያከናውናሉ። በሚጋበዙበትም ፡ ጊዜ ፡ በመዝናናት ፡ ደስታቸውን ፡ በሆታ ፡ ይገልጣሉ። ዘፈኖቹም ፡ እንደጊዜው ፡ ሁናቴ ፡ የግብርናን ፡ ሥራ ፡ በየመልኩ ፡ የሚያመለክቱ ፡ ናቸው። የሚሰጡትን ፡ ትርጉም ፡ አስተውለን ፡ ስንመረምር ፡ የሰው ፡ ልጅ ፡ ግብርናን ፡ የተለየ ፡ ሞያ ፡ አድርጐ ፡ መያዝ ፡ ያለበት ፡ መሆኑን ፡ በሬዎች ፡ ለገበሬዎች ፡ ታላቅ ፡ ረዳትና ፡ የሥራ ፡ ጓደኞች ፡ መሆናቸውን ፡ ሰብል ፡ በሥራው ፡ አድካሚ ፡ ቢሆንም ፡ ለሰው ፡ ሕይወት ፡ ጠቃሚነቱን ፡ እህል ፡ ያለው ፡ ፈርዛዛ ፡ ብር ፡ ያለው ፡ ቀበዝባዛ ፡ መሆኑን ፡ ሰነፎች ፡ ለመብል ፡ ሲገኙ ፡ ለሥራ ፡ መታጣታቸውን ፡ ... ይህንንና ፡ ይህን ፡ የመሳሰለውን ፡ ሁሉ ፡ እየዘረዘረ ፡ የሚያሞግስና ፡ የሚዘልፍ ፡ ነው። ከዚህም ፡ የምናገኘው ፡ ቁም ፡ ነገር ፡ የሰው ፡ እጅ ፡ ሳያዩ ፡ ሳይራቡ ፡ ሳይጠሙና ፡ ሳይታረዙ ፡ ለመኖር ፡ መሬትን ፡ አርሶ ፡ ራስን ፡ መቻል ፡ ይበልጣል ፡ የሚል ፡ ነው። እንግዲህ ፡ ከግጥሞቹ ፡ ውስጥ ፡ ጥቂቶቹን ፡ እንዘርዝራቸው።

### በአዝመራ ፡ ወቅት ፡ የሚዘፈን።

(የበሬውን ፡ ውለታ ፡ ስለመግለጥ) ፡

እሸሩሩ ፡ በርዬ ፡ እሸሩሩ ፡
አንተ ፡ በሠራኸው ፡ ይኖራል ፡ ሀገሩ ፡

በሬና ፡ ገበሬ ፡ ቢጣሉም ፡ አይበጅ ፡

እንዲያው ፡ ስተት ፡ ብሎ ፡ ይጠመዷል ፡ እንጂ።

በሬ ፡ የሌለው ፡ ሰው ፡ ማዕረግም ፡ ኣይደርሰው ፡
ከሸንጎም ፡ ቢወጣ ፡ ሰው ፡ አይዋሰው።

በሬ ፡ አንተን ፡ የጠላ ፡ ጐኔ ፡ አንተን ፡ የጠላ ፡
የገና ፡ የጥምቀት ፡ ይለምናል ፡ ጠላ።

ምነው ፡ በቅዳሜ ፡ ምነው ፡ በእሁድ ፡ ቢያርሱ ፡
ከባለጸጋ ፡ ቤት ፡ ከሚመላለሱ።

በርዬ ፡ በርታልኝ ፡ ትንፋሽህ ፡ ምንድነው ፡
ምርቱ ፡ ለኔ ፡ ቢሆን ፡ ገለባው ፡ ለአንተ ፡ ነው።

በርዬ ፡ ምሩቁ ፡ ምሩቁ ፡
አንተ ፡ ካልዞርክበት ፡ አይሰበር ፡ ምርቁ ፡
በዱላ ፡ ቢመቱ ፡ በመንሽ ፡ ቢደልቁ ፡

የበሬን ፡ ውለታ ፡ መጫወት ፡ ነው ፡ ማታ ፡
በሰፌ ፡ ገበታ ፡ በዋንጫ ፡ ጋጋታ።

## ፬-መ የአዳኞች ፡ ዘፈን።

ወትሮ ፡ አዳኝ ፡ ለአውሬ ፡ ግዳይ ፡ ወደበረሓ ፡ ሲሄድ ፡ ወኔውን 'በመቀስቀስ ፡ ብርታት ፡ ለመስጠትና ፡ በለስ ፡ ቀንቶት ፡ የተመኘውን ፡ ፈጽሞ ፡ በተመለሰ ፡ ጊዜ ፡ ለማሞገስ ፡ የሚደረግ ፡ ጨዋታ ፡ ነው ፡ ግጥሙም ፡ እንደአውሬው ፡ ዓይነትና ፡ እንደቁጥራቸው ፡ ብዛት ፡ የተለያየ ፡ ሆኖ ፡ ይገኛል። ገዳዩ ፡ እቤት ፡ ሲገባ ፡ ቤተ ፡ ዘመዶቹ ፡ ጐረቤቶቹና ፡ ባልንጀሮቹ ፡ ተሰብስበው ፡ በዓል ፡ በማድረግ ፡ በዘፈን ፡ ይቀበሉታል ፡ በዚህም ፡ ሁናቴ ፡ ገዳይነቱ ፡ በይፋ ፡ ይረጋገጣል ፡ ስለአገኘው ፡ ክብር ፡ ደግሞ ፡ የተለመደውን ፡ የአዳኞች ፡ ባህል ፡ ጠብቆ ፡ ቅቤ ፡ ይቀባል። ምንም ፡ እንኳን ፡ በአሁኑ ፡

ጊዜ ፡ ይህንን ፡ የመሰለው ፡ ሥራ ፡ ተፈላጊነት ፡ ባይኖረውም ፡ የተነቀፈውም ፡ ቢሆን ፡ ጥንት ፡ አባቶቻችን ትልቅ ፡ ሞያ ፡ አድርገው ፡ በመያዛቸው ፡ በዚሁ ፡ ክብርም ፡ ማዕረግም ፡ ዝናም ፡ ያገኙበት ፡ እንደነበረ ፡ አይዘነጋም። በአደን ፡ ሰዓት ፡ ይዘፈኑ ፡ ከነበሩት ፡ ግጥሞች ፡ ጥቂቶቹን ፡ ከዚህ ፡ በታች ፡ አቅርቤአለሁ።

ተኩሼ ፡ ሄደብኝ ፡ ብሎ ፡ ከማለቱ ፡
ቀረብ ፡ ብለህ ፡ ተኩስ ፡ ወርቅ ፡ ነው ፡ ብልቱ።

ምክንያት መስጠት ተገቢስላለመሆኑ ፡

ካፈ ፡ ሙዙ ፡ ዘቅዘቅ ፡ ከሰደፉ ፡ ቀና ፡
አበጀህ ፡ አበጀህ ፡ ሞት ፡ አይቀርምና።

የጠመንጃ አዴኃገንን ፡ ስለማድነቅ ፡

ዝሆን ፡ ብትገድል ፡ በጣም ፡ ደስ ፡ አለኝ ፡
አውራሪስ ፡ ብትገድል ፡ በጣም ፡ ደስ ፡ አለኝ ፡
ጐሽ ፡ ኮረምቱ ፡ ገድለህ ፡ ኮልባ ፡ ላክልኝ።

በዝሆን ግዳይ ፡ ላይ ፡ ጐሽ ፡ እንዲታከል ፡ ስለ ፡ መገፋፋትና ፡ ማበረታታት ፡

አንቺ ፡ ምን ፡ ቸገረሽ ፡ የገዳይ ፡ ውሽማ
አንተርሶሽ ፡ ያድራል ፡ አዶ ፡ እንደ ፡ በርኩማ።

እንኳን 'ሚስት' ውሽማ፡ በወዳጅዋ ግዳይ መኩራት ፡ ስለሚገባት ፡

አውራሪስ ፡ መታጠቅ ፡ እየገደሉ ፡ ነው።
ገዝቶማ ፡ መታጠቅ ፡ ነጋዴ ፡ መሆን ፡ ነው።

በገደሉት ፡ አውራሪስ ፡ የተዘጋጀ፡ ጐራዴ ፡ መታጠቅ ፡ ዋጋ ፡ ያለው ፡ ስለመሆኑ ፡

ቀጭን ፡ ኩታ ፡ መልበስ ፡ አምሮህ ፡ እንደሆን ፡
ቀጭኔ ፡ ተጋድለህ ፡ አምጣልን ፡ ጐድኗን።

ቀጭን ፡ ኩታ ፡ ለመልበስ፡ ያማረው ፡ ቀጭኔ ፡ መግደል ፡ እንደሚያስፈልገው ፡

እስቲ ፡ እንዳሻው ፡ ባቦ ፡ እንዳለው ፡ ያርገኝ ፡
በቀጭኔ ፡ ደጋን ፡ የሚያስነድፈኝ።
ምነዋ ፡ ብኮራ ፡ ምነው ፡ ቢጀንነኝ ፡

ክብር ፡ ለሚሰጥ ፡ ባል ፡ መገዛት ፡ስለመገባቱ የገዳይ ፡ ሚስት ፡ ሆኜ

| | |
|---|---|
| ቀጭኔ ፡ ተጋዳይ ፡ ያገኘሁ ፡ እኔ ፡ ነኝ። | ፡ መኩራት ፡ ይብዛብኝ? |
| ታስታውቃለች ፡ የገዳይ ፡ ገረድ ፡<br>ካልቀዳች ፡ አይቀዱ ፡ ውሃ ፡ እንኳን ፡ ብትወርድ። | ለገዳይ ፡ ገረድ ፡ ስለሚሰ ፡ ጣት ፡ ቅድሚያና ፡ ክብር ፡ |
| እንግዲህ ፡ ጀመረ ፡ ሊቀመጥ ፡ ሊነሣ ፡<br>አንድ ፡ ኤልሞሌ ፡ ገድሏል ፡ ያውም ፡ ለሠላሳ። | ነቀፋ |
| የገዳይ ፡ ኣጋዳይ ፡ ሆኖ ፡ ከመመለስ ፡<br>አልነበረኸም ፡ ወይ ፡ አፈ ፡ ሾሌ ፡ ፈረስ። | ግሣፄ |
| የገዳይ ፡ ነጋዳይ ፡ ሆኖ ፡ መቶልሻል ፡<br>ግባ ፡ በይው ፡ እንጂ ፡ ከደጅን ፡ ያመሻል። | ዘለፋ ፡ |

## ፬-ሠ የአረኞች ፡ ዘፈን።

እረኞች ፡ ከብት ፡ በሚጠብቁበት ፡ ጊዜ ፡ ቀኑ ፡ ረዝሞ ፡ እንዳይሰለቻቸው ፡ በአንድ ፡ ቦታ ፡ ላይ ፡ ይሰበሰቡና ፡ ይዘፍናሉ ፡ ግጥማቸውም ፡ የዘመኑን ፡ ሁናቴ ፡ የክፍሉን ፡ ገዥዎች ፡ ክፋትና ፡ ደግነት ማለት ፡ ርኅሩኅነትና ፡ ጨካኝነት ፡ የሚገልጽ ፡ ነው። ከዚህም ፡ በቀር ፡ ማዶ ፡ ለማዶ ፡ ሆነው ፡ በዜማ ፡ ቃል ፡ ይለዋወጣሉ ፡ በቀድሞ ፡ ዘመን ፡ ስለአንዳንድ ፡ ገዥዎች ፡ የሥራ ፡ አፈጻጸም ፡ ለማወቅ ፡ ሲፈለግ ፡ እረኞች ፡ ምን ፡ አሉ ፡ ተብሎ ፡ ይጠየቅ ፡ ነበር ፡ ይባላል። ከዚህም ፡ በቀር ፡ የወደፊቱን ፡ የጊዜ ፡ ሁናቴ ፡ ከእረኞች ፡ በሚደረሰው ፡ ግጥም ፡ ለመገመት ፡ ይቻል ፡ እንደነበረ ፡ ብዙ ፡ ሽማግሌዎች ፡ ያወጋሉ ፡ ምክንያቱም ፡ ከእረኞች ፡ አንደበት ፡ የሚወጣው ፡ ቃል ፡ እንደትንቢት ፡ እየሆነ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ደርሷል ፡ ተብሎ ፡ በመታመኑ ፡ ነው። ይህንንም ፡ «አረቦን» ፡ ይሉታል። ትርጉሙም ፡ ወደፊት ፡ የሚመጣውን ፡ አመልካች ፡ ወይም ፡ አብሣሪ ፡ ማለት ፡ ነው። እረኞች ፡ እንደዚህ ፡ ያለውን ፡ ትንቢት ፡ አቀፍ ፡ ግጥማቸውን ፡ የሚያሰሙት ፡ የተለየ ፡ ስልት ፡ ባለው ፡ ዜማ ፡ ነው ፡ በግጥማቸውና ፡ በትንቢታቸው ፡ የታወቁ ፡ ክፈለ ፡ ሀገሮች ፡ አልፎ ፡ አልፎ ፡ ይገኛሉ።

**ለምሳሌ ፡** ጠላት ፡ ሀገራችንን ፡ በወራሪነት ፡ ይዞ ፡ በነበረ ፡ ጊዜ ፡ እረኞች ፡ የዘፈኑትን ፡ ቀጥሎ ፡ ያለውን ፡ ብንመረምር ፡ በእውነትም ፡ ትንቢት ፡ ተናጋሪዎች ፡ መሆናቸውን ፡ ልንረዳው ፡ እንችላለን።

ኒኬሉም ፡ ያልቅና ፡
አርኩም ፡ ይሄድና ፡
ጠቅል ፡ ይመጣና ፡
ያስተዛዝበናል ፡ ይኸ ፡ ቀን ፡ ያልፍና።

## ፬-ረ የመንፈሳዊ ፡ ግጥም ፡ (የታቦት) ፡

ለአምላክ ፡ ለመላእክት ፡ ለሰማዕታት ፡ ለቅዱሳንና ፡ ለጻድቃን ፡ በየክብረ ፡ በዓሉ ፡ ከምዕመናኑ ፡ የሚደረግ ፡ ምሥጋና ፡ ነው። ግጥሙም ፡ የእግዚአራሔርን ፡ ታጋሽነት ፡ ከሃሊነት ፡ ርኅሩኅነት ፡ ቸርነት ፡ ዘርዝሮ ፡ ያስረዳል። ከዚህም ፡ ሌላ ፡ የመላእክትን ፡ ታዳጊነትና ፡ የቅዱሳንን ፡ ገድል ፡ ይገልጻል። እንዲሁም ፡ ሰው ፡ ምንም ፡ ቢደላውና ፡ ምኞቱ ፡ ተፈጽሞ ፡ በዓለም ፡ ላይ ፡ ሀብት ፡ በብዙ ፡ ቢያከማች ፡ በክብር ፡ ላይ ፡ ክብር ፡ ቢያገኝ ፡ በመጨረሻው ፡ አፈር ፡ መሆን ፡ እንደማይቀርለት ፡ ያስገነዝባል ፡ አምላካችን ፡ በርኅራሄውና ፡ በቸርነቱ ፡ ፍጡሩን ፡ እንዲጠብቅና ፡ እንዲታደግ ፡ የመማጸኛ ፡ ቃልም ፡ ይገኝበታል ፡ የታቦት ፡ ዘፈን ፡ ዓይነቱ ፡ የበዛ ፡ ቢሆንም ፡ ቅሉ ፡ ለምሳሌ ፡ ያህል ፡ ዋና ፡ ዋናዎቹ ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ የሚገኙት ፡ ናቸው።

## የታቦት ፡ ዘፈን።

### ፩ ፡ ስለ ፡ አማኑኤል።

ኸረ ፡ እሰይ ፡ አማኔል ፡ ኸረ ፡ እሰይ ፡ አማኔል ፡ ተቀባዮች። ይህነኑ ፡ በመመለስ

በምን ፡ አወቀበት ፡ በበሽታው ፡ ጠባይ ፡
ጠበሉን ፡ ከሥሩ ፡ ቤቱን ፡ ከፋፉ ፡ ላይ ፡

ኸረ ፡ እሰይ ፡ አማኑኤል ፡ ነገሠ ፡

ኸረ ፡ እሰይ ፡ አማኑኤል ፡ ነገሠ ፡
በወሰካ ፡ መጥቶ ፡ በእግሩ ፡ ገሥገሠ ፡

ለካ ፡ አንት ፡ ኑረሃል ፡ መድኃኒቴ ፡
ለካ ፡ አንት ፡ ኑረሃል ፡ አብነቴ ፡
በወሰራ ፡ ዶሮ ፡ ሲበረበር ፡ ቤቴ ፡

ውል ፡ ውል ፡ አለኝ ፡ ጠበሉ ፡ ውል ፡ ውል ፡ አለኝ ፡ አሸንዳው።

## ፪ ፡ ስለ ፡ እመቤታችን።

ነይ ፡ ነይ ፡ እምዬ ፡ ማርያም ፡ ተቀባዮች ይህነኑ ፡ በመመለስ ፡
ነይ ፡ ነይ ፡ እምዬ ፡ ማርያም ፡
በምትወጅው ፡ ልጅሽ ፡ በመድኃኔ ፡ ዓለም ፡

አንድ ፡ እፍኝ ፡ ሽንብራ ፡ አልያዝኩም ፡ ከቤቴ ፡
ስሟ ፡ ስንቅ ፡ ነው ፡ የእመቤቴ ፡
ስሟ ፡ ስንቅ ፡ ነው ፡ የእመቤቴ።

ማርያም ፡ ማርያም ፡ ሲሏት ፡ ስሟ ፡ እንኳን ፡ መጣሙ ፡
ቤዛ ፡ የሆነችው ፡ ለፍጥረት ፡ ዓለሙ ፡

እለምንሻለሁ ፡ እስከ ፡ ዘለዓለም ፡
የአማኑኤል ፡ እናት ፡ እምዬ ፡ ማርያም።

እለምንሻለሁ ፡ እስከ ፡ ጊዜ ፡ ሞቴ ፡
የፈጣሪዬ ፡ እናት ፡ ማርያም ፡ እመቤቴ። ተቀባዮች ፡ ይህነኑ ፡ ሰመመለስ

## ፫ ፡ ስለ ፡ ሚካኤልና ፡ ገብርኤል ፡

ታስምረኝ ፡ እንደሆን ፡ ቆሜልህ ፡ ልዋል ፡ ተቀባዮች ፡ ይህነኑ ፡ ሰመመለስ
የአምላክ ፡ ባለሟል ፡ ቅዱስ ፡ ሚካኤል።

እየው ፡ ወሮ ፡ ሲገባ ፡ የሚካኤል ፡ አጀባ ፡

እየው ፡ ሎሌው ፡ ሲያምር ፡ ሎሌው ፡ ሲያምር ፡ የሚካኤል ፡ ደብር ፡
እኔስ ፡ በሀገሬ ፡ ስንኳን ፡ ሰው ፡ ወፍ ፡ አለምዳለሁ ፡ ወፍ ፡ አለምዳለሁ ፡
ለገብርኤል ፡ ለመልአኩ ፡ አድሬአለሁ ፡

ያረፈርፍ ፡ ያረፈርፍ ፡ ወርቅ ፡ ያረፈርፍ ፡
የቅዱስ ፡ ገብርኤል ፡ የለምዱ ፡ ዘርፍ።

## ፬ ፡ ስለ ፡ አቡነ ፡ ገብረ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡

ኧረ ፡ እሰየው ፡ አባቴ ፡ እረ ፡ እሰየው ፡ መድኃኒቴ ፡ ተቀባዮች ፡ ይህነኑ ፡ በመመለስ

ገብረ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ አቡዬ ፡ ጻድቁ ፡
ገደል ፡ እንዳከርማ ፡ የሚሰነጥቁ ፡

ገብረ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ እንደኛው ፡ ሰው ፡ ናቸው ፡
ከድንጋይ ፡ ላይ ፡ ጠበል ፡ የፈለቀላቸው ፡
አንበሳና ፡ ነበር ፡ የሰገደላቸው።

## ፭ ፡ ስለ ፡ አቡነ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ተቀባዮች ፡

ታስምሩኝ ፡ እንደሆን ፡ ልምጣ ፡ በግንቦት ፡ ተቀባዮች ፡ ይህነኑ ፡ በመመለስ
እቴጌ ፡ ያለሁት ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡
ተክልዬ ፡ ተክልዬ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡
ሳንቃው ፡ መከፈቻው ፡ የሚካኤል ፡ ለት (ዕለት) ፡

## ፮ ፡ ስለ ፡ ቅዱስ ፡ ላሊበላ

ተይ ፡ ተይ ፡ ሥጋዬ ፡ ተመከሪ ፡ ተቀባዮች ፡ ይህነኑ ፡ በመመለስ
ተይ ፡ ሥጋዬ ፡ ተመከሪ ፡
አንዳንድ ፡ ቀን ፡ እንኳን ፡ ለነፍስሽ ፡ እደሪ።

ኧረ ፡ ተወኝ ፡ ተወኝ ፡ ነገ ፡ ባይ ፡
ኧረ ፡ ተወኝ ፡ ተወኝ ፡ ነገ ፡ ባይ ፡
ዕድሜህን ፡ ለከተህ ፡ አኑረሃል ፡ ዎይ።

ነፍሴን ፡ አልሰዳትም: በዋዛ ፡
ነፍሴን ፡ አልሰዳትም ፡ በዋዛ ፡
ላሊበላ ፡ ሄጄ ፡ ጠበቃ ፡ ሳልገዛ።

ኧረ ፡ እንደምን ፡ አድርጐ ፡ አነጸው ፡
ኧረ ፡ እንደምን ፡ አድርጐ ፡ ሠራው ፡
የመጥረቢያው ፡ እንኳን ፡ እጄታ ፡ የለው።

ዓይኔ ፡ ዓለም ፡ አየ ፡ እግሬ ፡ ደርሶ ፡
ዓይኔ ፡ ዓለም ፡ አየ ፡ እግሬ ፡ ደርሶ ፡

የድንጋይ ፡ ወጋግራ ፡ የድንጋይ ፡ ምሰሶ።

## ፬-ሰ የልመና ፡ ግጥም።

ድሆች ፡ የሰዎችን ፡ ልቡና ፡ ለማራራትና ፡ እጃቸውንም ፡ እንዲዘረጉላቸው ፡ ለማድረግ ፡ በሚለምኑበት ፡ ጊዜ ፡ አሳዛኝ ፡ በሆነ ፡ በለሰለሰና ፡ በረቀቀ ፡ ድምፅ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ግጥሞችን ፡ ያሰማሉ።

ከግጥሞቻቸውም ፡ ውስጥ ፡ ምሥጢራቸው ፡ ጥልቅ ፡ የሆኑ ፡ ብዙ ፡ ቃላት ፡ ይገኙባቸዋል ፡ አካለ ፡ ስንኩሎች ፡ ዓይነ ፡ ስውሮች ፡ ሕመምተኞችና ፡ ጠዋሪ ፡ የሌላቸው ፡ ሽማግሎች ፡ ልብን ፡ በሚያሳዝንና ፡ በሚነካ ፡ ሁናቴ ፡ የዓለምን ፡ ከንቱነት ፡ ያስገነዝባሉ።

ሰው ፡ ዛሬ ፡ መልአክ ፡ መስሎ ፡ ቢታይም ፡ ነገ ፡ አፈር ፡ ከመሆን ፡ አለመቅረቱን ፡ ያስረዳሉ ፡ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ የዚህ ፡ ዓለም ፡ ተድላና ፡ ደስታ ፡ ተካፋይ ፡ ባለመሆናቸው ፡ እያዘኑ ፡ በእነሱ ፡ ላይ ፡ የደረሰው ፡ መጥፎ ፡ ዕድል ፡ እንዳይገጥመን ፡ እንጠነቀቅ ፡ ዘንድ ፡ በአሳዛኝ ፡ ዜማና ፡ በተቃኑ ፡ ግጥሞች ፡ ይመክሩናል። ለምሳሌም ፡ ያህል ፡ ከዚህ ፡ በታች ፡ የተጻፉትን ፡ እንመልከት።

እንዴት ፡ አደራችሁ ፡ እንደምን ፡ አላችሁ ፡ (ዓይነ ፡ ስውር) ፡
እንዲሁ ፡ በመላ ፡
እናንተ ፡ በብርሃን ፡ እኔ ፡ በጨለማ።

ብርሃን ፡ አይደለም ፡ ወይ ፡ ለፍጥረት ፡ ዓለሙ ፡
ምነው ፡ ለኔ ፡ ብቻ ፡ ቀኑ ፡ መጨለሙ።

ዓይኔን ፡ ግምባር ፡ ያርገው ፡ ብላችሁ ፡ አትማሉ ፡
እጅግ ፡ ያስጨንቃል ፡ መሪ ፡ ማባበሉ።

ዓይኔን ፡ ግምባር ፡ ያርገው ፡ ብሎ ፡ ይምላል ፡ ሰው ፡
መሪ ፡ ማባበሉን ፡ እንደኔ ፡ ባይቀምሰው።

ከሁሉም ፡ ከሁሉም ፡ ዕውር ፡ ያሳዝናል ፡
እሜዳ ፡ ላይ ፡ ቆሞ ፡ ገደል ፡ ገባሁ ፡ ይላል።

ሥርቼ ፡ በበላሁ ፡ ነበረ ፡ ምኞቴ ፡
ብርሃኔ ፡ ተይዞ ፡ ቢሳነኝ ፡ ጉልበቴ ፡
አልቅሼ ፡ በላሁኝ ፡ እንደልጅነቴ።

እዩት ፡ እጇ ፡ ሞቶ ፡ እዩት ፡ እግሬ ፡ ሞቶ ፡ (እጅ ፡ እግሩንና ፡ አካሉን ፡ የተጐዳ)
ያስለፈልፈኛል ፡ ሆዴ ፡ ብቻ ፡ ቀርቶ ፡

መሞቱን ፡ ይሞታል ፡ ሁሉም ፡ ያዳም ፡ ልጅ ፡
በቁሙ ፡ መፍረሱ ፡ ያሳዝናል ፡ እንጅ።

እባክህ ፡ አምላኬ ፡ አለሁ ፡ አለሁ ፡ በለኝ ፡
ሆኛለሁ ፡ ገለባ ፡ ነፋስ ፡ የበተነኝ።

ረኃብ ፡ ጸንቶብኝ ፡ ስጮህ ፡ ወንድማችሁ ፡
ያንድዩ ፡ ወዳጆች ፡ አይጨክን ፡ ልባችሁ።

ስለማርያም ፡ ብሎ ፡ ሲለምን ፡ ደካማ ፡
የተማረ ፡ እኮ ፡ ነው ፡ ቃሉን ፡ የሚሰማ ፡

እናትና ፡ ልጁን ፡ ሁለቱን ፡ ያመነ ፡
እንኳንስ ፡ ሌላው ፡ ሰው ፡ በላዔ ፡ ሰብእ ፡ ዳነ።

መሬት ፡ አትቆጭ ፡ ቀስ ፡ ብዬ ፡ እረግጣለሁ ፡
አንቺ ፡ ላይ ፡ እኔ ፡ ሥር ፡ መሆኔን ፡ አውቃለሁ።

መሬት ፡ እረገጥኩሽ ፡ መልሼ ፡ መልሼ ፡
እንታረቃለን ፡ አከላቴን ፡ ክሼ።
ረገጡኝ ፡ ብለህ ፡ መሬት ፡ አትቆጣ
ሁሉ ፡ ረጋፊ ፡ ነው ፡ ልብሱን ፡ ቢያነጣጣ።

ጣል ፡ ጣል ፡ አርጉበት ፡ ከምጽዋቱ ፡ ለኔ ፡
አላሳዝንም ፡ ወይ ፡ እንዲህ ፡ በመሆኔ።

## ፬-ሸ የልቅሶ ፡ ግጥም።

በኢትዮጵያ ፡ አባት ፡ እናት ፡ ባል ፡ ሚስት ፡ ልጅ ፡ ዘመድ ፡ ወዳጅ ፡ በሞቱ ፡ ጊዜ ፡ በወላጆቻቸውና ፡ በወገኖቻቸው ፡ ዘንድ ፡ ብርቱ ፡ ኃዘን ፡

ይደረጋል።

በዚህ ፡ ምክንያት ፡ የተሰበሰበውንም ፡ ሕዝብ ፡ ጭምር ፡ ለማስለቀስ ፡ አልቃሽ ፡ የተባሉ ፡ ሰዎች ፡ ይጠራሉ። እነዚህም ፡ በቤት ፡ ወይም ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ከኃዘነተኞቹ ፡ መካከል ፡ ይቆሙና ፡ በምሳሌ ፡ የሞተው ፡ ወንድ ፡ ሲሆን ፡ ምስሉን ፡ ወይም ፡ ጌጡን ፡ ተራ ፡ በተራ ፡ እየያዙ ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ የኃዘን ፡ ዜማ ፡ ደግነቱን ፡ ሞያውን ፡ ከእሱ ፡ በፊት ፡ ያለፉትን ፡ ዘመዶቹን ፡ እንዲሁም ፡ የሚቱ ፡ ወገኖችም ፡ ባይሆኑ ፡ ቀድሞ ፡ የሞቱትን ፡ ነገሥታት ፡ መሳፍንት ፡ መኳንንት ፡ ጀግኖች ፡ ወይዛዝርት ፡ አንድ ፡ በአንድ ፡ ያነሣሉ ፡ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ብዙው ፡ ባለቁስል ፡ ሆኖ ፡ ስለሚገኝ ፡ ኃዘኑ ፡ የበለጠ ፡ ይጋጋልና ፡ ዕንባ ፡ ከሁሉም ፡ ዓይን ፡ ላይ ፡ በጐርፍ ፡ ሲወርድ ፡ ይታያል።

ከእንጉርጉሮቹም ፡ ውስጥ ፡ አንዳንዶቹን ፡ ብንመለከታቸው ፡ በእውነትም ፡ ልብ ፡ የሚነኩ ፡ ሆነው ፡ እናገኛቸዋለን።

<u>፩ ፡ ስለ ፡ ነገሥታት ፡ ሞት።</u>

*ዐጼ ፡ ምኒልክ ፡ ሲሞቱ ፡*
*ምነው ፡ አትሄዱ ፡ ከፍታቱ ፡*

*እናንተ ፡ ሰዎች ፡ ከፋታችሁ ፡*
*አለማስቀበራችሁ።*

**ሠ** ፡ ሰው ፡ ሞቶ ፡ ለምን ፡ ከልቅሶ ፡ አልደረሳችሁም ፡ እቀብር ፡ አልመጣችሁም? ።

**ወ** ፡ ተድላና ፡ ደስታ ፡ ያልተለያቸው ፡ የዓለም ፡ ማያ ፡ የነበሩ ፡ ዐጼ ፡ ምኒልክ ፡ ሞቱባችሁ ፡ ተቀበሩባችሁ።

*ጌታዬ ፡ ምኒልክ ፡ ጃኖ ፡ ኣለምንኹም ፡*

*በቅሎ ፡ አለምንኹም ፡*
*አምና ፡ ነበር ፡ እንጂ ፡ ዘንድሮስ ፡ የለኹም።*

**ሠ** ፡ ገንዘብ ፡ የነበረዎት ፡ አዱኛ ፡ የተረፈዎት ፡ አምና ፡ ነበር ፡ ዘንድሮስ ፡ ተቸግረዋል ፡ ለራስዎም ፡ አይበቃዎትም ፡ አልቋል።

**ወ** ፡ በሕይወተ ፡ *ሥጋ* ፡ የነበሩት ፡ አምና ፡ ነበር ፡ እንጂ ፡ ዘንድሮስ ፡ በዚህ

፡ ዓለም ፡ የሉም ፡ መሞትዎን ፡ ሕሊናችን ፡ አውቆታል፤ ልቦናችን ፡ ተረድቶታል።

*እስቲ ፡ ጠይቁልኝ ፡ ርቃ ፡ ሳትሄድ ፡*
*እቴጌ ፡ ምንትዋብ ፡ ሚስት ፡ ናት ፡ ገረድ።*

**ሠ ፡** ሚስት ፡ ወይስ ፡ ገረድ ፡ መሆኗን ፡ ርቃ ፡ ሳትሄድ ፡ አረጋግጣችሁ ፡ ጠይቁልኝ።
**ወ ፡** እህትም ፡ እናትም ፡ ገረድም ፡ ነበረች ፡ በአዛኝነቷ ፡ እንደ ፡ እናት ፡ በአገልግሎቷ ፡ እንደገረድ ፡ ናት።

## ፪ ፡ ስለ ፡ መሳፍንት ፡ ሞት።

*ይህ ፡ ሁሉ ፡ ሰዋስው ፡ ይህ ፡ ሁሉ ፡ ምሥጢር ፡*
*ቅኔ ፡ አንተ ፡ ጠፋህ ፡ ወይ ፡ መስፍነ ፡ ሐረር።*

**ሠ ፡** በሰዋስው ፡ በምሥጢር ፡ የሚያሙህ ፡ ለምንድነው ፡ የማይገባህ ፡ መስሏቸው ፡ ይሆን? የሰዋስው ፡ ጌታ ፡ የግዕዝ ፡ መምሕር ፡ መሆንክን ፡ አልተረዱትም? ቅኔ ፡ ከአንተ ፡ የተረፈ ፡ መሆኑን ፡ ማን ፡ በነገራቸው!
**ወ ፡** ለኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ቅን ፡ አሳቢ ፡ የነበርከው ፡ ልዑል ፡ መኰንን ፡ በሞት ፡ ተለየኸን ፡ ወይ ፡ ከዚህ ፡ ዓለም ፡ ጠፋህ ፡ ወይ።

## ፫ ፡ ስለ ፡ መኳንንት ፡ ሞት ፡

*የንጉሥ ፡ አሽከር ፡ ጠፍቶ ፡ ሲፈለግ ፡ ሌሊት ፡*
*ቀን ፡ ከተድላ ፡ ጋራ ፡ ሲሄድ ፡ አየሁት።*

**ሠ ፡** ንጉሡን ፡ ከድቶ ፡ ኮብልሎ ፡ የጠፋው ፡ አሽከር ፡ ሳይፈራ ፡ ቀን ፡ ከተድላ ፡ ጋር ፡ ሲሄድ ፡ አየሁት።
**ወ ፡** ተድላ ፡ ደስታ ፡ ማግኘት ፡ ዓለም ፡ ማየት ፡ እንደልብ ፡ መደሰት ፡ ከደጃዝማች ፡ ተድላ ፡ ጓሉ ፡ ጋራ ፡ አብሮ ፡ ቀረ ፡ እሳቸው ፡ ሲሞቱ ፡ ሁሉም ፡ ነገር ፡ እንዳልነበረ ፡ ሆነ።

## ፬ ፡ ስለ ፡ ወይዛዝርት ፡ ሞት

*አይታለብበት ፡ አይጮኽበት ፡ ላም ፡*
*ምነው ፡ እመጫቷን ፡ ከንፍሮ ፡ ገዳም።*

**ሠ ፡** ላም ፡ ከሌለበት ፡ ወተት ፡ ከማይገኝበት ፡ ላይ ፡ ለምን ፡ እመጫቷን ፡ አስቀመጧት? ።
**ወ ፡** በወሊድ ፡ የሞተችውን ፡ እመጫት ፡ እገዳም ፡ ቀበሯት።

*ወርቀ ፡ ዘቦ ፡ ግምጃ ፡ የሚገባትን ፡*
*በጨርቋ ፡ ቀበሯት ፡ ምንትዋብ ፡ ወሌን።*

**ሠ** ፡ በወርቀ ፡ ዘቦ ፡ ግምጃ ፡ መከፈን ፡ የሚገባትን ፡ ምንትዋብ ፡ ወሌን ፡ በመናኛ ፡ ጨርቅ ፡ ጠቅልለው ፡ ቀበሯት።
**ወ ፡** ምንትዋብ ፡ ወሌ ፡ ገና ፡ በወጣትነቷ ፡ ወጣት ፡ ሳለች ፡ ሞተች ፡ አሳዛኝ ፡ ቅስፈት ፡ ደረሰባት።

## ፰ ፡ ስለ ፡ ሚስት ፡ ባል ፡ ወንድም ፡ ልጅ ፡ ሞት።

*አራሲቱ ፡ ወተት ፡ ጠጪ ፡ ይሻልሻል ፡*
*-አልቦ ፡ ይዞ ፡ ባልሽ ያስፈርድብሻል።*

**ሠ** ወተት ፡ አልቦ ፡ አምጥቶልሻል ፡ ጠጪ ፡ ይደግፍሻል ፡ እንደ ሴት ፡ አዘጋጅቶ ፡ ባልሽ ፡ ያመጣልሽን ፡ እንቢ ፡ ማለት ፡ ጡር ፡ ይሆንብሻል።
**ወ** ፡ ባልሽ ፡ የእግር ፡ አልቦሽን ፡ ይዞ ፡ ዘመድ ፡ አዝማድሽን ፡ ያስለቅሳል።

*ገብስ ፡ አርሚ ፡ ሲለኝ ፡ ልቤ ፡ እየታከተ ፡*
*ጤፍ ፡ አርሚ ፡ ሲለኝ ፡ ልቤ ፡ እየታከተ ፡*
*ነዶ ፡ አግዢ ፡ ሲለኝ ፡ ልቤ ፡ እየታከተ ፡*
*-እንግዲህ ፡ ልረፈው ፡ መከር ፡ ተከተተ።*

**ሠ** ፡ አረም ፡ ከማረም ፡ ነዶ ፡ ከመሸከም ፡ አረፍሁ ፡ መከር ፡ ተሰበሰበ ፡ አዝመራችን ፡ አልቆ ፡ በውጭ ፡ ያለው ፡ እኽል ፡ ሁሉ ፡ እጐተራ ፡ ገባ።
**ወ** ፡ ሥራ ፡ ሲያዘኝ ፡ ይሰለቸኝ ፡ የነበረው ፡ ትጉሁ ፡ ባሌ ፡ ሞተ ፡ መቃብር ፡ ገባ ፡ ብቻዬን ፡ ቀረሁ።

*አሞራው ፡ ንገረኝ ፡ ላልቅሰለት ፡ እቱ ፡*
*ባለሟሉ ፡ አንተ ፡ ነህ ፡ የበላህ ፡ ከፊቱ።*

**ሠ** ፡ ከፊቱ ፡ ቀርበህ ፡ ትበላ ፡ የነበርከው ፡ ባለሟሉ ፡ አንተ ፡ ነህ ፡ አንተ ፡

የማታውቀው ፡ ነገር ፡ የለም ፡ ወንድሜ ፡ የሆነውን ፡ ንገረኝና ፡ ላልቅስለት።

**ወ** ፡ የወንድሜን ፡ ፊት ፡ የዘነተርህ ፡ በጥፍርህ ፡ እየቧጠጥህ ፡ የበላኸው ፡ አሞራው ፡ አንተ ፡ ነህ።

*ይማርልኝ ፡ ብዬ ፡ በጌምድር ፡ ሰድጄ ፡*
*ቀለም ፡ ገባው ፡ አሉ ፡ እሳት ፡ ሆነ ፡ ልጄ ፡*

**ሠ** ፡ ልጄ ፡ ቀለም ፡ ይቀበላል ፡ ትምህርት ፡ ይገባዋል ፡ እሳት ፡ ሆኗል ፡ አሉ።
**ወ** ፡ ለትምህርት ፡ በጌምድር ፡ የሄደው ፡ ልጄ ፡ በእሳት ፡ ተቃጠለ ፡ በሕይወቱ ፡ ነደደ።

## ለ ፡ ኃይልንና ፡ ልምድን ፡ ማሰላሰልንና ፡ ቅልጥፍናን ፡ የተፈጥሮ ፡ ስጦታን ፡ ወይም ፡ ዝንባሌን ፡ የሚጠይቁ ፡ ባ ህ ሎ ች።

በዚህ ፡ ክፍል ፡ ከሚጠቀሱት ፡ ጨዋታዎች ፡ ውስጥ ፡ አንዳንዶቹ ፡ ከማሰላሰል ፡ ጋራ ፡ በጣት ፡ ቅልጥፍናና ፡ ፈጣንነት ፡ የሚከናወኑ ፡ ናቸው። አንዳንዶቹ ፡ ደግሞ ፡ የተፈጥሮ ፡ ስጦታን ፡ ወይም ፡ ዝንባሌን ፡ ይጠይቃሉ ፡ እነዚህንም ፡ ለመጫወት ፡ ምን ፡ ዓይነት ፡ ማሰብና ፡ መመራመር ፡ እንደሚያሻ ፡ የሚያስገኙትን ፡ ጥቅም ፡ ጭምር ፡ በዝርዝር ፡ ማወቁ ፡ ጠቃሚ ፡ ይሆናል ፡ ስለዚህም ፡ እያንዳንዱ ፡ አርዕስተ ፡ ነገር ፡ መጽሐፍ ፡ ለመጻፍ ፡ በቂ ፡ መነሻ ፡ ለመሆን ፡ ስለሚችል ፡ አጥኚዎችና ፡ ተመራማሪዎች ፡ በዚህ ፡ ረገድ ፡ ሊደክሙበት ፡ ይገባል።

እንዲሁም ፡ በሀገራችን ፡ የራሳችን ፡ የሆኑ ፡ ኃይልን ፡ የሚጠይቁ ፡ አያሌ ፡ ጨዋታዎች ፡ ይገኛሉ። እነሱም ፡ ሰውነት ፡ እንደሸቦ ፡ እንዲለመጥና ፡ እንዲጠመዘዝ ፡ እንደላስቲክ ፡ እንዲለጠጥና ፡ እንዲተጣጠፍ ፡ አድርገው ፡ መልካም ፡ ቅጥን ፡ (ፎርም) ፡ የሚሰጡ ፡ ቁመናን ፡ የሚያሳምሩ ፡ ናቸው ፡ አዘውትረው ፡ በተጠቀሙባቸው ፡ ጊዜ ፡ ለአካል ፡ ጥንካሬን ፡ ለሕይወት ፡ ጤንነትን ፡ ለማስገኘት ፡ ፍቱን ፡ መድኃኒት ፡ ናቸው።

እነዚህንም ፡ ጂምናስቲክ ፡ ወይም ፡ እስፖርት ፡ በሚባል ፡ ጠቅላላ ፡ ስም ፡ ልንጠራቸው ፡ እንችላለን ፡ ኃይል ፡ የሚፈልጉት ፡ ጨዋታዎች ፡

የሚጠይቁት ፡ እንቅስቃሴ ፡ የእጅንና ፡ የእግርን ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ የመላ ፡ ሰውነትን ፡ ጭምር ፡ ነው

ጂምናስቲክ ፡ ማድረግ ፡ የለመደ ፡ ሰው ፡ ቢሄድና ፡ ቢሮጥ ፡ አይደክመውም ፡ አያልበውም ፡ ጣመን ፡ አይሰማውም ፡ ዳገት ፡ ቁልቁለትም ፡ አይፈራም። በአጭሩ ፡ የመላው ፡ ሰውነቱ ፡ ሥራሥሮች ፡ የተፍታቱ ፡ ስለሆኑ ፡ በምንም ፡ ዓይነት ፡ ቢሆን ፡ የኃል ፡ ሥራ ፡ አያሰቅቀውም ፡ እስፖርት ፡ አዘውታሪም ፡ ጦርነት ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ ሠይፍ ፡ ጐራዴና ፡ ጦር ፡ በመመከት ፡ ገደል ፡ በመውረድ ፡ ዳገት ፡ ዛፍና ፡ መሰላል ፡ በመውጣት ፡ ውሃ ፡ በመዋኘት ፡ ጦር ፡ በመወርወር ፡ በመጋለብ ፡ በመሮጥ ፡ በመዝለል ከብዙ ፡ አደጋዎች ፡ ሊድን ፡ ይችላል።

በእውነቱ ፡ በዚህ ፡ ክፍል ፡ የተጻፉትን ፡ ጨዋታዎች ፡ አንድ ፡ ባንድ ፡ ተንትኖ ፡ የሚሰጡትን ፡ አገልግሎት ፡ ጭምር ፡ መረዳት ፡ በጠቀመ ፡ ነበር። ዳሩ ፡ ግን ፡ ከላይ ፡ እንደገለጽኩት ፡ ሁሉ ፡ የተነሳሁበት ፡ ዓላማው ፡ ለጣዕም ፡ ያህል ፡ ከሁሉም ፡ ትንሽ ፡ ትንሽ ፡ ቅምሻ ፡ ለመስጠት ፡ ስለሆነ ፡ ሰፊውን ፡ ሃሣብ ፡ ለአጥኚዎች ፡ ትቸዋለሁ።

ቅምሻ ፡ ለማለት ፡ ያስደፈረኝም ፡ «መስካችን ፡ ሰፊ ፡ ነው ፡ ግራና ፡ ቀኝ ፡ ቢሄዱ ፡ አያደናቅፍም» ፡ ላልኩት ፡ ማስረጃ ፡ እንዲሆኑኝ ፡ ከልምዶቻችን ፡ ውስጥ ፡ አንዳንዶቹን ፡ ለምሳሌ ፡ ያህል ፡ ጫፍ ፡ ጫፉቸውን ፡ ብቻ ፡ ለመጥቀስ ፡ በመገደዴ ፡ ነው

እነዚህ ፡ ከላይ ፡ የተገለጹት ፡ ባህሎቻችን ፡ እንዳሉ ፡ በሙሉ ፡ ተጠብቀው ፡ እሥራ ፡ ላይ ፡ እንዲውሉ ፡ ባይመከርም ፡ ቅሉ ፡ ከውስጣቸው ፡ አንዳንዶቹ ፡ እየተመረጡ ፡ ጊዜው ፡ በሚጠይቀው ፡ ዓይነት ፡ «በሜቶድ» ቢዘጋጁ ፡ ከኛም ፡ አልፈው ፡ ለእስፖርት ፡ አፍቃሪዎች ፡ እንደሚጠቅሙ ፡ እተማመናለሁ።

ኣሁን ፡ እነዚህን ፡ ጨዋታዎች ፡ ምን ፡ እየተባሉ ፡ እንደሚጠሩ ፡ ለማስረዳት ፡ ስል ፡ በመልክ ፡ በመልካቸው ፡ እንደሚከተለው ፡ ዘርዝሬ ፡ አቅርቤአቸዋለሁ።

ሀ ፡ ኃይልንና ፡ ልምምድን ፡ የሚጠይቁ።

1. ፈረስ ፡ ግልቢያ ፡
2. ውሃ ፡ ዋና ፡
3. ዒላማ ፡ ተኩስ ፡
4. አውሬ ፡ አደን ፡
5. ጉግስ ፡ ጨዋታ ፡
6. ዘንግ ፡ ውርወራ ፡
7. ጊጤ ፡ ጨዋታ ፡
8. ገና ፡ ጨዋታ ፡
- ጥንጓን ፡ ወይም ፡ ዕሩሯን ፡ በዱላ ፡ መምታት ፡
- ኳስን ፡ ይዞ ፡ መሮጥ ፡
9. ምክት ፡
10. ቅምጦሽ ፡
11. ሽምጥ ፡
12. ቁጭቋጮ ፡
13. ትግል ፡
14. እርግጫ ፡ (የእግር ፡ ቦክስ)
15. ዝላይ ፡
16. ሩጫ ፡
17. ምክት ፡ በመሣሪያ ፡
18. ጅራፍ ፡ መጋረፍ ፡
19. ማጋፈት ፡ (ለሴት) ፡
20. ጮቤ ፡
21. እስክስታ ፡ (ውዝዋዜ) ፡

ለ ፡ ማሰላሰልንና ፡ ቅልጥፍናን ፡ የሚጠይቁ።

1. ሠንጠረዥ ፡
2. ገበጣ ፡

3. ተላቲን ፡
4. አካንዱራ ፡

## ሐ ፡ የተፈጥሮ ፡ ስጦታን ፡ ወይም ፡ ዝንባሌን ፡ የሚጠይቁ።

1. በገና ፡
2. መሰንቆ ፡
3. ክራር ፡
4. ዋሽንት ፡
5. እንቢልታ ፡

ከዚህ ፡ በላይ ፡ ከተጠቀሱት ፡ ባህሎች ፡ ውስጥ ፡ ብዙዎቹ ፡ በዝከረ ፡ ነገር ፡ መጽሐፍ ፡ ተዘርዝረው ፡ ተጽፈው ፡ ስለሚገኙ ፡ በመጀመሪያው ፡ እትም ፡ ከገጽ ፡ 874 ፡ እስከ ፡ ገጽ ፡ 895 ፡ መመልከት ፡ ይጠቅማል።



# ስለደራሲው በጥቂቱ

ብላቴን ጌታ ማኅተመ ሥላሴ ወልደ መስቀል በ፲፰፻፹፪ ዓ.ም. በሰሜን ሸዋ ቡልጋ ውስጥ የተወለዱ ታዋቂ የሥነ ጽሑፍ ሰው ከመኾናቸው ባሻገር፤ በፈረንሳይ አገር የግብርና ትምሕርት ያጠናቀቁ ኢትዮጵያዊ ነበሩ። በስልጣንም መጀመሪያ የልዑል አልጋወራሽ መርድ አዝማች አስፋ ወሰን ፀሐፊ፤ የእርሻ ሚኒስቴር ምክትልና ዋና ሚንስትር፤ የገንዘብ ሚኒስትር፤ የሕዝብ አገልግሎት ሚኒስትር እንዲሁም የዘውድ አማካሪ በመሆን አገራቸውን አገልግለዋል።

በታሪክ ፊት ከፍተኛ ግምት የሚሰጠውና አጠቃላዩን የኢትዮጵያን ሕዝብ ኢኮኖሚያዊ፤ ማኅበራዊና ፖለቲካዊ እንቅስቃሴ የሚዘክረውን «ዝክረ ነገር» የተሰኘውን መጽሐፍ በ ፲፱፻፵፪ ዓ.ም. ለህትመት አብቅተዋል። እኚህ ታላቅ የሥነ ጽሑፍ ሰው፤ በታሪክና ባህል፤ በትምህርተ ጥበባት እና በመንፈሳዊ ግንባራት አሥራ አምስት መጻሕፍትን አበርክተዋል። እነዚህም መጻሕፍ

## <u>የደራሲው ሥራዎች</u>

<u>አንደኛ ፡ ክፍል ፡ ታሪክና ፡ ባህል።</u>

፩ ፡ ዝክረ ፡ ነገር፤　(ሁለት ፡ ጊዜ ፡ ታትሟል)

፪ ፡ ያባቶች ፡ ቅርስ፤　(ሦስት ፡ ጊዜ ፡ ታትሟል)

፫ ፡ እንቅልፍ ፡ ለምኔ፤　(ሦስት ፡ ጊዜ ፡ ታትሟል)

፬ ፡ አማርኛ ቅኔ' ነጠላ፤ (አምስት ፡ ጊዜ'ታትሟል)

፭ ፡ ስለኢትዮጵያ ፡ የመሬት ፡ ሥሪት ፡ አስተዳደርና ፡ ግብር፤

፮ ፡ አማርኛ ፡ ቅኔ ፡ ከነመፍቻው፤ (ሦስት ፡ ጊዜ ፡ ታትሟል)

፯ ፡ ያገር ፡ ባህል ፡ (ቡሏጋ)፤

፰ ፡ ባለን ፡ እንወቅበት፤

፱ ፡ የቀድሞው ፡ ዘመን ፡ ጨዋ ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ ጠባይና ፡ ባህል፤

፲ ፡ ቼ ፡ በለው፤

ሁለተኛ ፡ ክፍል ፡ ትምህርተ ፡ ጥበባት።

፲፩ ፡ ጥበበ ፡ ገራህት፤

፲፪ ፡ ብዕለ ፡ ገራህት፤

ሦስተኛ፡ ክፍል፡ አንክሮ፡ ለእግዚአብሔር፡ ተዘክሮ፡ ለነፍስ ፡ (መንፈሳዊ)።

፲፫ ፡ ዕጹብ ፡ ድንቅ፤

፲፬ ፤ ስም ፡ ከመቃብር ፡ በላይ፤

፲፭ ፤ ሰዋስወ ፡ ሰማይ፤